

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ

የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ሀምሌ/ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

1. መግቢያ 1
2. የትብብር መድረኩ ራዕይ፣ተልዕኮና ዕሴቶች 2
2.1 ራዕይ/Vision 2
2.2 ተልዕኮዎች/Mission 2
2.3 ዕሴቶች/ Values 3
3. የተከናወኑ ዋናዋና ግቦችና ተግባራት፡- 4
3.1. የአቅም ግንባታና እውቀት ሽግግር ስራዎች 4
3.1.1 የአገር ውስጥ የልምድ ልውውጥን በተመለከተ 4
3.1.2 የውጭ አገር የልምድ ልውውጥን በተመለከተ 10
3.1.3 የአቅም ግንባታ ስልጠናን በተመለከተ፤ 30
3.2. የሃብት ማፈላለግና ኔትወርኪንግ ስራዎችን በተመለከተ 61
3.3. የኮሙኒኬሽን ስራዎች በተመለከተ 73
3.4. ገቢን ለመሰብሰብ የተከናወኑ ግቦችና ተግባራት 85
3.5. የፕሮግራምና የፕሮጀክት ስራዎች የክትትልና ግምገማ ተግባራት 97
4. በእቅድ ተይዘው ያልተከናወኑ ተግባራትና ያልተከናወኑበት ምክንያት 102
5. ከእቅድ ውጭ የተከናወኑ ተግባራት 103
6. ያጋጠሙ ችግሮች፤የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤ 111
6.1. ያጋጠሙ ችግሮች 111
6.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 112
6.3. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 112
7. የማስፈጸሚያ ስልቶች፤ 114
7.1 ክትትልና ድጋፍ 114
7.2 ግምገማ፤ ሪፖርትና ግብረ-መልስ 114
8. በበጀት አመቱ አፈጻጸም በጥንካሬና በድክመት የታዩ ጉዳዮች፤ 115
8.1. በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች 115
8.2. በድክመት የታዩ ጉዳዮች 117
9. ማጠቃለያ 118
አባሪ፡- በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የ2017 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ማጠቃለያ፤ 121

1. መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከተሞች ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት እየተስፋፉና የህዝብ ቁጥራቸውም በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህ የከተሞች መስፋፋት በአንድ በኩል የኢኮኖሚ እድገት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ማዕከል በመሆን ለሀገራዊ ብልጽግና ወሳኝ ዕድሎችን የሚፈጥር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመሠረተ ልማት እጥረት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ጫና፣ የአካባቢ ብክለት እና ሌሎች ውስብስብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶችን ይዞ ይመጣል፡፡ እነዚህን ዕድሎች በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ተግዳሮቶችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ስልታዊና የተቀናጁ ምላሾችን መዘርጋት ከመቼውም ጊዜ በላይ ወሳኝ ሆኗል፡፡

ይህንን የከተሞች እድገት ለማስቀጠል ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግና ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ እንደ ተቋም ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የመድረኩ ዋና ተልዕኮ በከተሞች መካከል ጠንካራ የትስስርና የመደጋገፍ ባህልን በማጎልበት፣ በጋራ የመማርና የመደጋገፍ ሥርዓት እንዲፈጥሩ በማድረግ እንዲሁም በዓለም አቀፍና በሀገር ደረጃ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ፈጠራ የታከለባቸው መፍትሔዎችን በማጋራት የጋራ ልማትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ልምዶችን በመቀመርና በአባል ከተሞች በማስፋፋት እንዲሁም የአመራሩንና የባለሙያዎችን የአፈጻጸም አቅም በተከታታይ በመገንባት ላይ ያተኮሩ ተግባራትን እንደ ዋነኛ አጀንዳ አድርጎ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሰረትም የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ በመንደፍ ወደ ትግበራ ተገብቶ ሲከናወን የቆየ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ለማከናወን በተያዘው መርሃ-ግብር መሠረት የትብብር መድረኩ የ2017 በጀት ዓመት ሥራዎች አፈጻጸም ሪፖርት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

2. የትብብር መድረኩ ራዕይ፣ተልዕኮና ዕሴቶች

2.1 ራዕይ/Vision

ዘላቂ ልማት የተረጋገጠባቸው፣ለኑሮ ምቹ፣ አምራች እና ተወዳዳሪ የኢትዮጵያ ከተሞችን ለመፍጠር እሴት የሚጨምር የከተሞች ማህበር መሆን ነው።


2.2 ተልዕኮዎች/Mission

1/ ከተሞች ተልዕኳቸውን እንዲወጡ መደገፍ፤


2/ ለከተሞች የልምድ ልውውጥ እና የእውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

3/ ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤መቀመርና ለአባል ከተሞች ማሰራጨት፤

4/ የከተሞችን እህትማማችነት እና ጠንካራ ትብብር ማሳደግ፤



2.3 ዕሴቶች/ Values



3. የተከናወኑ ዋናዋና ግቦችና ተግባራት፡-

3.1. የአቅም ግንባታና እውቀት ሽግግር ስራዎች

3.1.1 የአገር ውስጥ የልምድ ልውውጥን በተመለከተ

ግብ 1፡"በወቅታዊ የከተማ ልማት አጀንዳዎች" ዙሪያ ያተኮረ በ100 አባል ከተሞች መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደጥናት ለማዘጋጀት ታቅዶ 80 ተሳታፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞችን የወደፊት የእድገት አቅጣጫ ለመቅረጽና በጋራ አመራር የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ያለመ ወሳኝ የትብብር መድረኩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤና የልምድ ልውውጥ መድረክ ከጥቅምት 26-27/2017 ዓ.ም 80 የከተማ ከንቲባዎች እና የዘርፉ አመራሮች (63 የከተማ ከንቲባዎች፣ 4 ምክትል ከንቲባዎች፣ 3 የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች፣ 3 የከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና 7 የክልል የከተማ ልማትና መሠረተ ልማት ዘርፍ ቢሮ ኃላፊዎች) በተገኙበት በከተማ ፕላን አፈጻጸም በተለይም በኮሪደር ልማት ላይ ያተኮረ የልምድ ልውውጥ አውደጥናት በሐዋሳ ከተማ ተካሂዷል፡፡

የመድረኩ ዋነኛ ትኩረት ዕውቀትን ወደ ተግባራዊና ዘላቂ ለውጥ መቀየር ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ተሳታፊዎች የከተሞችን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት እንዲገነዘቡና ውሳኔዎቻቸውን በመረጃ ላይ እንዲመሰርቱ የሚያስችላቸው የ20 ከተሞችን ተጨባጭ ሁኔታ የዳሰሰው የጥናት ሰነድ ግኝቶች ቀርበዋል፡፡ ይህ የጥናት ውጤት የከተሞችን የጋራ ተግዳሮቶችና ልዩ እድሎች በግልጽ በማሳየት ለቀጣይ የፖሊሲና የስትራቴጂ ቀረጻ እንደ ወሳኝ ግብዓት ሆኖ አገልግሏል፡፡ በተጨማሪም ከተሞች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ተቋቁመው ቀጣይነታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያስችላቸውን 'የከተሞች ችግሮችን የመቋቋም አቅም (Urban Resilience)' ጽንሰ-ሐሳብ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ በመፍጠር መሪዎቹ ወደፊት ለሚመጡ ፈተናዎች ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል፡፡

የዚህ መድረክ የላቀ ስኬት ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር በማስተሳሰሩ ላይ ሲሆን የሐዋሳ ከተማ በኮሪደር ልማት ያስመዘገበችው ስኬትና ተሞክሮ የቀረበ ሲሆን የከተማው ክቡር ከንቲባ የልማቱን ስኬትና የተሻገሯቸውን ተግዳሮቶች በማቅረብ ለተሳታፊዎች ከፍተኛ መነሳሳትን ፈጥረዋል፡፡ ይህ የዕውቀት ሽግግር በንግግር ብቻ ሳይወሰን ሁሉም አመራሮች በቀጥታ በመስክ በመገኘት የልማቱን ውጤት በመስክ ጉብኝት እንዲያዩ ተደርጓል፡፡ ይህ የመስክ

ምልከታ የኮሪደር ልማት ጽንሰ-ሐሳብ በወረቀት ላይ ብቻ ያለ እቅድ ሳይሆን በትክክለኛ አመራርና ቁርጠኝነት ወደ መሬት ወርዶ የዜጎችን ህይወት የሚለውጥ ተጨባጭ እውነታ መሆኑን አረጋግጧል። ይህም ለሌሎች ከተሞች በቀላሉ ሊቀስሙትና ሊተገብሩት የሚችሉትን ተግባራዊ ትምህርት ሰጥቷቸዋል።

ይህ ጉባኤ በውይይቶች፣ በተጨባጭ መረጃዎችና በተግባራዊ ልምድ የተደገፈ በመሆኑ የተቀመጠለትን ግብ አሳክቷል። አመራሮቹ በጋራ በመምከር ከተሞቻቸውን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል አዲስ ኃይልና ራዕይ ይዘው እንዲመለሱ አስችሏቸዋል።

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀትን በተመለከተ</u>

በተካሄደው የአውደጥናት መድረክ ላይ በሶስት ወሳኝና እርስ በእርስ በተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም የኮሪደር ልማት፣ የከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ጥናት እና የከተሞች ችግርን የመቋቋም አቅም(Urban Resilience) ላይ ሁለንተናዊ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ያለመ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር ተካሄዷል። ይህ የተቀናጀ አካሄድ ከተሞችን ውብና ዘመናዊ ከማድረግ ባለፈ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲሰጡና ለወደፊት ቀውሶች ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችል ጠንካራ መሠረት ለመጣል ታቅዶ የተከናወነ ነው ።

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት በኮሪደር ልማት ዙሪያ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን ከጽንሰ-ሐሳብና ከስትራቴጂ ዝግጅት ጀምሮ የእቅድ ዝግጅት፣ የዲዛይን ስራዎች፣ የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ እንዲሁም ከመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር ያለውን ቅንጅት በዝርዝር ዳሷል። በተጨማሪም እንደ ወሰን ማስከበር፣ የተነሺዎች አያያዝና የካሳ ክፍያ፣ የግንባታ ግብዓት ጥራት ማረጋገጥ ያሉ ፈተናዎችንና መፍትሄዎቻቸውን ተንትኗል። ትግበራውም የእግረኛ መንገድ፣ የሳይክል ሌይን፣ አረንጓዴ ልማት እና ስማርት ፓርኪንግን የመሳሰሉ የዘመናዊ ኮሪደር ልማት ክፍሎችንም አጠቃሏል። ይህ ሁሉን አቀፍ ይዘት ያለውን ተሞክሮ አመራሮች የኮሪደር ልማትን እንደ አንድ ፕሮጀክት ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ የከተማ ትራንስፎርሜሽን ሂደት እንዲገነዘቡት አስችሏል።

በተጨማሪም የ20 ከተሞች ወቅታዊ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጥናት ግኝቶች መቅረቡ አመራሮች ውሳኔዎቻቸውን በተጨባጭ መረጃ ላይ እንዲመሰርቱና የህዝብን ጥያቄዎች በውጤታማነት እንዲመልሱ ያላቸውን አቅም አጎልብቷል። በተጓዳኝም በከተሞች ችግርን የመቋቋም አቅም (Urban Resilience) ዙሪያ የተሰጠው ገለጻ የጽንሰ-ሐሳቡን ምንነት፣ ዋና ዋና ምሰሶቹን፣ የመለኪያ ስልቶችን፣ዓለም አቀፍ ማዕቀፎችንና ስኬታማ ተሞክሮዎችን አካቷል።

ይህም ከተሞችን ለኑሮ ምቹና ከአደጋ ነጻ ለማድረግ የሚያስችሉ መሰረታዊ መርሆዎችን በማስተዋወቅ አመራሮቹ የረዥም ጊዜ የከተማ ፕላን እንዲኖራቸው አስችሏል።

ይህንን ሰፊ ዕውቀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ያጣመረ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። የሐዋሳ ከተማ ክቡር ከንቲባ ከተማቸው በኮሪደር ልማት ያለፈችበትን የገፃጅት፣ የትግበራና የማጠቃለያ ምዕራፍ በተሞክሮ መልክ ሲያቀርቡ የቀረቡት ጽንሰ-ሐሳቦች በተግባር የተፈተኑና ውጤታማ መሆናቸውን አሳይቷል። ይህንን ተከትሎ ተሳታፊዎቹ የተብራራላቸውን የልማት ሥራዎች በመስክ በመገኘት መጎብኘታቸው ዕውቀቱ በአዕምሯቸው ውስጥ እንዲሰርጽና ከፍተኛ መነሳሳትን እንዲፈጥር አድርጓል።

የመርሃ ግብሩ ዋነኛ ትኩረት ዕውቀቱ በስልጠናው አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ነበር። ይህንን ለማሳካትም የሐዋሳ የኮሪደር ልማት የተሞክሮ ሰነድ እና የከተሞች ችግርን የመቋቋም አቅም(Urban Resilience) የስልጠና ሰነድ በዲጂታል መልክ በጋራ በተከፈተው የቴሌግራም ቡድን ላይ ተጭነዋል። ይህ ዲጂታል ሥርዓት ተሳታፊዎቹ ከስልጠናው በኋላም መረጃዎቹን እንደ ቋሚ ማጣቀሻ እንዲጠቀሙ፤ ያገኙትን ዕውቀት ለሥራ ባልደረቦቻቸው በቀላሉ እንዲያጋሩ እና እንደ ቋሚ የእውቀት ማከማቻ እንዲያገለግል በማድረግ የፕሮግራሙን ተጽዕኖ ከፍ አድርጎታል ።

የተገኙ ውጤቶች

- የተሻሻለውን የድርጅቱን የመተዳደሪያ ደንብ በማዘመን እና በማጽደቅ ረገድ ጠቃሚ ግብአቶችን የማግኘት ዕድል ፈጥሯል።
- በ20 አባል ከተሞች የተካሄደው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናት ሪፖርት ለወደፊት ተመሳሳይ ስራዎች ጥሩ ትምህርት አስገኝቷል።
- ከተሞች እየተካሄደ ካለው የሐዋሳ ከተማ የኮሪደር ልማት አተገባበር ጠቃሚ ልምዶችን እንዲያገኙ በር ከፍቷል ።
- የትግራይ ክልል ከንቲባዎችንና ቢሮ ሃላፊዎችን ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ከመጡ ከንቲባዎችና አመራሮች ጋር የማገናኘት እድል አስገኝቷል።
- አዳዲስ አባል ከተሞች በአባልነት እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እድል ፈጥሯል።
- ለከተማ ከንቲባዎች እና የዘርፉ አመራሮች የከተማ ፕላን ትግበራ በመረጃ ላይ በተመሰረተ ውሳኔ መነሻ በማድረግ ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው የጋራ መግባባት ተፈጥሯል።



ምስል 1፡ የልምድ ልውውጡ ተሳታፊዎች በከፊል


- ***የተዘጋጀውን ስልጠናዊ አውደጥናት አስመልክቶ በመድረኩ ላይ ስለቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮችና አቀራረብ እንዲሁም ስልጠናዊ አውደጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ምቹነትና የተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ወቅታዊነት በተመለከተ በተሳታፊዎች የተሞላ የመገምገሚያ ቅጽ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተመላክቷል፡፡***

የመድረክ ገለጻዎች ግምገማ



Made with Napkin

. አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ፤



❖ ከላይ በተመለከተው ቻርት እንደሚታየው የተካሄደውን አውደጥናት መድረክ አስመልክቶ ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ በተደረገው መሰረት ተሳታፊዎች የቀረቡት ተሞክሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት

የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኩ በሁሉም ረገድ የተሳካና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠረና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡

- በመሆኑም የአገር ውስጥ አውደጥናትና ልምድ ልውውጥ አፈጻጸምን በተመለከተ በኮሪደር ልማት አፈጻጸም ዙሪያ 80 ተሳታፊዎች፣ከኔዘርላንድ የከተሞች ማህበር (VNGi) ዊአር ኤብል ፕሮግራም ጋር በመተባበር መጋቢት 15/2015 ዓ.ም በአዳማ ከተማ አስተዳደር በአካታች የስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ 35 ተሳታፊዎች በተገኙበት የልምድ ልውውጥ አውደጥናት የተካሄደ ሲሆን ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአንድ የአውደጥናት መርሃግብር ያነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

3.1.2 የውጭ አገር የልምድ ልውውጥን በተመለከተ

ግብ2፡ ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተሞች ከንቲባዎችና የማኔጅመንት አባላት የተውጣጡ 28 ተሳታፊዎች በተለያዩ አለም አቀፍ ጉባኤዎች እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 23 ተሳትፈው የእቅዱ 82 በመቶ ተከናውኗል፡፡

<u>3.1.2.1 በኬንያ ኪሱሙ ከተማ በተካሄደው 4ኛው የከተማ ኢንቨስትመንት ኮንፈረንስ እና ስልጠና</u>

- የኢትዮጵያ ከተሞችን የልማትና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማሳደግና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም በተያዘው ዕቅድ መሠረት የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ከንቲባዎች የሆኑ የደሴ፣ የሽሬ እንዳስላሴ፣ የይርጋጨፌ፣ የግልገል በለስ፣ የባምባሲ እና የመቱ ከተማ ክቡራን ከንቲባዎች እና የትብብር መድረኩ የዕቅድ ዝግጅት ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከህዳር 16 -18/2024 ዓ.ም ኬንያ ኪሱሙ ከተማ ላይ በተካሄደው 4ኛው የከተማ ኢንቨስትመንት ኮንፈረንስ እና ስልጠና ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ መድረኩም የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ለዘላቂ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ለአፍሪካ ሉዓላዊ መንግስታት የእድገት ጎዳና' ('Leveraging the AfCFTA for Sustainable Trade and Investment:A Development Pathway for African Sub-Sovereigns.') በሚል መሪ ቃል ከንቲባዎች፣

አለም አቀፍ ተቋማት፣ የየአገራት የከተሞች ማህበራት እና ተመራማሪዎች በተገኙበት ተካሂዷል።

- የኮንፈረንሱ አንዱ ዓላማ ከ AfCFTA ግቦች ጋር በማቆራኘት በአፍሪካ አገራት ክልሎችና ከተሞች መካከል የንግድ፣ የልማት እና የኢንቨስትመንት ዕቅዶችን በማስተዋወቅ እና የእርስ በርስ ልምድ ልውውጥ በማድረግ የላቀ ትብብር ለመፍጠር ነው። በኮንፈረንሱም የኢትዮጵያ ከተሞች ከንቲባዎች ከሌላ አገራት ከንቲባዎች ጋር የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፤ በኮንፈረንሱ በተሰጠው ስልጠና አቅማቸውን ገንብተዋል፤

- ክቡራን ከንቲባዎች በመድረኩ በቀረቡ የተለያዩ ፓናል ውይይቶች ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን ለአብነትም የአህጉራዊ የፋይናስ ተቋማት(አፍሪኤግዚም ባንክ) ለአፍሪካ አካባቢያዊ ሉዓላዊ መንግስታት የሚያደርጉትን የብድርና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጥባቸውን መስኮች ለተሳታፊዎች በማቅረብ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ሆኗል። በዚሁ መሰረትም ክቡራን ከንቲባዎች ከባንኩ የስራ ኃላፊዎች ጋር ትስስርና አጋርነት ለመፍጠር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ለማድርግ ዕድል አግኝተዋል። በተያያዘም በአፍሪካ አካባቢያዊ ሉዓላዊ መንግስታት ዘንድ ያሉ የንግድና ኢንቨስትመንት ዕድሎችን እንዲሁም በኢንቨስትመንት ማስተዋወቅና መሳብ ዙሪያ ጥልቅ እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙና ግንዛቤያቸውን ከፍ ለማድረግ የሚረዱ የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ መፍጠሪያ ስትራቴጂዎችና ምርጥ ተሞክሮዎች ቀርበው ልምድ ተወስዶባቸዋል።

- በዚህ ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ ከንቲባዎች በርካታ ተግባራትን በስኬት አከናውነዋል። በመጀመሪያ ከሌሎች አገራት ከመጡ አቻዎቻቸው ጋር በመወያየት የተሻሉ የከተማ አስተዳደር፣ የኢንቨስትመንት መስህብና የንግድ ስልቶችን ተለዋውጠዋል። በሁለተኛ ደረጃ በጉባዔው በተሰጠው ልዩ ሥልጠና አማካኝነት የአመራር ክህሎታቸውንና አቅማቸውን ገንብተዋል። በተጨማሪም ለቀጣይ ትብብርና ድጋፍ መሰረት የሚጥሉ የእህትማማች ከተማ ግንኙነቶችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ውይይቶችን በማድረግና የአገራችንን መልካም ገጽታ በመገንባት እንደ አንድ አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል። ከንቲባዎቹ ያገኙት እውቀት፣ የፈጠሩት ግንኙነትና ያስተዋወቁት የኢንቨስትመንት ዕድል ለከተሞቻቸው ቀጣይ ዕድገት ወሳኝ ግብዓት ነው።


- በመድረኩ እንዲሳተፉ የቪዛና ተያያዥ ጉዳዮች ከተመቻቸላቸው መካከል የአርባምንጭ ከተማ ክቡር ከንቲባ ባጋጠማቸው ተደራራቢ ስራ ምክንያት ሊሳተፉ አልቻሉም። በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም ደረጃ 88 በመቶ ነው።

<u>የእውቀት ሽግግርና ሰርፀትን በተመለከተ፤</u>

የእውቀት ሽግግርና ሥርጸት የአንድን ተቋምም ሆነ የአገርን ቀጣይነት ያለው ዕድገት ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ ሁለት ተያያዥና ወሳኝ የአስተዳደር መሣሪያዎች ናቸው። የእውቀት ሽግግር ማለት ከአንድ ምንጭ ወደ ሌላው አዲስ ክህሎትን፣ መረጃንና ልምድን የማስተላለፍ ሂደት ሲሆን፣ ሥርጸት ደግሞ ይህ የተገኘው እውቀት በሰፊው ተሰራጭቶና ወደ ተግባር ተለውጦ ተቋማዊ ለውጥ የሚያመጣበት ደረጃ ነው። የእውቀት ሥርጸት የሚጀምረው አመራሮቹ ወደየከተሞቻቸው ሲመለሱ ያገኙትን ልምድ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብና የጋራ ውይይት በመፍጠር ነው። ይህንን ተከትሎም ከጉባዔው የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች በመጠቀም ለየከተሞቻቸው የሚሆኑ ተጨባጭ የድርጊት ዕቅዶችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። ሂደቱን ይበልጥ ለማስፋት ከንቲባዎቹ ያገኙትን ክህሎት ለሌሎች የከተማው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በማካፈል የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ማካሄድ አለባቸው። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ከጉዞው የተገኙትን ቁልፍ ትምህርቶች በማጠናቀር ለሁሉም አባል ከተሞች በስልጠና መድረኮች ማካፈል ያለበት ሲሆን ይህም እውቀቱት ተቋማዊ ያደርገዋል።

በዚሁ መሰረትም ጉባዔው ላይ በተለይም **"በኢንቨስትመንት" ዙሪያ** ሰፊ የእውቀት ሽግግርና ሥርጸት መርሃ ግብር ተካሂዷል። ይህ መርሃ ግብር በርካታ ዝርዝር ርዕሰ ጉዳዮችን አካቷል። ከእነዚህም መካከል የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ጽንሰ-ሀሳብና መርሆዎች፣ ከተሞች ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚጠቀሙባቸው ውጤታማ ስትራቴጂዎች፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ዘዴዎች፣ ውጤታማ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፖሊሲዎች፣ በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንዲሁም በሌሎች አገራት የተገኙ ስኬታማ ተሞክሮዎች በስፋት ተዳሰዋል። ይህንን እውቀት ለማስተላለፍም የተለያዩ ስልቶች ጥቅም ላይ ውለዋል። መርሃ ግብሩ **በሥልጠና፣ በፓናል ውይይቶች**፣ በተለያዩ ከተሞች የተዘጋጁ የኢንቨስትመንት እድሎችን በሚያሳዩ **ኤግዚቢሽኖች** እና **የኪሱሙ ከተማን ተጨባጭ ልምድ ለመቅሰም በተደረገ የመስክ ጉብኝት** የተደገፈ ነበር። ይህም ከንቲባዎቹ ንድፈ-ሐሳባዊ እውቀትን ከተግባራዊ ልምድ ጋር እንዲያዋህዱ አስችሏቸዋል።

በኮንፈረንሱ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት የተካሄደባቸው ዝርዝር ርዕሰ ጉዳዮች፡-







ምስል 2፡ 4ኛው የኢንቨስትመንት ኮንፈረንስ እና ስልጠና ተሳታፊዎች (*November/2024*)

የተገኙ ውጤቶች

- **የተሻሻሉ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ዕድሎች፡ ክቡራን ከንቲባዎች በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ስምምነት/AfCFTA/ ማዕቀፍ ስለ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ዕድሎች ተስፋ መሰነቃቸው፡፡**

- **ክቡራን ከንቲባዎች ከአፍሪኤግዚም ባንክ የስራ ኃላፊዎች ጋር ትስስርና አጋርነት ለመፍጠር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ለማድርግ ዕድል አግኝተዋል፡፡**

- ተሳታፊ ክቡራን ከንቲባዎች ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከንቲባዎች ጋር በንግድ፣ በኢንቨስትመንት እና በአስተዳደር ዘርፎች የልምድ እና እውቀት ልውውጥ በማድረጋቸው ክህሎታቸው እና እውቀታቸው ጨምሯል።

- የተጠናከረ ክልላዊ ግንኙነቶች፡- ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከተማ ከንቲባዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነቶች ተፈጥሯል።

- ተሳታፊዎቹ በኪሱሙ ከተማ የተደረገላቸውን የመስክ ጉብኝት በመጠቀም፣ በንድፈ-ሀሳብ የተማሩትን በተግባር የተደገፈ ተሞክሮ በማየት ግንዛቤያቸውን አጠናክረዋል።

- የኢትዮጵያ ከተሞች በአህጉራዊ መድረክ የላቀ ዕይታ (visibility) እና እውቅና እንዲኖራቸው አስችሏል። የአፍሪ ኤግዚም ባንክ የትብብር መድረኩ ለክልላዊና አካባቢያዊ መንግስታት አቅም ግንባታ የሰጠውን ትኩረትና የልኡክ ቡድኑ አባላት ላደረጉት ንቁ ተሳትፎ የምስጋና ደብዳቤ መላክ ችሏል።

- የአገራችን የከተማ ልማት ስትራቴጂዎችን ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ሰፊ ዓላማዎች ጋር ለመቃኘት የሚያስችሉ ጠቃሚ ግብዓቶች ተገኝተዋል።

3.1.2.2 የዓለም ከተሞችና የአካባቢ መንግሥታት ድርጅት (UCLG) ሥር በሚገኘው የአቅም ግንባታና የተቋማት ልማት (CIB) የሥራ ቡድን ጉባዔ ተሳትፎን በተመለከተ፤

- የኢትዮጵያ ከተሞችን ዓለም አቀፍ ትብብርና ተጠቃሚነት ለማሳደግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የትብብር መድረኩ ሁለት የማኔጅመንት አባላት በተላከላቸው ግብዣ መሠረት በኔዘርላንድስ ተገኝተው ተሳትፎ አድርገዋል። አመራሮቹ በዓለም ላይ የሚገኙ ከተሞችንና የአካባቢ መንግሥታትን በአንድ መረብ በሚያስተሳስረው የዓለም ከተሞችና የአካባቢ መንግሥታት ድርጅት (UCLG) ሥር በሚገኘው የአቅም ግንባታና የተቋማት ልማት (CIB) የሥራ ቡድን ጉባዔ ላይ በመገኘት የኢትዮጵያ ከተሞችን ወክለዋል። በመድረኩ የኢትዮጵያ ከተሞችን በተለያዩ የልማት መስኮች በተለይም በአቅም ግንባታ ዘርፍ ሊደግፉ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ስልታዊ ግንኙነቶችን መፍጠር ትኩረት ተደርጎ ተሰርቷል። በቆይታቸውም ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት (U.S. State Department) ከፍተኛ ባለሥልጣን፣ ከኔዘርላንድስ ከተሞች ማኅበር ዋና ዳይሬክተር፣ ከUCLG የሥራ ቡድን አባላት እንዲሁም ተጽዕኖ ፈጣሪ ከሆኑት ከብሪክስ አገራት የከተሞች ማኅበር ተወካዮች ጋር ፍሬያማ ውይይቶችን አድርገዋል።

ከተደረጉት የማግባባት ሥራዎች መካከል ዋነኛውና ትልቁ ***የሸገር ከተማ ከንቲባ በብሪክስ አገራት የከተሞች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲመረጡ*** ለማስቻል የተደረገው ጠንካራ ጥረት ሲሆን ይህም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የከተሞች መድረኮች ላይ ያላትን ተደማጭነትና የመሪነት ሚና ለማሳደግ የተወሰደ ወሳኝ ስትራቴጂያዊ እርምጃ ነው።





ምስል 3፡ የየሀገራት የከተሞች ማህበራት ኔትወርክ ዋና ተቋም (UCLG) የአቅም እና ተቋማዊ ግንባታ (CIB) ጉባዔ በኔዘርላንድ ሄግ ከተማ *(August/2024)*

- በኔዘርላንድስ ከተካሄደው ስኬታማ ውይይት በመቀጠል የትብብር መድረኩ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ጋር የጀመረውን ግንኙነት ወደ ተጨባጭ የትብብር መስኮች ለማሸጋገር የሚያስችል ቀጣይ እርምጃ ተወስዷል። በዚህም መሠረት ጥቅምት 14/2017 ዓ.ም በአሜሪካ ኤምባሲ የኢኮኖሚ ዘርፍ የሥራ ኃላፊዎችና በትብብር መድረኩ አመራሮች መካከል በመድረኩ ጽ/ቤት ውይይት ተካሂዷል። በውይይቱም ሁለቱ ተቋማት በቀጣይ በጋራ ሊሠሩ በሚችሉባቸው አጀንዳዎች ላይ በስፋት ተመካክረዋል። ይህንን ፍሬያማ ውይይት ተከትሎም ኤምባሲው ***የኢትዮጵያ ከተሞችን በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በመሠረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፎች ሊደግፍ የሚችል የፕሮጀክት ሀሳብ (Proposal) እንዲቀርብለት በይፋ ጠይቋል።*** ይህንን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ዝርዝር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለአሜሪካ ኤምባሲ የገባ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከኤምባሲው የሚሰጠውን ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።



ምስል 4፡ ከአሜሪካ ኤምባሲ ከመጡ የስራ ኃላፊዎች ጋር

3.1.2.3 የአዲሱ ብሪክስ+ የከተሞች ማኅበር ጉባዔ ተሳትፎን በተመለከተ፤

- **በተመሳሳይ በኔዘርላንድስ የተጀመረው የዲፕሎማሲ ጥረት ሌላ ወሳኝ ስኬት አስመዝግቧል፡፡ የትብብር መድረኩ ዋና ዳይሬክተር ከብሪክስ አገራት የከተሞች ማህበር ተወካዮች ጋር አስቀድመው ባካሄዱት የማግባባት ሥራና ባቀረቡት የእጩነት ጥቆማ አማካኝነት ከጥቅምት 21 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በዱባይ በተካሄደው የአዲሱ ብሪክስ+ ከተሞች ማኅበር ጉባዔ ላይ ኃላፊ ውጤት ተገኝቷል፡፡ ማኅበሩም የሸገር ከተማ ክቡር ከንቲባ ዶ/ር ተሾመ አዱኛን የምክትል ፕሬዚዳንትነት ቦታ እንዲይዙ በአብላጫ ድምፅ መርጧል፡፡ ይህ ምርጫ የኢትዮጵያ ከተሞች በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላቸውን ተደማጭነት በእጅጉ የሚያሳድግና አገራችን በዓለም አቀፍ የከተሞች ፖሊሲና የልማት አጀንዳዎች ላይ በቀጥታ ድምፅ እንዲኖራት የሚያስችል ታሪካዊ ስኬት ነው፡፡**



ምስል 5፡ የብሪክስ+ ከተሞች ማህበር ም/ፕሬዚዳንት እና የሸገር ከተማ ከንቲባ ክቡር ዶ/ር ተሾመ አዱኛ ሲያወያዩ (ከቀኝ ወደ ግራ ሁለተኛ ረድፍ ላይ)



ምስል 6፡ የአዲሱ የብሪክስ+ ከተሞች ማህበር ተሳታፊዎች በከፊል (*October/2024)*

3.1.2.4 በተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ ሰፈራ ፕሮግራም (UN-Habitat) ሁለተኛው የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ መደበኛ ጉባዔ ተሳትፎን በተመለከተ

- ከህዳር 25-27/2017 ዓ.ም በኬንያ ናይሮቢ በተካሄደው ሁለተኛው የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ ሰፈራ መርሃ ግብር (UN-Habitat) የስራ አመራር ቦርድ መደበኛ ስብሰባ ላይ የትብብር መድረኩ ዳሬክተር ጀነራል እና የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የኢትዮጵያን የከተማ ልማት ፖሊሲና ስኬታማ ተሞክሮዎች በዓለም አቀፍ መድረክ ለማስተዋወቅና ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ጋር ያለውን ትብብር ለማጠናከር ተገኝተው ነበር፡፡ ይህ ጉባዔ በዓለም ዙሪያ ያሉ የከተማ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች የሚሰባሰቡበት ከፍተኛ መድረክ በመሆኑ የኢትዮጵያን ተሞክሮ ለማካፈልና ስትራቴጂያዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር ትልቅ ዕድል የሰጠ ነበር፡፡

- በዚህ ወሳኝ መድረክ ላይ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ኢትዮጵያ በከተሞች ልማት ዘርፍ እያስመዘገበች ያለውን ተጨባጭ ለውጥ ለአለም አቀፉ ማኅበረሰብ በስፋት አብራርተዋል፡፡ በንግግራቸውም የአገሪቱ የከተማ ልማት ትኩረት ዘላቂ፣ አካታችና ማንኛውንም ጫና መቋቋም የሚችሉ (resilient) ከተሞችን በመፍጠር ላይ ያተኮረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህንን ለማሳካትም መንግሥት ከመሠረተ ልማት ግንባታ ባሻገር የዜጎችን የኑሮ ጥራት በቀጥታ የሚያሻሽሉና አካባቢን የማይጎዱ ፕሮጀክቶችን በቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ እየገነባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

- ለዚህም እንደ ማሳያ ኢትዮጵያ ወደ ሰው-ተኮር የልማት አካሄድ መሸጋገሯንና በተለይም ለዜጎች ጤናና ምቹ እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ለእግረኞች ምቹ የሆኑ የእንቅስቃሴ መስመሮች፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚያበረታቱ የብስክሌት መንገዶች እና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያገለግሉ ዘመናዊ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች በስፋት እየተገነቡ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡ ይህ ተሳትፎ የኢትዮጵያን ቁርጠኝነት ከማሳየቱም ባሻገር ከሌሎች አገራት ጋር የተሻለ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ለከተሞቻችን ተጨማሪ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ለማፈላለግ የሚያስችሉ የትብብር በሮችን የከፈተ ተልዕኮ ነበር፡፡



ምስል 7፡ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ ሰፈራ (UN-Habitat) **የስራ አመራር ቦርድ መደበኛ ስብሰባ** (***December/2024***)

3.1.2.5 4ኛው ዓለም አቀፍ የሥነ ሕንፃና ኮንስትራክሽን ፎረም ተሳትፎን በተመለከተ፤

- 7 የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ከንቲባዎች (የደብረማርቆስ፣ የኮምቦልቻ፣ የሆሳዕና፣ የዲላ፣ የማይጨው፣ የደጀን እና የወናጎ ከተሞች ክቡራን ከንቲባዎች) **ከየካቲት 29 እስከ መጋቢት 01/2017 ዓ.ም ሩሲያ ካዛን ከተማ** ላይ በተካሄደው 4ኛው ዓለም አቀፍ የስነ ህንጻና ኮንስትራክሽን ፎረም (the IV International Architectural and Construction Forum) ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ፎረሙም 'በብዝሃነት ውስጥ አንድነት' ('Unity in Diversity') በሚል መሪ ቃል ከንቲባዎች፣ አለም አቀፍ ተቋማት፣ የየአገራት የከተሞች ማህበራት እና ተመራማሪዎች በተገኙበት ተካሂዷል፡፡ የፎረሙ ዓላማ በአገራት በከተማ ልማትና በሥነ ህንጻ ዘርፍ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን እንደየአገራት ነባራዊ ሁኔታ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ እንዲሁም በከንቲባዎች፣ በአርክቴክቶች፣ በከተማ ፕላነሮች፣ በፖሊሲ አውጪዎች እና በሌሎች ተሳታፊዎች መካከል ትብብርን ለማጎልበት ነው፡፡ ፎረሙ ከስነ ህንጻ፣ ከከተማ ፕላን እና ከዘላቂ ልማት ጋር ተዛማችነት ያላቸውን ርእሰ ጉደዮችን ባካተተ መልኩ የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡




ምስል 8፡ የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ከንቲባዎች በፎረሙ በከፊል (*March/2025*)

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት፤</u>

ይህ በሩሲያ ካዛን ከተማ የተካሄደው 4ኛው ዓለም አቀፍ የሥነ ሕንፃና ኮንስትራክሽን ፎረም ለኢትዮጵያ ከንቲባዎች ወሳኝ የእውቀት ሽግግርና ሥርጸት መድረክ ነበር፡፡ የእውቀት ሽግግሩ በሁለት አቅጣጫ የተከናወነ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ከንቲባዎቹ ከሌሎች አገራት በተለይም በሥነ ሕንፃና በዘላቂ የከተማ ፕላን ዙሪያ ምርጥ ተሞክሮዎችን በውይይትና በሥልጠና ቀስመዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማትና የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን የፈጠራ ሥራዎች በማቅረብ የራሳቸውን ልምድ አካፍለዋል፡፡ የእውቀት ሥርጸቱም የተገኘውን ልምድ ወደየከተሞቻቸው ይዞ ከመመለስ ባለፈ ለወደፊት ቀጣይነት ያለው የትብብርና የልምድ ልውውጥ በር የሚከፍቱ የእህትማማች ከተማ ግንኙነቶችን ለመፍጠር ጥረት በማድረጋቸው ይበልጥ ተጠናክሯል፡፡

በፎረሙ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት የተካሄደባቸው ዝርዝር ርዕሰ ጉዳዮች፡-



3.1.2.6 <u>የሞስኮ ፓርክ ሲዝን ኤክስፖ 2025 ተሳትፎን በተመለከተ፤</u>

ከሚያዝያ 15-16 ቀን 2017 ዓ.ም በሩሲያ ሞስኮ የተካሄደው "የፓርክ ሲዝን ኤክስፖ" የከተማ መናፈሻዎችን፣ የመዝናኛ ሥፍራዎችንና አረንጓዴ ቦታዎችን ከመንደፍ፣ ከግንባታና ከአስተዳደር ጋር የተያያዙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስተዋወቅ ያለመ ዓለም አቀፍ መድረክ ነው። የኤክስፖው መሠረታዊ ዓላማ ዘላቂ፣ ለአካባቢ ተስማሚና ለኑሮ ምቹ የሆኑ ከተሞችን ለመገንባት የሚያግዙ አዳዲስ የፈጠራ ሀሳቦችን ማጋራትና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችንና አመራሮችን ማሰባሰብ ነው።

በዝግጅቱ ላይ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተውጣጡ ሚኒስትሮች፣ የከተማ ከንቲባዎች፣ የዋና ዋና ፓርኮች ዳይሬክተሮች፣ የፕላን ባለሙያዎች፣ የመሬት ገጽታ ንድፍ አውጪዎች፣ የአካባቢ ጥበቃ ተመራማሪዎችና በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ተሳትፈዋል። የውይይት መድረኮቹ በዘመናዊ የፓርክ ንድፍ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ አረንጓዴ መሠረተ ልማቶችን በመገንባትና

የማኅበረሰብ ተሳትፎን በማረጋገጥ ዙሪያ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ በተለይም የተለያዩ ከተሞች ስኬታማ የፓርክ ልማት ተሞክሮዎቻቸውን ያጋሩ ሲሆን በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ "የአረንጓዴ ዐሻራ" ፕሮጀክት እንደ ምርጥ ተሞክሮ ቀርቧል፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዋና ዳይሬክተር በኤክስፖው ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ለኢትዮጵያ ከተሞች በርካታ ጠቃሚ ውጤቶችን አስገኝተዋል፡፡ በዋነኝነት በአዲስ አበባ ከተማ የተተገበረውን "የአረንጓዴ ዐሻራ" ንቅናቄና እንደ እንጦጦ፣ አንድነት እና ወዳጅነት ያሉ ፓርኮችን የግንባታ ስኬት ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማጋራት የአገሪቱን ገጽታ ለመገንባት ችለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዘላቂ የፓርክ አስተዳደርና ቴክኖሎጂ ዙሪያ አዳዲስ ዕውቀቶችን ከመቅሰም ባለፈ ለኢትዮጵያ ከተሞች የፓርክ ልማት ፕሮጀክቶች የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ የትብብርና የአጋርነት ግንኙነቶችን መፍጠር ችለዋል፡፡

ዝግጅቱ የተለያዩ መድረኮችንና የኤግዚቢሽን ክፍሎችን ያካተተ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በብሪክስና በአጋር አገራት መካከል የፓርክ ልማትን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ውይይት እንዲካሄድ ያስቻለው **የብሪክስ የፓርኮች መድረክ** በዕውቀት ልውውጥና በአቅም ግንባታ ላይ ያተኮረው የፓርክ ዳይሬክተሮች የትምህርት መድረክ እና በፓርክ አስተዳደርና ልማት የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ እውቅና የሰጠው ***የሩሲያ ፓርኮች ሽልማት ሥነ ሥርዓት*** ይገኙበታል፡፡ የኤግዚቢሽኑ ክፍሎችም በአጠቃላይ የከተማ ውበትና ገጽታ ግንባታ፣ በጽዳትና ውበት፣ በደኅንነትና ቴክኖሎጂ፣ በመዝናኛ፣ በስፖርት፣ በሥነ-ምህዳር እና በቱሪዝም ዙሪያ ያተኮሩ ነበሩ፡፡



ምስል 9፡ የፓርክ ሲዝን ኤክስፖ በከፊል

በአጠቃላይ ጉባኤው የኢትዮጵያን ስኬት ለማስተዋወቅ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ወደ አገር ቤት ለማምጣትና ለወደፊት የከተሞች አረንጓዴ ልማት ፖሊሲዎች ጠቃሚ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ወሳኝ መድረክ ሆኖ አገልግሏል።

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት</u>

"የፓርክ ሲዝን ኤክስፖ 2025" ተሳትፎ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ዕውቀቶችን ለመቅሰም እና የሀገር ውስጥ ስኬታማ ተሞክሮዎችን ለማጋራት ወሳኝ መድረክ ሆኖ አገልግሏል። ይህ ተሳትፎ በዋናነት ሁለት መልክ ያለው የእውቀት ሽግግርን ያካተተ ነበር። በአንድ በኩል የሀገሪቱን "የአረንጓዴ ዐሻራ" ንቅናቄና እንደ እንጦጦ፣ አንድነትና ወዳጅነት ያሉ ፓርኮችን የግንባታ ስኬት እንደ ምርጥ ተሞክሮ በማቅረብ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ ተቀባይ ብቻ ሳትሆን ለሌሎች አገራት ልምዷን የምታካፍል መሆኗን አሳይቷል። ይህም የትብብር መድረኩን ተሳትፎ ከዕውቀት ተቀባይነት ወደ ዕውቀት አበርካችነት ያሸጋገረ ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ዳሬክተር ጀነራሉ በዘመናዊ የፓርክ ንድፍ፣ በዘላቂ አስተዳደር፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ መሠረተ ልማቶች፣ በደኅንነት ቴክኖሎጂ እና በፋይናንስ ሞዴሎች ዙሪያ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ወደ አገር ቤት ይዘው መጥተዋል። ይህ ልምድ ልውውጥ የተከናወነው እንደ "ብሪክስ የፓርኮች መድረክ" እና "የፓርክ ዳይሬክተሮች የትምህርት መድረክ" ባሉ ጥልቅ የፖሊሲ ውይይቶችና አቅም ግንባታ ላይ ባተኮሩ መድረኮች ነበር። በተጨማሪም በኤግዚቢሽን ላይ የቀረቡት የጽዳት፣ የደኅንነት፣ የመዝናኛ እና የስፖርት ቴክኖሎጂዎች፣ በዓይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ዕውቀቶችን ለማግኘት አስችለዋል። ይህም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በቀላሉ በመረዳት ወደ አገር ቤት ለማስገባትና ለመተግበር ያግዛል።

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በኤክስፖው የተገኙትን አዳዲስ የአሠራር ስልቶች፣ የቴክኖሎጂ አማራጮችና የአስተዳደር ሞዴሎች በመቀመር ለሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች በስልጠና፣ በውይይት መድረኮችና በማማከር አገልግሎት የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት። የ"ፓርክ ሲዝን ኤክስፖ 2025" ተሳትፎ ለአንድ ጊዜ ብቻ የተደረገ ጉዞ ሳይሆን ቀጣይነት ላለው የመማማርና የልማት ሂደት መሠረት የጣለ ስትራቴጂካዊ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መድረክ ነበር።


ФорумПарков.Р


23 АПРЕЛЯ
10.50–11.50
ТПП РФ
АРТ
23–24 апреля 2025
ГЛАВНОЕ ПАРКОВОЕ СОБЫТИЕ РОССИИ
ФорумПарков.РФ
ParkSeason EXPO





ምስል 10፡ የትብብር መድረኩ በፓርክ ሲዝን ኤክስፖ ተሳትፎ በከፊል (April 23-24/2025)

3.1.2.7 የብሪክስ ፕላስ (BRICS+) የከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ጠቅላላ ጉባኤ ተሳትፎን በተመለከተ፤

የደብረብርሃን ከተማ ም/ከንቲባ እና የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዳይሬክተር ጀነራል ከግንቦት 18 እስከ 22 ቀን 2017 ዓ.ም በብራዚል ማሪካ ከተማ በተካሄደው የብሪክስ ፕላስ

(BRICS+) የከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ጉባኤ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያን ወክለው ተሳትፈዋል። ጉባዔው "ያልተማከለ ትብብርና ዘላቂ የከተማ ልማትን ማጎልበት"' ('"Fostering Decentralized Cooperation and Sustainable Urban Development.") በሚል መሪ ቃል የተካሄደ ሲሆን ከብሪክስ አገራት(ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽ፣ ኢትዮጵያ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኢራን፣ ሳዑዲ ዓረቢያ እና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች) እንዲሁም ከሌሎች አገራት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከንቲባዎች፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት የስራ ኃላፊዎች፣ የከተሞች ማህበራት፣ የከተማ ፕላን ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በተገኙበት ተካሂዷል።

የጠቅላላ ጉባዔው መሠረታዊ ዓላማ የአባልና የአጋር አገራት ከተሞች የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታትና የልማት ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል ጠንካራ መድረክ መፍጠር ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ጉባዔው የማጎበሩን ሕጋዊና አስተዳደራዊ መዋቅር የሚያጸናውን መተዳደሪያ ደንብ (ቻርተር) በውይይት በማጽደቅ ወሳኝ እርምጃ ወስዷል። በተጨማሪም የማጎበሩን ቀጣይ የሁለት ዓመት (2025—2026) እንቅስቃሴዎች የሚመራውን የሥራ ዕቅድ በማጽደቅ ለወደፊቱ ግልጽ አቅጣጫ አስቀምጧል። ከእነዚህ ተቋማዊ ውሳኔዎች ባሻገር ጉባዔው በአባል ከተሞች መካከል ያለውን ትብብርና የአጋርነት ግንኙነት ለማጎልበት ቁርጠኝነቱን አሳይቷል። በዚህም መሠረት የዕውቀት፣ የቴክኖሎጂና የልምድ ልውውጥን የሚያበረታቱ ማዕቀፎችን ለማጠናከር ተወስኗል። በተለይም እንደ COP30 ባሉ ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ጉባዔዎች ላይ የከተሞችን ድምፅ አንድ ለማድረግና በአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚያስችል የጋራ የአቋም መግለጫ ለማዘጋጀት ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይህም በዓለም አቀፍ ጉዳዮችና በዘላቂ ልማት ውስጥ የአካባቢ መስተዳድሮችን ሚና ከፍ ለማድረግ ያለውን የጋራ ራዕይ ያንጸባርቃል።

በጉባዔው ማጠናቀቂያ ላይ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ከሩሲያ አቻው ጋር ባደረገው የሁለትዮሽ ውይይት አማካኝነት የደብረ ብርሃን ከተማ ከሩሲያ ፌዴሬሽን ንዥኒ ኖቭጎሮድ ከተማ ጋር ታሪካዊ የእህትማማችነት ስምምነት ተፈራርማለች። ይህ ስምምነት በንግድ፣ በኢኮኖሚና በባህል ዘርፎች የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያለመ ሲሆን በተለይ በኢንዱስትሪ፣ በከተማ ፕላን፣ በትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና በቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ ለሚደረግ ትብብር ቅድሚያ ይሰጣል። ከዚህም ባሻገር የጋራ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማበረታታት የሁለቱን ከተሞች ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠንና ነባር ኢንተርፕራይዞችን በማዘመን እንዲሁም አዳዲስ የማምረቻ ተቋማትን ለመፍጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህንን ስኬት መነሻ በማድረግ

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ሌሎች ከተሞች ከአባል አገራት ከተሞች ጋር ተመሳሳይ ጉድኝቶችን እንዲፈጥሩ እንደሚሠራ ቁርጠኝነቱን ገልጿል።

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት፤</u>

የኢትዮጵያ ልዑክ በብሪክስ ፕላስ የከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ጠቅላላ ጉባዔ መሳተፉ ለአንድ ጊዜ ብቻ የተደረገ ተሳትፎ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ከተሞች ቀጣይነት ያለው የእውቀት ሽግግርና ስርፀት ወሳኝ ምዕራፍ ነበር። "ያልተማከለ ትብብርና ዘላቂ የከተማ ልማትን ማጎልበት" በሚለው የጉባዔው መሪ ቃል እንደተንጸባረቀው የመድረኩ ዋነኛ ግብ በከተሞች መካከል የልምድ፣ የቴክኖሎጂና የአሠራር ልውውጥን ማጠናከር ነው።

የእውቀት ሽግግሩ የተከናወነው በተለያዩ መደበኛና ተቋማዊ ስልቶች ነው። ከእነዚህም መካከል በደብረ ብርሃን እና በንቸርኒ ኖቭጎሮድ ከተማ መካከል የተፈረመው የእህትማማችነት ስምምነት ተጨባጭና ተቋማዊ የሆነ የእውቀት ሽግግር ማዕቀፍ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ስምምነት በኢንዱስትሪ፣ በከተማ ፕላንና በቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ ቀጥተኛ የልምድ ልውውጥን ለማስጀመር መሠረት የጣለ ሲሆን ***የማኅበሩ ቻርተርና የሥራ ዕቅድ መጽደቁ*** ደግሞ ለቀጣይ የዕውቀት ልውውጥ መደበኛና የተደራጀ መሠረት ጥሏል።

በጉባዔው የተገኙት ዕውቀቶችና ልምዶች ሁለገብ የነበሩ ሲሆን በአንድ በኩል እንደ ቻይናና ህንድ ካሉ አገራት በዘመናዊ የከተማ አስተዳደርና ቴክኒካዊ አሠራር የተገኙ ተሞክሮዎች ተወስደዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የደብረ ብርሃንን የኢንቨስትመንት ዕድሎች ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር መፍጠርን የተመለከተ ኢኮኖሚያዊ ዕውቀት ተገኝቷል። ከዚህም ባሻገር በዩኒቨርሲቲዎች መካከል የምርምር ትብብር ለመፍጠርና ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ለማመቻቸት የሚያስችሉ ዕድሎች ተፈጥረዋል። ይህም ዕውቀት በግለሰብና በተቋም ደረጃ እንዲሰርጽ ያግዛል።

የተገኘውን ዕውቀት በአገር ውስጥ የማስረጹ ኃላፊነት የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ላይ የወደቀ ሲሆን የተገኙትን ልምዶችና የአጋርነት ግንኙነቶች በመቀመር ለሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች በውይይት መድረኮችና በሌሎች ስልቶች ያሰራጫል። በአጠቃላይ የብሪክስ ፕላስ የከተሞች ጉባዔ ተሳትፎ የኢትዮጵያ ከተሞች ከዓለም አቀፍ አጋሮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገረና ስትራቴጂካዊ የዕውቀት ካፒታልን ለመገንባት የተወሰደ ወሳኝ እርምጃ ነው። ይህም ከተሞቻችንን ከዕውቀት ተቀባይነት ወደ ዕውቀት አበርካችነት የሚያሸጋግርና ዘላቂ የከተማ ልማትን ለማረጋገጥ ጠንካራ መሠረት የጣለ ሆኖ ተገኝቷል።



ምስል11፡የደብረ ብርሃን ከተማ ከሩሲያ ፌዴሬሽን ንዥኒ ኖቭጎሮድ ከተማ ጋር የእህትማማችነት ስምምነት በመፈራረም ላይ (May/2025)

ከውጭ አገር የልምድ ልውውጥ መድረኮች ተሳትፎ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች

- **ተሳታፊዎች ከሌላ አገራት አቻዎቸው ጋር የእውቀትና የተሞክሮዎች ልውውጥ በማድረግ አቅማቸው ተገንብቷል፡፡**
- **የትብብር መድረኩ ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር ተባብሮ የመስራት ጥረቶች ተሻሽለዋል፡፡ ይህም ከተሞቻችን በአቅም ግንባታ እና ልምድ ልውውጥ ረገድ ያለባቸውን ክፍተት በመደገፍ ረገድ ተስፋ ሰጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡**
- **ትብብር መድረኩ የኢትዮጵያ ከተሞችን በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ መድረኮች የመወከል ብቃት ጨምሯል፤**
- **የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ያለው እይታና ስፍራ (visibility) ጨምሯል፡፡**
- **የሸገር ከተማ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ የብሪክስ ከተሞች ማኅበር ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸው የኢትዮጵያ ከተሞች በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ያላቸውን ተዓማኒነትና የመሪነት ሚና አሳድጓል፡፡**

- ለከተሞች የአቅም ግንባታ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ማዘመን ስራዎች ከዓለም አቀፍ አጋሮች የፕሮጀክት ድጋፍ እና ሙያዊ እገዛ (ለምሳሌ ከአሜሪካ ኤምባሲ፣UCLG World እና ከብሪክስ አገራት) ለማግኘት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፡፡

- የፖሊሲ ተፅእኖ፡- በ UN-Habitat ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ የኢትዮጵያ ተወካዮች በአለም አቀፍ የከተማ ልማት ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ፣ ልምዶቻቸውን እና ተግዳሮቶቻቸውን እንዲያካፍሉ አስችሏቸዋል፡፡

- የአገር ውስጥ የግንባታ ፕሮጀክቶችን እና የከተማ ልማትን ለማሻሻል የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብና በማስተዋወቅ ዙሪያ ክቡራን ከንቲባዎቹ ተጨማሪ እውቀትና ክህሎቶችን ማግኘት ችለዋል፡፡

- የደብረብርሃን ከተማ ከሩሲያ ፌዴሬሽን ንዥኒ ኖቭጎሮድ (Nizhny Novgorod) ከተማ ጋር በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በትምህርትና በከተማ ልማት ዘርፎች ላይ ትብብር ማድረግ የሚያስችል ይፋዊ የእህትማማችነት ጉድኝት ተፈጥሯል፡፡ በዚህም የከተማው አመራሮችና ባለሙያዎች በሌሎች አባል ከተሞች የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

- በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ እና በንዥኒ ኖቭጎሮድ እንዲሁም በሌሎች የብሪክስ ከተሞች በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በከተማ ልማት፣ በዘላቂ ልማትና በቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ የጋራ የምርምር ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችል ግንኙነት ለመፍጠር እድል ተፈጥሯል፡፡

- የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር በደብረብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክና በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ያሉትን ሰፊ ዕድሎች ለብሪክስ አባልና አጋር ሀገራት ባለሀብቶች በቀጥታ ለማስተዋወቅና ፍላጎት ያላቸውን ወገኖች ለመሳብ ወርቃማ ዕድል ፈጥሯል፡፡

- እንደ ቻይና፣ ብራዚል እና ህንድ ካሉ አገራት ከተሞች በዘመናዊ የከተማ አስተዳደር፣ በቆሻሻ አወጋገድ፣ በዘመናዊ ትራንስፖርት እና በቤቶች ልማት ዙሪያ ያላቸውን ስኬታማ ተሞክሮዎች ለመቀመርና በአገር ውስጥ ለመተግበር የሚያስችል ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡

- የብሪክስ ፕላስ (BRICS+) የከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ማኅበር ቻርተርና የሥራ ዕቅድ መጽደቁ ለቀጣይ የዕውቀት ልውውጥ መደበኛና የተደራጀ መሠረት ጥሏል፡፡
- በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የኢትዮጵያ ከተሞች መገኘትና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የአገሪቱንና የከተሞቿን ገጽታ ከመገንባት ባለፈ፣ በቀጣይ በሚኖሩ ተመሳሳይ መድረኮች ላይ ተደማጭነትና ተፈላጊነት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡
- የኢትዮጵያን ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች በማስተዋወቅ ከሩሲያና ከሌሎች አባል አገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን ቁጥር ለማሳደግ እንዲሁም የባህል ልውውጥ ፕሮግራሞችን ለመጀመር የሚያስችል መሠረት ተጥሏል፡፡
- በደብረብርሃንና አካባቢዋ የሚመረቱ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን (ለምሳሌ ከኢንዱስትሪ ፓርኩ የሚወጡ ምርቶች) በብሪክስ አገራት ሰፊ ገበያ ውስጥ ለማስተዋወቅና የንግድ ትስስር ለመፍጠር እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመውበታል፡፡
- የኢትዮጵያ ተሳትፎ በአህጉር ደረጃ የአፍሪካ ከተሞች በብሪክስ ፕላስ መድረክ ላይ ያላቸውን የጋራ አቋምና የልማት ፍላጎት ለማንጸባረቅና የጋራ ድምፃቸውን ለማሰማት የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

❖ በአጠቃላይ የውጭ አገር ልምድ ልውውጥን በተመለከተ በበጀት አመቱ ውስጥ 28 ተሳታፊዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 23 **ተሳታፊዎች(82 በመቶ)** ከሃገር ውጭ የተለያዩ ኮንፈረንሶች ላይ ተሳታፊ በመሆን የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡

3.1.3 የአቅም ግንባታ ስልጠናን በተመለከተ፤

ግብ 3፡ ለ30 የሱማሌና ሃረሪ ክልል ከተሞች እንዲሁም ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች፤ ሰራአስኪያጆችና የክልል የዘርፉ ሰራ ሃላፊዎች በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በህዝብ ተሳትፎ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ47 ተሳታፊዎች ተሰጥቷል፡፡

ከህዳር 25-26/2017 ዓ.ም በጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ከሶማሌ ክልል ከተሞችና ከክልሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ እንዲሁም ከድሬደዋና ከሐረር ከተሞች ለተውጣጡ 47 ከንቲባዎች፤

ምክትል ከንቲባዎች፤ ቢሮ ኃላፊዎች እና የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች በህዝብ ተሳትፎ እና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።

የሥልጠናው ይዘት በሁለት እርስ በእርስ ተያያዥ እና ለከተሞች ዘላቂ ልማት ወሳኝ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነበር። የመጀመሪያው የማዘጋጃቤታዊ ገቢን በማሳደግ የከተሞችን የፋይናንስ ነጻነት ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በልማት ሥራዎች ላይ የህዝብ ተሳትፎን በማጠናከር የባለቤትነት ስሜትን መፍጠርና የልማቱን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ ነው። በዚህም ተሳታፊዎቹ የገቢ ምንጮችን በማስፋፋት፣ የአሰባሰብ ሥርዓቱን በማዘመን፣ እንዲሁም የልማት ዕቅዶችን ከህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር በማጣጣም ዙሪያ ጥልቅ ዕውቀትና ተግባራዊ ክህሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም 157 በመቶ ነው።

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀትን በተመለከተ፤</u>

በከተሞች አስተዳደር ውስጥ የዜጎችን ተሳትፎ ለማሳደግና የማዘጋጃቤታዊ ገቢ አቅምን ለማጠናከር ያለመ የተቀናጀ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል። ይህ መርሃ ግብር ዕውቀትን በማስተላለፍ ብቻ ሳይወሰን የተላለፈው ዕውቀት በተሳታፊዎች ዘንድ እንዲሰርጽና ወደ ተግባር እንዲለወጥ የሚያስችሉ ስልታዊ አካሄዶችን የተከተለ ነበር።

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት የከተሞችን አንገብጋቢ ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉ ሁለት ቁልፍ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል። በዜጎች ተሳትፎ ዙሪያ ከተሳትፎ ጽንሰ-ሀሳብና አስፈላጊነት ጀምሮ የተለያዩ የተሳትፎ ዓይነቶች፣ ደረጃዎችና ውጤታማ ስልቶች እንዲሁም ይህንኑ የሚደግፉ የህግ ማዕቀፎችና የአተገባበር ሂደቶች በስፋት ተዳሰዋል። በተመሳሳይ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዘመናዊና 'ስማርት' የገቢ አሰባሰብና አስተዳደር ሥርዓቶች፣ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ምንነትና አስፈላጊነቱ፣ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ሂደት የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራዊ መፍትሔዎች ተብራርተዋል። ይህም አመራሮች ችግሮችን ከመሰረቱ ተረድተው ሁለንተናዊ መፍትሔ እንዲቀርጹ ለማስቻል ያለመ ነበር።

ይህንን ይዘት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ሁለገብ የአቀራረብ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። በመጀመሪያ በመደበኛ ሥልጠና የመሠረታዊ ንድፈ-ሀሳቦችንና የህግ ማዕቀፎችን ማስጨበጥ ተችሏል። በመቀጠል በቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የራሳቸውን ተሞክሮ እንዲያካፍሉ፣ ተግዳሮቶቻቸውን በጋራ እንዲፈትሹና በጋራ መፍትሔ እንዲፈልጉ በማድረግ ተሳታፊን ማዕከል ያደረገ አካሄድ ተግባራዊ ሆኗል። ከሁሉም በላይ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ለማገናኘት ከኔዘርላንድዋ ሬኒን ከተማ የተገኘው ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንዲሁም በአገር ውስጥ ስኬታማ ከሆኑ ከተሞች የተገኙ ልምዶች ቀርበዋል። ይህ አካሄድ የቀረቡት መፍትሔዎች

በወረቀት ላይ ብቻ የሚቀሩ ሳይሆኑ በተግባር የተፈተኑና ውጤታማ መሆናቸውን በማሳየት ለተሳታፊዎች መነሳሳትን ፈጥሯል።

የመርሃ ግብሩ ዋነኛ ትኩረት ዕውቀቱ በስልጠናው አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን ለማሳካትም ሁሉም የስልጠና ሰነዶችና የተሞክሮ ሰነዶች በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው በጋራ በተከፈተ የቴሌግራም ቡድን እንዲሁም በትብብር መድረኩ ድረገጽ ላይ ተጭነዋል። ይህ ዲጂታል ሥርዓት ተሳታፊዎቹ ከስልጠናው በኋላም መረጃዎቹን እንደ ቋሚ ማጣቀሻ እንዲጠቀሙ፣ ያገኙትን ዕውቀት ለሥራ ባልደረቦቻቸው በቀላሉ እንዲያጋሩ እና እንደ ቋሚ የእውቀት ማከማቻ እንዲያገለግል ያስችላል። በመሆኑም የእውቀት ስርፀቱ ቀጣይነት ያለውና በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የፕሮግራሙን ተጽዕኖ ከፍ አድርጎታል።

የእውቀት ሽግግርና ስርፀት የተካሄደባቸው ዝርዝር ርዕሰ ጉዳዮችም የሚከተሉትን ያካትታል፡-



የተገኙ ውጤቶች

- ❖ የስልጠናው ተሳታፊዎች አቅም ጨምሯል፡- የስልጠናው ተሳታፊዎች በህዝብ ተሳትፎና በማዘጋጃ ቤት ገቢ አስተዳደር ዙሪያ አቅማቸው በእውቀትና በክህሎት ተገንብቷል።

- በክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች እና የከተማ አመራሮች መካከል የበለጠ መቀራረብን ፈጥሯል፡፡
- በክልሉ የሚገኙ አባል ያልሆኑ ከተሞች አባል ለመሆን ፍላጎት አሳይተዋል፡፡

የተገኙ ውጤቶች

□የስልጠናው ተሳታፊዎች አቅም ጨምሯል	የአመራር መቀራረብ ፈጥራል፤	ኳዳዲስ አባላትን ለማግኘት እድል ተፈጥራል፤
• *የስልጠናው ተሳታፊዎች በህዝብ ተሳትፎና በማዘጋጀ ቤት ገቢ አስተዳደር ዙሪያ አቅማቸው በእውቀትና በክህሎት ተገንብቷል።*	□*በክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች እና የከተማ አመራሮች መካከል የበለጠ መቀራረብን ፈጥሯል።*	□በክልሉ የሚገኙ አባል ያልሆኑ ከተሞች አባል ለመሆን ፍላጎት አሳይተዋል።









ምስል 12፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች በከፊል

- ***የተዘጋጀውን ስልጠናዊ አውደጥናት አስመልክቶ በመድረኩ ላይ ስለቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮችና አቀራረብ እንዲሁም ስልጠናዊ አውደጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ምቹነትና የተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ወቅታዊነት በተመለከተ በተሳታፊዎች በተሞላ የመገምገሚያ ቅጽ መሰረት በማድረግ የተገኘው ውጤት ቀጥሎ ባለው መልኩ ተመላክቷል፡፡***

1.በመድረኩ ላይ ስለቀረበው ገለጻ





በአጠቃላይ የተካሄደውን የስልጠናዊ አውደጥናት መድረክ አስመልክቶ ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ በተደረገው መሰረት ተሳታፊዎች የቀረቡት ተሞክሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኩ በሁሉም ረገድ የተሳካና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠረና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይህም በክልሉ

አመራሮች በኩል ለቀረበው ሥልጠና ከፍተኛ ፍላጎትና ቁርጠኝነት እንደነበር ከማሳየቱም በላይ የተመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ወቅታዊና የከተሞቹን አንገብጋቢ ችግሮች የሚፈቱ መሆናቸውን በጉልህ ያረጋግጣል፡፡

ግብ 4፡ ለ30 የትግራይ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ኃላፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር፣ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በከተሞች ምግብ ዋስትና ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ40 ተሳታፊዎች ተሰጥቷል:: በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም 133 በመቶ ነው፡፡

ከጥቅምት 8-9/2017 ዓ.ም በድሬዳዋ አስተዳደር ከትግራይ ክልል ከተሞችና ከክልሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ለተውጣጡ ለ40 ከንቲባዎች፤ ምክትል ከንቲባዎች፤ የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች እና የቢሮ ኃላፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ ስርዓት፣ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በከተማ ምግብ ዋስትና" ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የሥልጠናው ይዘት የክልሉን ከተሞች ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባና በሦስት ወሳኝ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የመጀመሪያው "ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር" ሲሆን ከተሞች በገቢ ረገድ የራሳቸውን ውሳኔ እንዲወስኑና የልማት ሥራዎቻቸውን በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ የሚያስችላቸውን የገቢ ምንጭ የማስፋፋትና የማስተዳደር ስልቶችን ያካተተ ሲሆን ሁለተኛው "የማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብን የተመለከተና ከተሞች ስለ ማዘጋጃቤታዊ ገቢ ምንነትና ዓይነቶች በዝርዝር አውቀው ገቢያቸውን አሟጠው እንዲሰበስቡና በዚህም ሂደት ስለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ "የከተማ ምግብ ዋስትና" ሲሆን በከተሞች የምግብ አቅርቦት ተደራሽነትንና አጠቃቀምን በማረጋገጥ የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራዊ መፍትሔዎችን የዳሰሰ ነበር፡፡






ምስል 13፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች በከፊል

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀትን በተመለከተ</u>

የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብሩ ባልተማከለ የፋይናንስ ስርዓት፣ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና የከተማ ምግብ ዋስትና ዙሪያ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን ይህ የተቀናጀ አካሄድ የከተሞችን አስተዳደራዊ ነጻነት፣ የፋይናንስ አቅምና የማህበራዊ ደህንነትን በአንድነት ለመፍታት ያለመና ዕውቀቱ በተሳታፊዎች ዘንድ እንዲሰርጽና ወደ ተግባር እንዲለወጥ የሚያስችሉ ስልታዊ አካሄዶችን ተከትሏል፡፡

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት የከተሞችን አስተዳደራዊ፣ማህበራዊ እና የፋይናንስ ፈተናዎች የሚፈታ ሁለንተናዊ ይዘት ያለው ሲሆን ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ-ሀሳብና መርሆዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ከተሞች የፋይናንስ ውሳኔዎችን በራሳቸው እንዲወስኑ የሚያስችላቸውን መሰረታዊ ግንዛቤ አስጨብጧል፡፡ በመቀጠል ወደ ማዘጋጃቤታዊ ገቢ ጉዳይ በመግባት የገቢን አስፈላጊነት፣ የተለያዩ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ምንጮችን፣ እንዲሁም በአሰባሰብ ሂደት የሚታዩ ተግዳሮቶችንና ዘላቂ መፍትሔዎቻቸውን በዝርዝር ዳሷል፡፡ በተጨማሪም የከተማ ምግብ ዋስትና ጽንሰ-ሐሳብ ዋና ዋና ምሰሶዎች እንዲሁም የእጦቱ መንስኤዎችና ተጽእኖዎች ላይ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በመጨረሻም የከተማ አስተዳደሮች የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ሊጫወቱት ስለሚገባው ሚናም ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

ይህንን ይዘት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ያጣመረ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የዕውቀት ሽግግሩ በመደበኛ ሥልጠና የተከናወነ ሲሆን የንድፈ-ሀሳብ

ዕውቀቱን ከተጨባጭ ስኬት ጋር ለማገናኘት ሁለት ወሳኝ ተሞክሮዎች ቀርበዋል። የኔዘርላንድስ ስማርት የከተማ ግብርና ተሞክሮ እና የይርጋለም ከተማ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ያስመዘገበችው ስኬት ተሞክሮ የቀረቡ ሲሆን የመፍትሔ ሐሳቦቹ በተግባር የተፈተኑና ውጤታማ መሆናቸውን በማሳየት ለተሳታፊዎች ከፍተኛ መነሳሳትን ፈጥሯል።

የመርሃ ግብሩ ዋነኛ ትኩረት ዕውቀቱ በስልጠናው አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ነበር። ይህንን ለማሳካትም ሁሉም የስልጠና ሰነዶችና የተሞክሮ ሰነዶች በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው በጋራ በተከፈተ የቴሌግራም ቡድን ቻናል እንዲሁም በትብብር መድረኩ ድረገጽ ላይ ተጭነዋል። ይህ ዲጂታል ሥርዓት ተሳታፊዎቹ ከስልጠናው በኋላም መረጃዎቹን እንደ ቋሚ ማጣቀሻ እንዲጠቀሙና ያገኙትን ዕውቀት ለሥራ ባልደረቦቻቸው በቀላሉ እንዲያጋሩ እንዲሁም እንደ ቋሚ የእውቀት ማከማቻ ሆኖ እንዲያገለግል ያስችላል።




የተገኙ ውጤቶች

- የስልጠናው ተሳታፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር፣በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ እና በከተማ ምግብ ዋስትና" ዙሪያ ግንዛቤ ጨብጠዋል፡፡
- በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች እና የከተማ አመራሮች መካከል መቀራረብን ፈጥሯል፡፡
- ከተሞች የማዘጋጃቤታዊ ገቢን በገቢ ርዕሱ መሰረት አሟጠው ለመሰብሰብ ተነሳስተዋል፡፡
- ሥልጠናውና ተያያዥ ሰነዶች በዲጂታል መልክ ተደራሽ በመሆናቸው ቋሚ የእውቀት ማከማቻ ተፈጥሯል፡፡
- ከፍተኛ የተሳትፎ ምጣኔ መመዝገቡ፣ የተመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውና ወቅታዊ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡
- ለቀጣይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ጠቃሚ ግብዓቶች ተገኝተዋል፡፡
- የክልሉ የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ በስልጠናው የቀረቡ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ አድርጓል፤




- ***የተዘጋጀውን ስልጠናዊ አውደጥናት አስመልክቶ በመድረኩ ላይ ስለቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮችና አቀራረብ እንዲሁም ስልጠናዊ አውደጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ምቹነትና የመስተንግዶን በተመለከተ በተሳታፊዎች በተሞላ የመገምገሚያ ቅጽ መሰረት በማድረግ የተገኘው ውጤት ቀጥሎ ባለው ቻርት ተመላክቷል***

- **ከታች በተመለከተው ቻርት እንደሚታየው የተካሄደውን የስልጠናዊ አውደጥናት መድረክ አስመልክቶ ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ በተደረገው መሰረት ተሳታፊዎች የቀረቡት ተሞክሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኩ በሁሉም ረገድ የተሳካና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠረና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን አመልክተዋል፡፡**



2.አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ፤



Made with Napkin

ግብ 5፡ ለ16 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና ስራአስኪያጆች እንዲሁም የክልል የዘርፉ የስራ ሃላፊዎች በከተሞች የራስ ገቢን ማሳደግ (Self- Financing for Cities) ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል::

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለሚገኙ አባል ከተሞች ከንቲባዎች፤ ስራአስኪያጆችና የዘርፉ የክልል አመራሮች የካቲት 27 እና 28/2017 ዓ.ም በአሶሳ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓትን በመዘርጋት ወጪያቸውን በራሳቸው ገቢ መሸፈን በሚችሉበት ሁኔታ(Self- Financing for Cities)" እና በማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ ስልጠናዊ አውደጥናት ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ስልጠናው ጠለብዙ ደረጃ አስተዳደርና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ፤ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ፤ ያልተማከለ አስተዳደር መመዘኛዎች፤ ያልተማከለ አስተዳደር ዓይነቶች፤የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብና ፈተናዎችና ስኬታማ ተሞክሮዎች ዙሪያ ሰፊ ገለጻና ማብራሪያ በመስጠት ከተሞች የራሳቸውን ሃብት በማመንጨት አቅማቸውን ማጎልበት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር መስራት እንዲችሉ አስችሏቸዋል:: የከተሞችን በገቢ ራስን የመቻል አቅም ለማጎልበትና ዘላቂ የልማት ምህዳርን ለመፍጠር በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከተሞች ከመንግሥት በጀት ጥገኝነት ወጥተው የራሳቸውን የልማት ፕሮጀክቶች በራሳቸው ገቢ እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸውን ብቃት ለመገንባት ያለመ ነበር::በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም 84 በመቶ ነው::



ምስል፡14 የስልጠና ተሳታፊዎች የጋራ ፎቶ

በተጨማሪም የትብብር መድረኩ የማኔጅመንት አባላት፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊና የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት

የአሶሳ ከተማን የኮሪደር እና የተለያዩ የመሠረተ ልማት ስራዎች ጎብኝተዋል፡፡ አመራሮቹ ከኮሪደር ልማት እና አስፓልት ስራ በተጨማሪ በከተማዋ እየተከናወኑ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎችን እንዲሁም የሳይንስ ሙዚየም ግንባታን ተመልክተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዋና ዳይሬክተር አቶ አንዱዓለም ጤናው በአሶሳ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ለትብብር መድረኩ ማኔጅመንት አባላት ለተደረገው አቀባበልና ለተበረከተው ስጦታ አመስግነው የኮሪደር ልማት የከተሞችን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ ከተሞች በራሳቸው አቅም ፕሮጀክቶችን መፈጸም እንደሚችሉ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡



ምስል፡15 የአሶሳ ከተማ የኮሪደር ልማት የመስክ ጉብኝት ፎቶ


<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀትን በተመለከተ፤</u>

- **የከተሞችን በገቢ ራስን የመቻል አቅም ለመገንባት ያለመው የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር ከተሞች የገቢ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸውን ሁለንተናዊ ዕውቀት ለማስጨበጥ ያለመ ነበር፡፡ ይህ መርሃ ግብር ግንባቤው በተሳታፊዎች ዘንድ እንዲሰርጽና ወደ ተግባር እንዲለወጥ ለማስቻል በይዘት፣ በአቀራረብ ስልት እና በዘላቂነት ላይ ያተኮረ የተቀናጀ አካሄድ ተከትሏል፡፡**

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት ሰፊና ጥልቅ ሲሆን የከተሞችን የራስ ገቢ የማሳደግ ጽንሰ-ሀሳብ ከመሰረቱ ለመገንባት የሚያስችሉ ርዕሰ ጉዳዮችን አካቷል፡፡ ፕሮግራሙ በመጀመሪያ የከተሞችን አስተዳደራዊ ነጻነት በሚያጠናክረው ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ-ሀሳብ ላይ ትኩረት አድርጓል፤ በዚህም ያልተማከለ አስተዳደር ምንነት፣ ዓይነቶች፣ መመዘኛዎች እንዲሁም ጠቀሜታዎቹና ተያያዥ ፈተናዎቹ በስፋት ተዳሰዋል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ዕውቀት ከባለብዙ ደረጃ አስተዳደርና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በማያያዝ፣ የገቢ አቅምን ማሳደግ ለአገልግሎት ጥራት መሻሻል ያለውን ፋይዳ አሳይቷል፡፡ በመቀጠልም የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ምንነት፣ አስፈላጊነቱና በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችና ተግባራዊ መፍትሔዎቻቸው እንዲሁም ስማርት የገቢ አሰባሰብ ስኬታማ ተሞክሮዎች ላይ ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡

ይህንን ይዘት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ያጣመረ ሁለገብ የአቀራረብ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመደበኛ ሥልጠና የመሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳቦችንና መርሆዎችን ማስጨበጥ ተችሏል፡፡

- **የመርሃ ግብሩ ሌላኛው ትኩረት ዕውቀቱ በስልጠናው አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን ለማሳካትም ሁሉም የስልጠና ሰነዶችና የተሞክሮ ሰነዶች በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው በጋራ በተከፈተ የቴሌግራም ቡድን ቻናል እንዲሁም በትብብር መድረኩ ድረገጽ ላይ ተጭነዋል፡፡**




የተገኙ ውጤቶች


- የስልጠናው ተሳታፊዎች ግንዛቤ ጨምሯል፡- የስልጠናው ተሳታፊዎች ባልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብ እና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብና አስተዳደር ዙሪየ አቅማቸው በእውቀትና በክህሎት ተገንብቷል፡፡
- በቤኒሻንጉል ክልል እና በጋምቤላ ክልል የከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች እና የከተማ ከንቲባዎችና ማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች መካከል የበለጠ መቀራረብን ፈጥሯል፡፡
- ለቀጣይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ጠቃሚ ግብዓቶች ተገኝተዋል፡፡
- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የከተማና መሠረተ ልማት ዘርፍ ቢሮ በስልጠናው የቀረቡ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ታሪፍ ደንብን ለመከለስ ዝግጁ ሆኗል፡፡
- ከተሞች የማዘጋጃቤታዊ ገቢን በገቢ ርዕሱ መሰረት አሟጠው ለመሰብሰብ ተነሳስተዋል፡፡
- *በስልጠናዊ አውደጥናቱ ላይ የተሰያዩ ገለጻዎች በተሰያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ሲሆን የመድረኩን አፈጻጸም ለመገምገምና ለቀጣይ ማስተካከያና ትምህርት ለመውሰድ ተሳታፊዎች በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች እንዲሁም አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ*

አስተያየታቸውን እንዲሰጡ መጠይቆች የተበተኑ ሲሆን ይህንኑ የተሰበሰበ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው መልኩ ተተንትኗል።

1. በስልጠናዊ አውደጥናቱ ላይ ስለቀረቡ ገለጻዎች በተመለከተ፤




2. አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ፤



- *ከላይ በቻርቱ እንደሚታየው የተካሄደውን የስልጠናዊ አውደጥናት መድረክ አስመልክቶ ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ በተደረገው መሰረት የቀረቡት ተሞክሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኩ በሁሉም ረገድ የተሳካና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠረና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡*

የልምድ ልውውጥ እና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መጠይቅ ውጤቶች

ከተሞች ያላቸውን ውጤታማ ስራ እና ሊያስተምር የሚችል መልካም ተሞክሮ ለሌሎች ማካፈል እንዲቻል እንዲሁም የእውቀት እና የክህሎት ክፍተቶቻቸውን በስልጠና ለመሙላት ይቻል ዘንድ የከተሞችን የልምድ ልውውጥ እና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማድረግ ፍላጎታቸውን ለማካተት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ይህንኑ መሰረት በማድረግ የተገኘው ውጤት ቀጥሎ ባለው ቻርት ተመላክቷል፡፡





ከላይ እንደተመለከተው የተሳታፊዎችን የልምድ ልውውጥ እና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማድረግ ፍላጎታቸውን ለማወቅ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የፍላጎት ዳሰሳ ውጤቱ እንደሚያሳየው ከተሞች በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ፤ በካዳስተር ስርዓትና በአገልግሎት አሰጣጥና ዲጂታይዜሽን ዙሪያ የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ማድረግ እንዲሁም ስልጠና እንደሚፈልጉ አመልክተዋል።

ግብ 6፡ ለ19 የደቡብ ኢትዮጵያ፤ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ ሲዳማና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከተሞች ከንቲባዎች እና የክልል የዘርፉ የስራ ሃላፊዎች ከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓትን በመዘርጋት ወጪያቸውን በራሳቸው ገቢ መሸፈን በሚችሉበት ሁኔታ (Self- Financing for Cities) እና በማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።

ሚያዝያ 28 እና 29/2017 ዓ.ም በአርባምንጭ ከተማ አስተዳደር በከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር በመዘርጋት *ከተሞች የራስ ገቢን ማሳደግ (Self- Financing for Cities) በሚችሉበት ሁኔታና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ* ዙሪያ ስልጠናዊ አውደጥናት ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ስልጠናው ሰለብዙ ደረጃ አስተዳደርና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ፤ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ፤ያልተማከለ አስተዳደር መመዘኛዎች፤ ያልተማከለ አስተዳደር

ዓይነቶች፤የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብና ፈተናዎችና ስኬታማ ተሞክሮዎች ዙሪያ ሰፊ ገለጻና ማብራሪያ በመስጠት ከተሞች የራሳቸውን ሃብት በማመንጨት አቅማቸውን ማጎልበት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

የሥልጠናው ዋና ትኩረት "በከተሞች የራስ ገቢን ማሳደግ (Self-Financing *for Cities*)" በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲሆን ተሳታፊዎቹን በንድፈ-ሀሳብ ዕውቀትና በተግባራዊ ክህሎት ለማብቃት ያለመ ነበር፡፡ በዚህም አዳዲስ የገቢ ምንጮችን የመለየትና የማስፋፋት ስልቶች፣ የአሰባሰብ ሥርዓቱን የማዘመንና ቴክኖሎጂን የመጠቀም አማራጮች እንዲሁም የተሰበሰበውን ገቢ ግልጽና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለልማት የማዋል የገቢ አስተዳደር መርሆዎች ላይ ውይይትና የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

ይህም የፕሮግራሙን ወቅታዊነትና አስፈላጊነት ከማሳየቱም በላይ በተሳታፊ ክልሎች በኩል የከተሞችን የገቢ አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ ቁርጠኝነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በመሆኑም የሥልጠናዊ አውደጥናት ተሳታፊ አመራሮች ወደየከተሞቻቸው ሲመለሱ ተግባራዊ የለውጥ ሥራዎችን እንዲጀምሩ የሚያስችል ጠንካራ መሠረት የጣለ ስኬታማ ተግባር ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም 73 በመቶ ነው፡፡

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት፤</u>

የከተሞችን በገቢ ራስን የመቻል አቅም ለመገንባት ያለመው የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር ከተሞች የገቢ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸውን ሁለንተናዊ ዕውቀት ለማስጨበጥ ያለመ ሲሆን መርሃ ግብሩ ዕውቀት በተሳታፊዎች ዘንድ እንዲሰርጽና ወደ ተግባር እንዲለወጥ ለማስቻል በይዘት፣ በአቀራረብ ስልት እና በዘላቂነት ላይ ያተኮረ የተቀናጀ አካሄድ ተከትሏል፡፡

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት ሰፊ ሲሆን የከተሞችን የራስ ገቢ የማሳደግ ጽንሰ-ሀሳብ ከመሰረቱ ለመገንባት የሚያስችሉ ርዕሰ ጉዳዮችን አካቷል፡፡ ፕሮግራሙ በመጀመሪያ የከተሞችን አስተዳደራዊ ነጻነት በሚያጠናክረው ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ-ሀሳብ ላይ ትኩረት በማድረግ ያልተማከለ አስተዳደር ምንነት፣ ዓይነቶች፣ መመዘኛዎች እንዲሁም ጠቀሜታዎቹና ተያያዥ ፈተናዎች በስፋት ተዳሰዋል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ዕውቀት ከባለብዙ ደረጃ አስተዳደርና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በማያያዝ የገቢ አቅምን ማሳደግ ለአገልግሎት ጥራት መሻሻል ያለውን ፋይዳ አሳይቷል፡፡ በመቀጠልም ወደ ዋናው የገቢ ጉዳይ በመግባት የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ምንነት፣ አስፈላጊነቱና ሊስፋፉ የሚችሉ ተሞክሮዎች እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችና ተግባራዊ መፍትሔዎቻቸው ላይ ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡

ይህንን ይዘት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ያጣመረ ሁለገብ የአቀራረብ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። **በመደበኛ ሥልጠና** የመሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳቦችንና መርሆዎችን ማስጨበጥ የተቻለ ሲሆን **በመስክ ጉብኝት** ደግሞ ተሳታፊዎቹ በንድፈ-ሀሳብ የተማሩትን በተግባር የማየት ዕድል አግኝተዋል። ከሁሉም በላይ ንድፈ-ሀሳቡን ከተጨባጭ ስኬት ጋር ለማገናኘት የኔዘርላንድዋ ሬኒን ከተማ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ያስመዘገበችው ስኬታማ ተሞክሮ ቀርቧል። ይህ የተቀናጀ አካሄድ የቀረቡት የመፍትሔ ሐሳቦች በወረቀት ላይ ብቻ የሚቀሩ ሳይሆኑ በተግባር የተፈተኑና ውጤታማ መሆናቸውን በማሳየት ለተሳታፊዎች ከፍተኛ መነሳሳትን ፈጥሯል።

በሌላ መልኩ ዕውቀቱ በስልጠናው አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ ይህንን ለማሳካትም ሁሉም የስልጠና ሰነዶችና የተሞክሮ ሰነዶች በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው በጋራ በተከፈተ የቴሌግራም ቡድን ቻናል ላይ እንዲሁም በትብብር መድረኩ ይፋዊ ድረገጽ ላይ ተጭነዋል። ይህ ዲጂታል ሥርዓት ተሳታፊዎቹ ከስልጠናው በኋላም መረጃዎቹን እንደ ቋሚ ማጣቀሻ እንዲጠቀሙ፤ ያገኙትን ዕውቀት ለሥራ ባልደረቦቻቸው በቀላሉ እንዲያጋሩ እና እንደ ቋሚ የእውቀት ማከማቻ እንዲያገለግል ያስችላል።




ምስል፡16 የስልጠና ተሳታፊዎች የጋራ ፎቶ

የመስክ ጉብኝትን በተመለከተ፤

የአርባምንጭ ከተማ ክቡር ካንቲባ ዶ/ር መስፍን መንዛ አርባምንጭ ከተማ እየተከናወኑ ያሉ በርካታ የልማት ስራዎች እእንዲጎበኙ ያደረጉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የአርባምንጭ ኮንፈረንስ ሪዞርት ፕሮጀክት ይገኝበታል። ይህ ፕሮጀክት የ2 አመት ሲሆን አሁን ላይ አፈጻጸሙ 55 በመቶ ላይ ደርሷል። በውስጡም በርካታ የመዝናኛ ቦታዎችን፤ የስብሰባ አዳራሾችን፤ አረንጓዴ ስፍራዎችንና ሬስቶራንቶችን ያካተተ ሌሎች የግል ባለሃብቶችን ወደ አካባቢው ለመሳብ አይነተኛ

ማሳያ የሆነ ፕሮጀክት ነው ብለዋል። ሁለተኛው በስልጠናው ተሳታፊዎች የተጎበኘው የልማት ስራ የአርባምንጭ ሁለገብ ስታዲየም ግንባታ ፕሮጀክት ሲሆን በ8 ቢሊየን ብር በጀት በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት እየተሰራ ይገኛል። ስታዲየሙ በካፍ ስታንዳርድ መሰረት የሚሰራ ሲሆን በመቀመጫ ብቻ 25,000 ተመልካቾችን ማስተናገድ የሚችል በ57.5 ሄክታር ቦታ ላይ ያረፈና በአሁኑ ሰዓት አፈጻጸሙ 14 በመቶ ላይ የደረሰ ፕሮጀክት ነው። በተጨማሪም ተሳታፊዎች በከተማዋ እየተሰራ ያለውን 24 ኪሎሜትር የኮሪደር ልማት ስራ ጎብኝተዋል። ከተማዋን ለነዋሪዎች ምቹ እንድትሆን ለማድረግ የተጀማመሩ የልማት ስራዎች በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ህዝቡና ባለሀብቱ ሚናውን እየተወጣ ሲሆን የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ቅልጥፍናና የህብረተሰቡ ተሳትፎ ለሌሎች ትምህርት የሚሰጥ መሆኑ ተመለክቷል።



ምስል፡17 የአርባምጭ ከተማ የልማት ስራዎች የመስክ ጉብኝት ፎቶ

የስልጠናዊ አውደጥናቱ ውጤቶች


ከላይ እንደ ተመለከተው ከቅድመ ዝግጅት አንስቶ በቅንጅት በመስራት መድረኩ በተፈለገው አግባብ እንዲሳካ ተደርጓል። በዚህም የተነሳ

- ተሳታፊዎች ከቀረቡ ገለጻዎችና ተሞክሮዎች በርካታ ጠቃሚ ልምዶችንና ትምህርቶችን ለመውሰድ መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል።
- ተሳታፊዎች በተለይም የነባርና አዳዲስ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ርዕሶች ዙሪያ አተኩረው ለመስራት እንዲነሳሱ ከማስቻሉም በላይ ከተሞች የፋይናንስ አቅማቸውን በራሳቸው እንዲሸፍኑ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ሚና ተጫውቷል።
- በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች እና የከተማ አመራሮች መካከል መቀራረብን ፈጥሯል፤ በአሰራር መመሪያዎችና ደንቦች ላይ የጋራ መረዳት እንዲፈጠር ሆኗል።


- የቀረቡ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ ለማድረግና ስራ ላይ ለማዋል ጠቃሚ ግብዓት ተገኝቷል፤
- ከተሞች የማዘጋጃቤታዊ ገቢን በየገቢ አርዕስቱ መሰረት አሚጠው ለመሰብሰብ ተነሳስተዋል፡፡
- የትብብር መድረኩ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በተለይም በጋሞ እና ሳውላ ዞኖች የሚገኙ አባል ያልሆኑ ከተሞች በአባልነት እንዲቀላቀሉ እድል ፈጥሯል፡፡

በስልጠናዊ አውደጥናቱ ላይ የተለያዩ ገለጻዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ሲሆን የመድረኩን አፈጻጸም ለመገምገምና ለቀጣይ ማስተካከያና ትምህርት ለመውሰድ ተሳታፊዎች በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች እንዲሁም አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ መጠይቆች የተበተኑ ሲሆን ይህንኑ የተሰበሰበ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው መልኩ ተተንትኗል፡፡


የመድረክ ገለጻዎች ግምገማ




Made with Napkin



የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ፍላጎት ዳሰሳ ውጤት



2. ከሌሎች ከተሞች መማር የሚፈልጉት መልካም ተሞክሮ



Made with Napkin

3. የስልጠና ፍላጎት

የስልጠና ዓይነት	ድግግሞሽ	ደረጃ
የአገልግሎትአሰጣጥና ዲጂታይዜሽን	10	1ኛ
የማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ	7	2ኛ
ስማርት ሲቲ ትግበራ	4	3ኛ
የከተማ አመራር ስልጠና	4	3ኛ
የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት	3	4ኛ
ፕሮጀክት ማኔጅመንት	3	4ኛ
ሀጋዊ የካዳስተር ስርዓት	2	5ኛ
የዜጎች ተሳትፎ	2	5ኛ

Made with Napkin


ግብ 7፡ ለ34 የትግራይ ክልል አባል ከተሞች ሰራአስኪያጆች እና የክልል የዘርፉ የስራ ሃላፊዎች ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓትን በመዘርጋት ወጪያቸውን በራሳቸው ገቢ መሸፈን በሚችሉበት ሁኔታ (Self- Financing for Cities) እና በማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል።


ግንቦት 05 እና 06/2017 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓትን በመዘርጋት ወጪያቸው በራሳቸው ገቢ መሸፈን በሚችሉበት ሁኔታ (Self-Financing for Cities) **እና በማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ ስልጠናዊ አውደጥናት ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ስልጠናው ለለብዙ ደረጃ አስተዳደርና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ፤ያልተማከለ አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ፤ ያልተማከለ አስተዳደር መመዘኛዎች፤ ያልተማከለ አስተዳደር ዓይነቶች፤የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብና ፈተናዎችና ስኬታማ ተሞክሮዎች ዙሪያ ሰፊ ገለጻና ማብራሪያ በመስጠት ከተሞች የራሳቸውን ሃብት በማመንጨት አቅማቸውን ማጎልበት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር መስራት እንዲችሉ አስችሏቸዋል። በዚሁ መሰረት 31 ወንድና 3 ሴት በድምሩ 34(106%) ተሳታፊዎች በተገኙበት ውጤታማ ውይይት ማድረግ ተችሏል።**



ምስል፡18 የስልጠና ተሳታፊዎች የጋራ ፎቶ

- በስልጠናዊ አውደጥናቱ ላይ የተለያዩ ገለጻዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ሲሆን የመድረኩን አፈጻጸም ለመገምገምና ለቀጣይ ማስተካከያና ትምህርት ለመውሰድ ተሳታፊዎች በቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች እንዲሁም አጠቃላይ ዝግጅቱን በተመለከተ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ መጠይቆች የተበተኑ ሲሆን ይህንኑ የተሰበሰበ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው መልኩ ተተንትኗል።





ከላይ እንደተመለከተው የተካሄደውን ስልጠናዊ አውደጥናት አስመልክቶ ለተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጠይቅ አስተያየት እንዲሰጡ በተደረገው መሰረት ተሳታፊዎች የቀረቡት ተሞክሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኩ በሁሉም ረገድ የተሳካና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠረና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን አመልክተዋል። ይህም ለቀረበው ሥልጠናዊ አውደጥናት ከፍተኛ ፍላጎትና ቁርጠኝነት እንደነበር ከማሳየቱም በላይ የተመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ወቅታዊና የከተሞቹን አንገብጋቢ ችግሮች የሚፈቱ መሆናቸውን በጉልህ ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ የአቅም ግንባታ ስልጠናን በተመለከተ በ5 የስልጠና መድረኮች ከ9 ክልሎችና ከድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የመጡ156 የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ከንቲባዎች፣ የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች እና የክልል የከተማና መሠረተ ልማት ዘርፍ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል። ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአንድ የስልጠና መርሃ ግብር እና በ52 ተሳታፊዎች ብልጫ እንዳለው ያሳያል።

3.2. የሃብት ማፈላለግና ኔትወርኪንግ ሰራዎችን በተመለከተ

ግብ 8፡ በከተማ ልማት አጀንዳዎች ዙሪያ በለጋሽ ድርጅቶች በሚወጡ ማስታወቂያዎች መሰረት ሁለት የሃብት ማፈላለጊያ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል።

- **በአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት(Local Economic Development) ዙሪያ ያተኮረ አንድ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለአውሮፓ ህብረት የተላከ ሲሆን ምላሹን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።**

- **ከአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ውይይት መሰረት በስቴት ዲፓርትመንት አመቻችነት ጥቅምት14/2017 ዓ.ም ከአሜሪካ ኤምባሲ የኢኮኖሚ ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች ጋር በትብብር መድረኩ ቢሮ በቀጣይ በጋራ ለመስራት በሚያስችሉ አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል። በኤምባሲው ጥያቄ መሰረት የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተሞችን በከተማ ልማት እና በአገልግሎት አሰጣጥ ሊደግፍ የሚችል የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለኤምባሲው ቀርቧል። ምላሹንም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።**

ግብ 9፡ ከተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ አገር መሰል ተቋማትና ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነትና ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል።

- **የትብብር መድረኩ ማኔጅመንት አባላት በኔዘርላንድ ሄግ የአለም አቀፉ የሀገራት የከተሞች ማህበራት ኔትወርክ ዋና ተቋም (UCLG) የአቅም እና ተቋማዊ ግንባታ (CIB) ጉባዔ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ግብዣ በተላከላቸው መሰረት 2 አመራሮች የኢትዮጵያ ከተሞችን በመወከል ተሳትፈው የኢትዮጵያ ከተሞችን በአቅም ግንባታ ሊደግፉ የሚችሉ አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወያይተዋል። በመድረኩ ከአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ከፍተኛ ሃላፊ፣ ከስዊድን ኢምባሲ ተወካይ፣ ከኔዘርላንድ**

ከተሞች ማህበር ዳይሬክተር ጀነራል፣ ከUCLG Working Group አባላት፣ ከብሪክስ አገራት የከተሞች ማህበር እና ሌሎችም ጋር የኔትወርኪንግ ስራዎች ተሰርተዋል።

- በጀርመን አገር "connective cities dialogue event" on "Sustainability Reporting and Voluntary Local Reviews" በተሰኘ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ልምዱን እንዲያካፍል መቀመጫው ጀርመን አገር በሆነው በ"Connective Cities" በተሰኘ አለም አቀፍ ተቋም ተጋብዟል። በዚሁ መሰረት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በማዛመድ በULGE ፕሮጀክት ድጋፍ በይርጋለም ከተማ ተግባራዊ የተደረገውን እና ውጤታማ የሆነውን የይርጋለም ከተማ የገቢና ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ልምድ መነሻ በማድረግ እና ተቋሙ በላከው የትኩረት ነጥቦች **አንድ የተሞክሮ ሰነድ** ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ተልኮላቸዋል።

- ፓዝ ፋይንደር ኢትዮጵያ (*PathFinder Ethiopia*) ከተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ጋር አብሮ ለመስራት የሁለቱም ድርጅቶች ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ተገኝተውበው ሰለድርጅቶቻቸው አጠቃላይ ገጽታ ያስተዋወቁ ሲሆን በምን ላይ አተኩረው መስራት እንዳለባቸውም ውይይት አድርገዋል። በዚሁ መሰረትም በጋራ ተባብሮ ለመስራት የሚያስችላቸውን የጋራ ስምምነት ሰነድ (MoU) ተፈራርመዋል። የዚህ የጋራ ስምምነት (MOU) አላማ ተዋዋይ ወገኖች ከየራሳቸው ተልእኮ እና አላማ ጋር የሚጣጣሙ የትብብር መስኮችን ለመለየት የሚተባበሩበትን ማዕቀፍ ማቅረብ ነው።

በዚሁ መሰረትም፡-

- በፓዝፋይንደር ኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መካከል ያለው ትብብር የሁለቱም ድርጅቶች ጥንካሬዎች፣ እውቀት እና ግብአቶች የየራሳቸውን የልማት ተነሳሽነት ውጤታማነት እና ተፅእኖ ለማሳደግ ያለመ ሲሆን የዚህ አጋርነት አስኳል ሁለቱ ወገኖች የትብብር ጥረታቸውን ተደራሽነትና መጠን ለማስፋት እንዲችሉ አዳዲስ የገንዘብ ዕድሎችን በጋራ በመለየትና በመከታተል፣ በጋራ ስምምነት ላይ የደረሱ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትና በመተግበር የሚያገለግሉትን ማህበረሰቦች ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

- *በመጨረሻም የዚህ አጋርነት ዋና አላማ የፓዝፋይንደር ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ተቋማዊ እና የጋራ አቅምን በማጠናከርና አቅማቸውን በመጠቀም ለታለመላቸው ማህበረሰቦች ሰፊ ልማት እና ፈጠራ መፍትሄዎች የበለጠ*

ውጤታማ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው። በፓዝፋይንደር ኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መካከል ያለው ትብብር ፕሮግራማዊ አላማ የከተሞችን ችግርን የመቋቋም አቅም ማሳደግ እና በኢትዮጵያ ከተሞች የጤና ሁኔታዎችን ማሻሻል ነው። የጤና ሰርአቶችን እና የሰነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በማጠናከር ላይ በማተኮር ሽርክናው የአየር ንብረት ለውጥን ተፅእኖ ለመቀነስ እና የህብረተሰቡን ደህንነት ለማሳደግ ይፈልጋል።

- **ከተሞችን ወደ ዘመናዊ፣ ቴክኖሎጂ-መር እና ህይወት-ተኮር ማዕከላት ለመቀየር በተያዘው አገራዊ ራዕይ መሠረት የትብብር መድረኩ ከአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ አጋሮች ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር የሚያደርገውን ጥረት በማጠናከር በአፍሪካ የልማትና የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንት ላይ ትኩረቱን ያደረገውን ሪፎከስ አፍሪካ ግሩፕ (Refocus Africa Group) ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ (Letter of Intent) በማዘጋጀት ወሳኝ እርምጃ ወስዷል፡፡ ይህ ሰነድ የትብብር ጥያቄ ከማቅረብ ባለፈ ሁለቱ ተቋማት በጋራ ሊያሳኳቸው የሚችሏቸውን ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች በግልጽ የሚያሳይ ስትራቴጂካዊ ሰነድ ነው፡፡**

- **የፍላጎት መግለጫው የኢትዮጵያ ከተሞች በአሁኑ ወቅት ከሚያጋጥሟቸው አንገብጋቢ ችግሮች በመነሳት የተቀረጸ ሲሆን ዘመናዊና ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማምጣት ያለመ ሲሆን ሰነዱ በተለይም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መሠረተ ልማት ዝርጋታ (ለዘላቂ ትራንስፖርትና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም)፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትን በቴክኖሎጂ ማዘመን፣ የድሮን ቴክኖሎጂን ለከተማ አስተዳደርና ለይዞታ ማረጋገጫ ሥራዎች መጠቀም፣ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶችን በብዛትና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችሉ አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ እንዲሁም የከተሞችን የገቢ ማሳደጊያ ስልቶችን በማዘመን በፋይናንስ ራስን መቻልን ማረጋገጥ ያሉትን ቁልፍ ዘርፎች የትብብር መስኮች አድርጎ ለይቷል፡፡**

- **ለቀረበው የትብብር ጥያቄ ከሪፎከስ አፍሪካ ግሩፕ የተገኘው ምላሽ እጅግ አዎንታዊ ከመሆኑም በላይ ለትብብሩ መሳካት ያለውን ጽኑ መሠረት የሚያሳይ ነበር፡፡ ድርጅቱ ከመድረኩ ጋር በቅርበት ለመሥራት ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት በደብዳቤ**

ከማረጋገጡም በላይ የመድረኩን የዘላቂ ከተማ ልማትና የቴክኖሎጂ ፈጠራን የማሳደግ ራዕይ እንደሚጋራና በሙሉ አቅሙ እንደሚደግፍ ገልጿል።


- ይህ የጋራ መግባባት ግንኙነቱን ከፍላጎት መግለጫ ወደ ተጨባጭ የትግበራ ምዕራፍ የሚያሸጋግር በመሆኑ በቀጣይ የትብብሩን ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር፣ የኃላፊነት ክፍፍልን፣ የጊዜ ሰሌዳንና የፋይናንስ አሠራርን የሚተነትን የጋራ የፕሮጀክት ሰነድ (Detailed Proposal) ለማዘጋጀትና ተከታታይ ውይይቶችን በማድረግ የትብብር ማዕቀፉን መሬት ላይ ለማውረድ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

ግብ 10፡ በአባል ከተሞችና ከተማ ልማት ቢሮዎች በመገኘት ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤ተሞክሮ መቀመር እና የማስፋፋት ሰራ ተከናውኗል።

- ዕውቀትን ተቋማዊ ለማድረግና ከተሞች ከተሻሉ ተሞክሮዎች እንዲማሩ ለማስቻል በ2016 ዓ.ም በተከናወኑ ዓለም አቀፍና አገር በቀል የልማት ሥራዎች ላይ የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችንና ተሞክሮዎችን በሰነድ የማስፈርና የማሰራጨት ሥራ በስፋት ተከናውኗል። በዚህም መሠረት በአጠቃላይ አስራ አራት (14) የተሞክሮ ሰነዶች በውስጥ አቅምና በከተሞች በራሳቸው ባለሙያዎች ተቀምረዋል። ከእነዚህ ውስጥ ስድስቱ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች የተገኙ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስምንቱ ደግሞ ከአገር ውስጥ ስኬታማ ከተሞች የተወሰዱ ናቸው። ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር እጅግ ከፍተኛ መሻሻል ያለው ሲሆን የተቋሙ የዕውቀት አያያዝ፣ የመተንተንና የማሰራጭት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን በግልጽ ያመለክታል።
- **ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች** መካከል በኔዘርላንድስ በተካሄደው የትምህርታዊ ጉዞ (Study Tour) የተገኙ ዕውቀቶች በአግባቡ ተቀምረዋል። እነዚህም የስማርት ከተማ እንቅስቃሴ ሥርዓት(smart urban mobility)፣ የስማርት ከተማ ግብርና፣ የኔዘርላንድስ ማዘጋጃ ቤቶች ማኅበር(VNG) የአደረጃጀትና የአሠራር፣ በሄግ ከተማ የተተገበረው የላክ ክ/ከተማ የከተማ ፕላንና የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም የሬኒን ከተማ የማዘጋጃ ቤት ገቢ አሰባሰብ ያሉ ዘመናዊ የከተማ አስተዳደር ጽንሰ-ሐሳቦችን ያካተቱ ናቸው። እነዚህ ሰነዶች የኢትዮጵያ ከተሞች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአገልግሎት አሰጣጥና የከተማ አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጉ የሚያግዙ ናቸው። በተጨማሪም የብራዚሏ ማሪካ ከተማ አካታች የከተማ ልማት ተሞክሮ በሰነድነት ተቀምሯል።

- **ከአገር ውስጥ ደግሞ ስምንት የአገር ውስጥ ስኬታማ ተሞክሮዎች የተቀመሩና ለህትመት ዝግጁ የተደረጉ ሲሆን እነዚህም የሀረር ጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ መልካም ተሞክሮ፤ የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት፣ የጅማ ኮሪደር ልማት፤የቢሾፍቱ እና የባህርዳር ከተሞች የኮሪደር ልማት፣ የአዳማ ከተማ የካዳስተርና የስማርት ሲቲ ፕሮጀክት አፈጻጸም እንዲሁም የቡታጅራ ከተማ ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ልምዶችን ያካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰነዶች ሌሎች ከተሞች ከተጨባጭ የአገር ውስጥ ስኬቶች እንዲማሩ፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እንዲረዱና ስኬታማ የአሠራር ሥርዓቶችን በቀላሉ እንዲተገብሩ ወሳኝ ግብዓት ሆነው ያገለግላሉ፡፡**
- **ከዚህ በተጨማሪም የጎንደር አጼ ፋሲል ግንብ አለም አቀፍ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ፣ የሐዋሳ ኮሪደር ልማት፣ የደሴ ካዳስተርና ስማርት ሲቲ፣ የደብረብርሃን ኢቨስትመንት አፈጻጸም እና የሆሳዕና አረንጓዴ ልማት ተሞክሮ ሰነዶች በከተሞቹ ተቀምረው ለትብብር መድረኩ እንዲላኩ በደብዳቤ ተጠይቆ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡**
- **የተሞክሮ ሰነዶችን ማዘጋጀት ብቻውን ግብ ባለመሆኑ የተመረጡና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ሰነዶች ታትመው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ በተለይም የስማርት ከተማ እንቅስቃሴ ሥርዓት፣ የስማርት ከተማ ግብርና፣ የኔዘርላንድስ ማዘጋጃ ቤቶች ማኅበር የአሰራርና አደረጃጀት ተሞክሮ (ህዳር 2017 ዓ.ም፣ 1ኛ ዕትም) እና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብና አስተዳደር (ህዳር 2017 ዓ.ም፣ 2ኛ ዕትም) ሰነዶች ታትመው ለከተሞች በህትመት (hard copy) ተሰራጭተዋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ከንቲባዎችና ስራአስኪያጆች በቀላሉ እንዲያገኟቸው የተቀመሩ ተሞክሮዎች በዲጂታል መልክ (soft copy) በትብብር መድረኩ የቴሌግራም ገጽና ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ተጭነዋል፡፡ ይህ የሥርጸት ሥራ ዕውቀቱ በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ ታጥሮ እንዳይቀር ከማድረጉም በላይ ዘላቂና ሰፊ ተደራሽነት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘርፍ የተቀመጠው ግብ ሙሉ በሙሉ የተሳካ በመሆኑ አፈጻጸሙ መቶ በመቶ ነው፡፡**

በ2017 ዓ.ም የተቀመሩ የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶች





ምስል 19: የተቀመሩ የተሞክሮ ሰነዶች የገጽ ሽፋን በከፊል

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት፤</u>

የእውቀት ሽግግርና ሥርጸት የተበታተኑ ልምዶችንና ግላዊ ክህሎቶችን ወደ ዘላቂና ተቋማዊ ሀብትነት የመቀየር ወሳኝ ሂደት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በ2017 ዓ.ም የተከናወነው የተሞክሮ ሰነድ ቅመራና ሥርጸት ሥራ ይህንን ጽንሰ-ሐሳብ በተግባር ያሳየ ስኬታማ ምዕራፍ ነበር፡፡

ሂደቱ በዋናነት በሁለት ተያያዥ ደረጃዎች የተከናወነ ሲሆን የመጀመሪያው የእውቀት ሽግግር (*Knowledge Transfer*) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእውቀት ሥርጸት (*Knowledge Dissemination*) ነው።

የመጀመሪያው ደረጃ የእውቀት ሽግግር ከተለያዩ ምንጮች ጠቃሚ መረጃዎችንና ልምዶችን የመሰብሰብና የመቀመር ሥራን ያካትታል። ይህ ሂደት በሁለት አቅጣጫ የተከናወነ ነበር። በአንድ በኩል እንደ ኔዘርላንድስ ካለ በከተማ አስተዳደር ከበለጸጉ አገራት የስማርት ከተማ እንቅስቃሴ፣ የስማርት ግብርና እና የተቋማት አደረጃጀት (VNG) ያሉ ዘመናዊና ቴክኖሎጂ-ተኮር ዕውቀቶችና የአገር ውስጥ ተጨባጭና ስኬታማ ተሞክሮዎች ተቀምረዋል። ይህ አካሄድ ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከአገር ውስጥ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣመር ለከተሞቻችን የሚሆኑ የተፈተኑና ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማቅረብ አስችሏል።

ሁለተኛው ደረጃ የእውቀት ሥርጸት ነው። ዕውቀት ከተሰበሰበና ከተቀመረ በኋላ በመደርደሪያ ላይ ከቀረ ዋጋ የለውም። በመሆኑም የተቀመሩት ሰነዶች ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉና ወደ ተግባር እንዲለወጡ ለማድረግ ሰፊ የሥርጸት ሥራ ተከናውኗል። ይህንን ለማሳካትም የተመረጡ ሰነዶች በህትመት (hard copy) ተዘጋጅተው ለሁሉም ከተሞች እንዲደርሱ ተደርጓል። ይህ ዘዴ መረጃው በቀጥታ ወደ አመራሩ እጅ እንዲደርስና ለውይይትና ውሳኔ አሰጣጥ ግብዓት እንዲሆን ያግዛል። ከዚህም ባሻገር ተመሳሳይ የተሞክሮ ሰነዶች በዲጂታል መልክ (soft copy) በትብብር መድረኩ የቴሌግራም ገጽና ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ በመጫን ዕውቀቱ ለሁሉም ባለድርሻ አካላትና ዜጎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል።

ይህ ሂደት የተሞክሮ ሰነዶችን ከማዘጋጀት ባለፈ ዕውቀትን ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያስችል የተሟላ ውደት ፈጥሯል። የሰነዶቹ መዘጋጀት የእውቀት ሽግግሩን ሲያመለክት ህትመታቸውና በዲጂታል ፕላትፎርሞች መሰራጨታቸው ደግሞ የእውቀት ሥርጸቱን ያረጋግጣል። ይህም የኢትዮጵያ ከተሞች ከመማር ባለፈ የተማሩትን እንዲተገብሩ የሚያስችል ጠንካራ መሠረት የጣለ ሲሆን ለዚህ ግብ የተቀመጠው አፈጻጸም መቶ በመቶ መሆኑ የተልዕኮውን ሙሉ ስኬት ያረጋግጣል።

የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች

- አስራ አራት (14) አዲስ የተሞክሮ ሰነዶች ተዘጋጅተው ለእውቀት ሽግግርና ስርጸት ዝግጁ ከመሆናቸውም በላይ ስድስት (6) ዓለም አቀፍ እና ስምንት (8) የአገር ውስጥ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያካተተ የእውቀት ክምችት ተፈጥሯል።
- አራት (4) ስትራቴጂካዊ የተሞክሮ ሰነዶች በህትመት መልኩ ተዘጋጅተው ለከተሞች ተሰራጭቷል፡፡
- አምስት የተሞክሮ ሰነዶች በቴሌግራም እና በድረ-ገጽ አማካኝነት በዲጂታል መልኩ ለሁሉም ተደራሽ ተደርጓል፡፡
- የተቋሙ የዕውቀት አያያዝና የመተንተን አቅም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በተጨባጭ ያደገ መሆኑ፤
- ዕውቀት በጥቂቶች እጅ ብቻ እንዳይቀር በህትመትና በዲጂታል ፕላትፎርሞች የተደገፈ የተቀናጀና ዘላቂ የሥርጸት መዋቅር ተፈጥሯል።
- የኢትዮጵያ ከተሞች ከስኬታማ የአገር ውስጥ ከተሞች ተሞክሮዎችን እንዲማሩ የሚያስችል ስርዓት ተፈጥሯል።
- ዕውቀትን ወደ ተቋማዊና ዘላቂ ሀብትነት ለመቀየር የሚያስችል ጠንካራ መሠረት ተጥሏል፡፡
- የአባል ከተሞች ከንቲባዎች የተቀመሩ ተሞክሮችን በማንበብ አዳዲስ እውቀቶችን እና ተሞክሮዎችን እንደየከተሞቻቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ላይ መሆናቸው ይገኝበታል፡፡

ግብ11፡ በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች የዘርፉን ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን (key performance indicators) መሰረት በማድረግ የመነሻ ሁኔታ መረጃዎችን (baseline data) በማሰባሰብ 1 ጥናታዊ ሰነድ ተዘጋጅቷል፤ ሰነዱን መነሻ በማድረግ የከተሞች ዳሽቦርድ (Ethiopian Cities Dashboard) ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ይፋ ተደርጓል፡፡

የዚህ ግብ ዓላማ የከተሞችን የአገልግሎት አሰጣጥና የአስተዳደር ብቃት በተጨባጭ መረጃ ለመለካት የሚያስችል የመነሻ ሰነድና ዳሽቦርድ ማዘጋጀት ነበር፡፡ ይህ ስኬት የከተሞች


አስተዳደር ከግምት አሰራር ወደ መረጃ-ተኮር ውሳኔ አሰጣጥ እንዲሸጋገር የሚያስችል ወሳኝ ምዕራፍ ከመክፈቱም በላይ በኢትዮጵያ የከተሞች አስተዳደር ውስጥ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአመራር ባህልን ለማስፈንና የአፈጻጸም ግልጽነትን ለማረጋገጥ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

የጥናታዊ ሰነዱ ዓላማ በተለዩ ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች (key performance indicators) **መነሻ በማድረግ ከተመረጡ የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተንተን ሰነድ በመሰነድና በማሰራጨት ፖሊሲ አውጪዎች፣ ተመራማሪዎች እና ከተሞች በግብዓትነት እንዲጠቀሙበት ለማስቻል ነው።**

የጥናት ሰነዱ የመጀመሪያ ክፍል የነበረው በተመረጡ ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች ላይ ተመስርቶ የከተሞችን ወቅታዊ ሁኔታ የሚተነትን አንድ ወጥ የጥናት ሰነድ የማዘጋጀት ተግባር በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። ይህ የመነሻ ጥናት ሰነድ (Baseline Study Document) **በ20 የናሙና ከተሞች የተሰበሰበውን ሰፊ መረጃ በማቀናጀትና በመተንተን የከተሞችን ጥንካሬና ድክመት በግልጽ የሚያሳይ የመጀመሪያው ዓይነት ሀገራዊ ሰነድ ሆኖ ተዘጋጅቷል። መረጃ የተሰበሰበባቸው ከተሞችም አዲስ አበባ፣ አርባምንጭ፣ አዳማ፣ አሶሳ፣ አክሱም፣ ባህር ዳር፣ ቢሾፍቱ፣ ቦንጋ፣ ደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ጋምቤላ፣ ጎንደር፣ ሐረር፣ ሐዋሳ፣ ሆሳዕና፣ ጅግጅጋ፣ ሰመራ፣ ሽገር፣ ወልቂጤ እና ወላይታ ሶዶ ናቸው።**

በዚህ የጥናት ሰነድ ላይ በመመስረት የግቡ ሁለተኛ ክፍል የሆነው ዘመናዊና ተጠቃሚን የሚያሳትፍ *"የኢትዮጵያ ከተሞች ዳሽቦርድ"* ተዘጋጅቶ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ይፋ ተደርጓል። ይህ ዳሽቦርድ ውስብስብና ሰፊ የነበረውን መረጃ ወደ ቀላል፣ ምስላዊና በቀላሉ ሊነጻጸር ወደሚችል ዲጂታል መድረክ በመቀየር የመረጃ ተደራሽነትን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለውጧል። ዳሽቦርዱ ይፋ መሆኑ የከተማ አስተዳደሮች ለሚያከናውኑት ተግባር ተጠያቂ እንዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ ዜጎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የከተሞቻቸውን አፈጻጸም በቀላሉ እንዲከታተሉ በማድረግ ግልጽነት የሰፈነበት የአስተዳደር ሥርዓት ለመገንባት የተጣለውን መሠረት ያጠናክራል።

ሁለቱንም ቁልፍ ውጤቶች ማለትም የጥናት ሰነዱንና ዳሽቦርዱን በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና ጥራት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህ ስኬት የከተሞችን የወደፊት የእድገት ጉዞ በመረጃ የሚመራ ለማድረግ የተለኮሰ ችቦ ነው። በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም ደረጃ መቶ በመቶ ነው።



የተገኘውን ውጤትና የከተሞቹን ዝርዝር መረጃ በሚከተለው ዳሽቦርድ መመልከት ይቻላል፦


https://app.powerbi.com/view?r=eyJrIjoiY2M5MzkyOWYtYzg0OC00ZmU1LWFiNDQtOTMxNDI3NzdiNjJlIiwidCI6ImRlMzk4MmNiLTNiMjAtNDhiZC04MzY2LTE1ZGY4NjEzZTZjMiIsImMiOjl9&pageName=df6272c9799d73861473

የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች

- **አንድ የተሟላና ወጥ የሆነ የከተሞች አፈጻጸም መነሻ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡**
- **ዘመናዊና ተጠቃሚን የሚያሳትፍ "የኢትዮጵያ ከተሞች ዳሽቦርድ" ተሰርቶ ለህዝብ ይፋ ሆኗል፡፡**
- **በ20 የናሙና ከተሞች ላይ የተመሰረተ አስተማማኝ የመረጃ ቋት** (database) **ተፈጥሯል፡፡**
- **በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ባህል እንዲፈጠር የሚያስችል መሠረት ተጥሏል፡፡**

- ለፖሊሲ አውጪዎችና ለከተማ አመራሮች የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ወሳኝ ግብዓት ሆኖ ቀርቧል፡፡
- ዜጎችና ባለድርሻ አካላት የከተሞቻቸውን አፈጻጸም በቀላሉ እንዲከታተሉና እንዲሳተፉ ግልጽነት እንዲፈጠር አስችሏል፡፡
- ከተሞች አፈጻጸማቸውን ከሌሎች ጋር እንዲያነጻጽሩ (benchmarking) የሚያስችል መሣሪያ ተፈጥሯል፡፡
- በመረጃ አሰባሰብ እና ትንተና ዙሪያ ስራውን ባከናወኑት በአገር በቀል ድርጅት እና በአለም አቀፍ ድርጅት መካከል ትብብርን እና የእውቀት ሽግግርን ፈጥሯል፡፡

የሶሺዮ ኢኮኖሚ ጥናትና ዳሽቦርድ ጥናት ውጤቶች





ምስል፡20 የተዘጋጀው ዳሽቦድ ገጽታ በከፊል

ግብ 12፡ የትብብር መድረኩ ተቋማዊ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት ተከናውኗል፡፡

ትብብር መድረኩ አማካሪ በመቅጠር እና የጋራ ውይይት በማድረግ በ7/08/2024 ከዋሊያ አማካሪ ድርጅት ጋር ውል በመግባት ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የትብብር መድረኩን ውጤታማ አስተዳደርን፣ ትብብርን እና ለአባል ከተሞች አገልግሎት አሰጣጥን የሚያበረታታ አዲስ ድርጅታዊ መዋቅር መቅረጽ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የትብብር መድረኩ አዲስ የመዋቅር ጥናት ተጠንቶ ተጠናቋል፡፡ መዋቅሩ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ማሳደግ፣ ስራዎችን ማቀላጠፍ እና የትብብር መድረኩን ስትራቴጂካዊ አላማዎች ለማሳካት የሚያስችል ነው ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የግቡ አፈጻጸም መቶ በመቶ ነው፡፡

3.3. የኮሙኒኬሽን ስራዎች በተመለከተ

ግብ 13፡ የ ULGE ፕሮጀክት 100 ቡክሌትና የተሞክሮ ሰነዶች ለማሳተም ታቅዶ 260 ኮፒ የተሞክሮ ሰነዶች ታትመዋል፡፡

በULGE ፕሮጀክት ድጋፍ ዕውቀትን ወደ ተግባራዊና ዘላቂ ለውጥ ለመቀየር የሚያስችል የተሞክሮ ሰነዶች ህትመትና ሥርጸት ሥራ በስኬት ተከናውኗል፡፡

በዚሁ መሰረት በአመቱ ውስጥ አምስት ሰነዶች በ260 ኮፒ ታትመው ለአባል ከተሞች እየተሰራጨ ይገኛል፡፡ እነዚህም የማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብና አስተዳደር ተሞክሮ፣ የኔዘርላንድ ማዘጋጃቤቶች ማህበር የአደረጃጀትና የአሰራር፣ የዘላግ ከተማ ስማርት የከተማ ግብርና፣ የዘላግ ከተማ ስማርት የከተማ እንቅስቃሴ (smart urban mobility) የተሞክሮ ሰነዶች እንዲሁም የትብብር መድረኩ የኮሚኒኬሽንና አድቮካሲ ስትራቴጂ ሰነድ እንዲታተሙ ተደርጓል፡፡ ሰነዶቹም ለከተሞች ከሃርድ ኮፒ በተጨማሪ ዕውቀቱ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ እንዲደርስ ለማድረግ ሁሉም ሰነዶች በዲጂታል መልክ (soft copy) ተዘጋጅተው በትብብር መድረኩ ድረ-ገጽ ላይ በመጫን እንደ ቋሚ የእውቀት ማከማቻ እንዲያገለግሉ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር በትብብር መድረኩ የቡድን ቴሌግራም እና ዋትስአፕ ገጾች ላይ እንዲሰራጩ መደረጉ መረጃው በፍጥነትና በቀላሉ ወደ ብዙ ተጠቃሚዎች እንዲደርስ አስችሎታል፡፡

የሰነዶቹ ይዘት፣ የሥርጸት ስልቱ ዘርፈ ብዙ መሆንና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም የፕሮጀክቱን ተጽዕኖ ከፍ በማድረግ ዕውቀት ወደ ተግባር እንዲለወጥ ጠንካራ ድልድይ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም መቶ በመቶ ነው፡፡











ምስል 21፡ የታተሙ የተሞክሮ ሰነዶች

ግብ 14፡ የአባል ከተሞች የእርስ በርስ የእህትማማችነት ቁርኝትን ከፍ ለማድረግና ከመሰል የውጪ ከተሞች ጋር ያላቸውን ትስስር ለማሳደግ 5 ከተሞችን በአገር ውስጥና 2 ከተሞችን ደግሞ ከውጪ አገራት ከተሞች ጋር የማስተሳሰር ስራ ለማከናወን ታቅዶ ሁለት ከተሞችን ከውጪ አገር ከተሞች ጋር ለማስተሳሰር በመቻሉ 28.5 በመቶ ተከናውኗል።

- **ባሳለፍነው በጀት ዓመት የአባል ከተሞች የእርስ በርስ የእህትማማችነት ቁርኝትን ከፍ ለማድረግና ከመሰል የውጪ ከተሞች ጋር ያላቸውን ትስስር ለማሳደግ 5 ከተሞችን በአገር ውስጥና 2 ከተሞችን ደግሞ ከውጪ አገራት ጋር ለማስተሳሰር የታቀደ ሲሆን በዚሁ መሰረት የጎንደር ከተማን ደቡብ አፍሪካ ከሚገኙ ከተሞች ጋር ለማስተሳሰር ይቻል ዘንድ ከደቡብ አፍሪካ የአካባቢ መንግስታት ማህበር ጋር ስምምነት እንዲፈራረሙ ተደርጓል።**





ምስል፡22 **የጎንደር ከተማ አስተዳደር ከደቡብ አፍሪካ ከተሞች ማህበር ተወካዮች ጋር ስምምነት ሲያደርጉ**

በተመሳሳይ ደብረ ብርሃን ከተማ በሩሲያ ፌዴሬሽን ውስጥ ከምትገኘው ንሾኒ ኖቭጎሮድ (Nizhny Novgorod) **ከተማ ጋር የእህትማማችነት ጉድኝት ለመመስረት የሚያስችላትን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች።**

በመሆኑም ባሳለፍነው በጀት ዓመት 7 ከተሞችን በአገር ውስጥና ከውጪ አገር ጋር የእህትማማችነት ግንኙነት ለመፍጠር ታስቦ 2 ከተሞችን በማስተሳሰር የዕቅዱን 28 በመቶ ለማከናወን ተችሏል።



ምስል፡23 **የደብረብርሃን ከተማ ም/ከንቲባ ከሩሲያዋ ንዥኒ ኖቭጎሮድ** (Nizhny Novgorod) **ከተማ ከንቲባ ጋር ስምምነት ሲያደርጉ**

ግብ 15፡ የትብብር መድረኩን አገልግልቶችና አጠቃላይ ገጽታ የሚያስተዋውቅ 11 ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄትና 48 ሳምንታዊ የከተሞች ፕሮፋይል የሚያስተዋውቅ ዲጂታል ፖስተር ለማዘጋጀት ታቅዶ ተከናውኗል፡፡

- **የሳምንቱ ከተማ ወይም 'ሲቲ ኦፍ ዘ ዊክ' በሚባል ሳምንታዊ ፖስተርና 'የከተሞች ድምጽ' በሚል ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄት በፖስተር መልክ ዲዛይን በማድረግና በተለያዩ የትብብር መድረኩ ማህበራዊ ሚዲያዎችና ዌብሳይትን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡**

- **በዚሁ መሰረት በበጀት አመቱ ሲቲ ኦፍ ዘ ዊክ በተባለው የሳምንቱ ከተማ ፖስተር ላይ 48 ከተሞችን ለማስተዋወቅ ታቅዶ የ48 ከተሞችን (ይርጋጨፌ፣ ቢሾፍቱ፣ አምቦ፣ ይርጋለም፣ ደብረ ማርቆስ፣ በደሌ፣ አዴት፣ ቻግኒ፣ ሚዛን አማን፣ ፍኖተ ሰላም፣ ሻሸመኔ፣**

አቢይ አዲ፣ ሳውላ፣ ሻሁራ፣ አይከል፣ ደጀን፣ መሆኒ፣ ጊዶሌ፣ ሆለታ፣ ሾኔ፣ አሶሳ፣ ፓዌ፣ አረካና ጅማ፤ደገሃቡር፣ ወልዲያ፣ ጎንደር፣ ሃላባ ቁሊቶ፣ ሸርቆሌ፣ ባህር ዳር፣ ሃውዜን፣ ነቀምቴ፣ ካማሺ፣ቦዲቲ፣ እዳጋ ሃሙስ፤ ገንዳ ውሃ፤ መቱ፣ ሰመራ ሎጊያ፣ አክሱም፣ ቡለን፣ አርባ ምንጭ፣ መቀሌ፣ ሊሙ ገነት፣ ደብረብርሃን፣ ወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ሐይቅና ጎደ) ከተሞች አጠቃላይ ገጽታዎች የሚዳስስ መረጃዎችን በማሰባሰብና ዲዛይን በመስራት የእቅዱን መቶ በመቶ ማከናወን ተችሏል። ይህም ባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 42(87 በመቶ) ከነበረበት ጋር ሲነጻጸር መሻሻል ታይቷል።


- በተመሳሳይ በአመቱ ውስጥ የትብብር መድረኩ በየወሩ የሚያከናወናቸውን አበይት ተግባራትንና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በተመለከተ 'የከተሞች ድምጽ' በሚል 12 ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄቶችን በማዘጋጀት ትብብር መድረኩን ለባለድርሻ አካላት ለማስተዋወቅ ባቀደው መሰረት 11 ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄቶችን ማዘጋጀት በመቻሉ የዕቅዱ 92 በመቶ ተከናውኗል። ይህም ባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 9(75 በመቶ) አፈጻጸም ከነበረበት ጋር ሲነጻጸር ትልቅ መሻሻል ታይቷል።





ግብ 16፡ የትብብር መድረኩ የአባል ከተሞች ቁጥር 96 ከነበረበት ወደ 111 እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የትብብር መድረኩ 30 አዳዲስ አባል ከተሞችን አባል ለማድረግ ታቅዶ 15 ከተሞች ከአምስት ክልልሎች ትብብር መድረኩን እንዲቀላቀሉ በማድረግ የዕቅዱን 50 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው አፈጻጸም በ2 ከተሞች ቅናሽ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡




ግብ 17፡ በበጀት አመቱ የትብብር መድረኩ ባዘጋጃቸው 5 ስልጠናዎችና 2 የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶች ላይ ጋዜጠኞችን በመጋበዝ የዘገባ ስራዎች በማከናወን የተቋሙ ገጽታና እይታ እንዲጨምር ተደርጓል። የግቡ አፈጻጸም መቶ በመቶ ተከናውኗል።

- የትብብር መድረኩ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ ማሻሻያ፣ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደርና በከተማ ምግብ ዋስትና ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ያተኮረ ስልጠና ***ለትግራይ ክተሞች*** ከንቲባዎችና የከተማ ልማት ዘርፍ አመራሮች **በድሬዳዋ ከተማ** ባዘጋጀው የስልጠና ፕሮግራም ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት መረጃው ይደርስ ዘንድ በከተማው የሚገኙ የሚዲያ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን የድሬዳዋ መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ የአማርኛ፣ የኦሮሚኛና የሶማሊኛ ቋንቋዎች ጋዜጠኞች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመጡ 6 ጋዜጠኞች ተገኝተው ዘግበዋል። በዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም(በድሬ ቲቪ፣ በፌስቡክ ገጾችና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዌብሳይት) እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።
- ***ለሶማሌ ክልል*** ከተሞች ከንቲባዎችና ስራአስኪያጆች፣***ለሐረርና ለድሬዳዋ ክተሞች*** የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆችና ለሶማሌ ክልል የከተማና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች **በጅግጅጋ ከተማ** በተሰጠው በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ማሻሻያና በዜጎች ተሳትፎ ጽንሰ ሃሳብ ስልጠና ላይ የሶማሌ ክልል ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ የአማርኛና ሶማሊኛ ቋንቋ ዘጋቢዎች፣ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጅግጅጋ ቅርንጫፍ እና ከክልሉ ከተማና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል የመጡ ባለሙያዎች ኩነቱን የመዘገብና በዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም (በሶማሌ ቲቪና ፌስቡክ ገጽ፣በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዌብሳይትና ፌስቡክ ገጽ)እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምር አድርገዋል።
- በተመሳሳይ በራስ ገቢ ማሳደግና ባልተማከለ የፋይናንስ ስርዓት ዙሪያ ያተኮረ ስልጠና ***ለቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልል ከተሞች*** ከንቲባዎችና ስራአስኪያጆች፣ ለለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የከተማና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች **በአሶሳ ከተማ**


በተሰጠበት ወቅት የስልጠናውን አጠቃላይ ክንውን ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ይደርስ ዘንድ አሶሳ ከተማ የሚገኙ የሚዲያ አካላት ማለትም የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አሶሳ ቅርንጫፍ፤ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሚዲያ፤ከአሶሳ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ የመጡ አራት ጋዜጠኞችንና ሶስት ካሜራ ማኖች በድምሩ **ሰባት** ባለሙያዎች በዕለቱ ተገኝተው ዘግበዋል፤ በየዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም(በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማስ ሚዲያ የቴሌቪዥን ፕሮገራም፣በፌስቡክ ገጾችና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዌብሳይት) እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምርና እንዲሰርጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ የስልጠናውን ክንውን የሚያሳዩ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ምስሎችን በመውሰድ የዶክመንቴሽን ስራም ተከናውኗል፡፡

- የትብብር መድረኩ ጠቅላላ ጉባኤና የልምድ ልውውጥ አውደጥናት ***በሀዋሳ ከተማ*** በተከናወነበት ወቅት ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮረፖሬት (ኢቢሲ)፣ ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሀዋሳ ቅርንጫፍ፤ ከሲዳማ ክልል ብሮድካስት ኮርፖሬት የአማርኛና የሲዳምኛ ቋንቋ ጋዜጠኞች እንዲሁም ከሀዋሳ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ባለሙያዎችን ተሳታፊ በማድረግና እንዲዘግቡ በማድረግ በዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም (በኢቢሲና በሲዳማ ብሮድካስት ኮርፖሬት የቴሌቪዥን ፕሮግራምና ፌስቡክ ገጾች፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዌብሳይትና ፌስቡክ ገጽ ፣በሃዋሳ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ፌስቡክ ገጽ እንዲሁም በተለያዩ የኤፍ ኤም ራዲዮ ጣቢያዎች) እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምር አግዘዋል፡፡ ሁሉም ሚዲያዎች የዘገቡትን በወቅቱ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራዎችን በማከናወንና በሁሉም የትብብር መድረኩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በመለጠፍ እንዲታወቅ ተደርጓል፡፡

- የትብብር መድረኩ ከኔዘርላንድ የከተሞች ማህበር (VNGi) ዊአር ኤብል ፕሮግራም ጋር በመተባበር መጋቢት 15/2015 ዓ.ም ***በአዳማ ከተማ*** አስተዳደር በአካታች የስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ የአውደጥናት ፕሮግራም ባካሄደበት መድረክ የፕሮግራሙን አጠቃላይ ክንውን ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ይደርስ ዘንድ አዳማ ከተማ ለሚገኙ የሚዲያ አካላት ማለትም ለኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት (ኦቢኤን) ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አዳማ ቅርንጫፍ፣ ለአዳማ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ፣ ለአዳማ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ ተደርጎላቸው በቦታው ተገኝተው በመዘገብ በየዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም(ኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት፤አዳማ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ የቴሌቪዥን ፕሮገራም፣ አዳማ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት) በፌስቡክ ገጾችና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዌብሳይት) እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምርና እንዲሰርጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። የስልጠናውን ክንውን የሚያሳዩ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ምስሎችን በመውሰድ የዶክመንቴሽን ስራም ተከናውኗል።
- በአርባምንጭ ከተማ የተካሄደውን ስልጠና አስመልክቶ የስልጠናውን አጠቃላይ ክንውን ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ይደርስ ዘንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልልና በአርባምንጭ ከተማ ለሚገኙ የሚዲያ አካላት ማለትም ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት (ኢቢሲ) ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ፣ ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አርባምንጭ ቅርንጫፍ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፤ ደቡብ ቴሌቪዥን አርባምንጭ ቅርንጫፍ፤ ጋሞ ቴሌቪዥን እና አርባምንጭ ኤፍ ኤም 90.9 በቦታው ተገኝተው የዘገቡ ሲሆን በየዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም እንዲተላለፉ በማድረግ የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ እንዲጨምርና እንዲሰርጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። የስልጠናውን ክንውን የሚያሳዩ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ምስሎችን በመውሰድ የዶክመንቴሽን ስራም ተከናውኗል።



- ***በመቀሌ ከተማ ለትግራይ ክልል*** ከተሞች ስራአስኪያጆችና የከተማ ልማት ዘርፍ አመራሮች በተሰጠው ስልጠና ዲ-ደብሊው/ ድምፂ ወያነ የትግርኛና አማርኛ/ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ፤የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት (ኢቢሲ) መቀሌ ቅርንጫፍ፤የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) መቀሌ ቅርንጫፍ እና የመቀሌ ከተማ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በቦታው ተገኝተው የዘገቡ ቢሆንም ከዲ-ደብሊው/ድምፂ ወያነ የትግርኛና አማርኛ/ ቴሌቪዥን ፕሮግራም በስተቀር ሌሎች በየዜና ማሰራጫ ጣቢያዎቻቸውም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎቻቸው እንዲተላለፉ አላደረጉም፡፡ የስልጠናውን ክንውን የሚያሳዩ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ምስሎችን በመውሰድ የዶክመንቴሽን ስራም ተከናውኗል፡፡



- በአጠቃላይ በአምስት ስልጠናዎችና ሁለት አውደ ጥናቶች ላይ ከአራት ክልሎችና ድሬደዋ አስተዳደር ከሚገኙ ብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችና ማህበራዊ ሚዲያዎች የመጡ 51 ጋዜጠኞች ተገኝተው የዘገባ ስራ የሰሩ ሲሆን የተዘገቡ ዜናዎችን የሚዲያ ሞኒቴሪንግ ስራ በማከናወን በትብብር መድረኩ ማህበራዊ ሚዲያዎች (ሁለት የፌስቡክ ገጾች፣ ዩቲዩብ፣ቴሌግራም፣ ሊንክድኢንና ቲዊተር እንዲሁም ዌብሳይት) እንዲሁም በአገር አቀፍና በተለያዩ የክልሎች ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲተላለፍና የሁነቶችን እንዲሁም የተቋሙን ዓላማ በተመለከተ መልዕክት ማስተላለፍና ማስረጽ ተችሏል። ይህ አፈጻጸም ባለፈው አመት 26 ጋዜጠኞች ተገኝተው የዘገባ ስራ ከሰሩት በእጥፍ ይበልጣል።

- ከዚህ ጎን ለጎን የትብብር መድረኩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በርካታ ተከታዮችን እያፈራ ሲሆን ለአብነትም ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በትዊተር 212፣ ቲክቶክ 1095፣ በሊንክድኢን 173 እና በፌስቡክ 8,500 ተከታዮች እንዳሉት መመልከት ተችሏል፡፡

3.4. ገቢን ለመሰብሰብ የተከናወኑ ግቦችና ተግባራት

ግብ 18፡ በአመቱ ከአባል ከተሞች ብር 40,350,000.00 ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ96 ነባርና አዲስ አባል ከተሞች ብር 22,230,000.00 በመሰብሰብ የግቡ 56 በመቶ ተከናውኗል፡፡


በ2017 በጀት ዓመት ውስጥ ከነባር አባል ከተሞች የአባልነት መዋጮ እና ከአዲስ አባላት ብር 40,350,000.00 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 22,230,000.00 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ ብር*20,405,000.00* ከነባር አባላት ዓመታዊ መዋጮና ውዝፍ ክፍያ ሲሆን ብር *1,825,000.00* ደግሞ ከ15 አዲስ አባል ከሆኑ ከተሞች የተሰበሰበ ነው፡፡ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከከፈሉ ከተሞች ብዛት አኳያ ሲታይ ባለፈው አመት 65 ከተሞች(48 ነባርና 17 አዲስ) ክፍያ የፈጸሙ ሲሆን አሁን ላይ ከ96(81 ነባርና 15 አዳዲስ) ከተሞች ገቢ በመሰብሰብ የእቅዱ 56 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ከገቢ መጠን አኳያ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ተሰብስቦ ከነበረው ብር 16,385,000.00 ጋር ሲነጻጸር በ35 በመቶ ብልጫ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡


ግብ19: ከውጭ አገር ነባር ዩኤልጂ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሃብት ድጋፍ 5,304,776.44 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ መቶ በመቶ ተከናውኗል፡፡

በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት ተገቢውን ዓመታዊ ዝርዝር እቅድ ተዘጋጅቶ በበጀት መጠየቂያ ቅፅ መሰረት ብር 5,304,776.44 ተሰብስቧል፡፡ ፕሮጀክቱንም በተቀመጠለት ጊዜ በመዝጋት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ግቡ መቶ በመቶ ተከናውኗል፡፡

ሰንጠረዥ1፡ የአመቱ የገቢና ወጪ አፈጻጸም

	ዝርዝር	የ1ኛ ሩብ ዓመት	የ2ኛ ሩብ ዓመት	የ3ኛ ሩብ ዓመት	የ4ኛ ሩብ ዓመት	ድምር
ገቢ	አዲስ አባል ከተማ ገቢ	210,000.00	820,000.00	210,000.00	585,000.00	**1,825,000.00**
	ነባር አባል ከተማ ገቢ	3,955,000.00	9,650,000.00	3,400,000.00	3,400,000.00	**20,405,000.00**
	ዩኤልጂ ፕሮጀክት	5,304,776.44	-	-	-	5,304,776.44
	ድምር	*9,469,776.44*	*10,470,000.00*	*3,610,000.00*	*3,075,000.00*	*27,534,776.44*
ወጪ	አስተዳደር ወጪ (20%)	1,014,088.60	1,255,498.24	1,525,730.70	2,175,650.35	5,970,967.89
	የፕሮግራም ወጪ (80%)	3,289,996.01	12,126,656.27	4,433,093.05	3,592,952.03	23,442,697.36
	ድምር	4,304,084.61	13,382,154.51	5,958,823.75	5,768,602.38	29,413,665.25






❖ *ትብብር መድረኩ በአመቱ ለመሰብሰብ ካቀደው ብር 53,654,776.44 አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ 51.3 በመቶ እንደሆን ማየት ይቻላል።*

ሰንጠረዥ 2፡ የነባር አባል ከተሞች የ2017 ዓ.ም አመታዊ መዋጮ ክፍያ አፈጻጸም እስከ 4ኛው ሩብ ዓመት ፤

ተ.ቁ	በ1ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች(19)	ተ.ቁ	በ2ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (40)	ተ.ቁ	በ3ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (12)	ተ.ቁ	በ4ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (10)
1	መቱ ከተማ	20	አዲግራት	60	ከሚሴ	72	አምቦ ከተማ
2	ጋምቤላ	21	ይርጋጨፌ	61	ወልቂጤ	73	አርባምንጭ ከተማ
3	ባምባሲ	22	አቢአዲ	62	ነፋስ መውጫ	74	ሾኔ ከተማ
4	ግልገል በለስ	23	ሆለታ	63	ሽሬ	75	ገንደውሃ ከተማ
5	በደሌ	24	ማይጨው	64	አዳማ	76	ቆላድባ ከተማ
6	ቡልጋ	25	አድዋ	65	ወረታ	77	ሁመራ ከተማ
7	የጉኒኖ	26	ሽራሮ	66	መሆኒ	78	ጠበላ ከተማ
8	እንጥጮ	27	ፍረወይኒ	67	ደብረብርሃን	79	ጎደሬ ከተማ
9	ራማ	28	እዳጋ ሀሙስ	68	ቢሾፍቱ	80	ሻሁራ
10	እዳጋ አርቢ	29	ወናጎ ከተማ	69	መቀሌ	81	ደ/ታቦር
11	ሀውዜን	30	ጂማ ከተማ	70	ደጎሎ	82	

ተ.ቁ	በ1ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች(19)	ተ.ቁ	በ2ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (40)	ተ.ቁ	በ3ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (12)	ተ.ቁ	በ4ኛው ሩብ ዓመት የከፈሉ ከተሞች (10)
12	ሰመራ	31	ገደብ ከተማ	71	ነጌሌ አርሲ	83	
13	ዉቅሮ	32	ደሴ ከተማ				
14	አይከል	33	ወላይታ				
15	ሸገር	34	ይርጋለም				
16	አክሱም	35	አጸቢ እንዳስላሴ				
17	ሀዋሳ	36	በሌ ሀዋሳ				
18	አዴት	37	ደጀን				
19	ቻግኒ	38	ቡታጅራ				
		39	ዲላ ከተማ				
		40	ሀላባ ከተማ				
		41	አረርቲ ከተማ				
		42	ድሬዳዋ ከተማ				
		43	ኮረም ከተማ				
		44	ሆሳዕና ከተማ				
		45	ሊሙ ገነት				
		46	ኮምቦልቻ				
		47	አረካ ከተማ				
		48	ደብረማርቆስ				
		49	ሻሸመኔ ከተማ				
		50	ሐረር ከተማ				
		51	አማኑኤል ከተማ				
		52	ነቀምት ከተማ				
		53	መካነየሱስ				
		54	ሳውላ ከተማ				
		55	ጊምቢ ከተማ				
		56	ወገዳ ከተማ				
		57	ወሊሶ ከተማ				
		58	ወልዲያ ከተማ				
		59	ቦዲቲ ከተማ				


በበጀት አመቱ በሙሉና በከፊል ክፍያ የፈጸሙ ነባር አባል ከተሞች በክልል
አማራ ክልል(23/30)
ኦሮሚያ ክልል(14/14)
ትግራይ ክልል(18/18)
አይከል ከተማ (150ሺ)
አዴት ከተማ
ቻግኒ (200 ሺ)
ደሴ ከተማ
ደጀን ከተማ (100 ሺ)
አረርቲ ከተማ
ኮምቦልቻ ከተማ
ደብረማርቆስ (500 ሺ)
መካነየሱስ ከተማ
ወገዳ ከተማ
ወልዲያ(1ሚሊየን50ሺ)
ከሚሴ
ነፋስ መውጫ
ወረታ
ደ/ብርሃን
ደሴ(100 ሺ)
አማኑኤል
ገንደውሃ100 ሺ)
ሁመራ(250 ሺ)
ቆላድባ (100 ሺ)
ሻሁራ(100 ሺ)
መቱ ከተማ
በደሌ ከተማ
ሸገር ከተማ
ሆለታ ከተማ
ጂማ ከተማ (800 ሺ)
ሊሙ ገነት ከተማ
ሻሸመኔ ከተማ
ነቀምት ከተማ
ጊምቢ ከተማ
ወሊሶ ከተማ (200
አዳማ
ቢሾፍቱ(500 ሺ)
ነጌሌ አርሲ
አምቦ
አንጥጨ ከተማ
ራማ ከተማ (50 ሺ)
አዲጋ አርቢ ከተማ (45 ሺ)
ሀውዜን ከተማ
ዉቅሮ ከተማ
አክሱም ከተማ (100 ሺ)
አዲግራት ከተማ
አቢአዲ ከተማ
ማይጨው ከተማ
አድዋ ከተማ
ሽራሮ ከተማ
ፍረወይኒ ከተማ
አዲጋ ሀሙስ ከተማ
ኮረም ከተማ (100 ሺ)
መቀሌ
መሆኒ
ሽሬ
አጽቢ
15



በበጀት አመቱ በሙሉና በከፊል ክፍያ የፈጸሙ ነባር አባል ከተሞች በክልል
ደቡብ ኢት/ያ(12/13)
ማዕከላዊ ኢት/ያ ክልል(5/5)
ሱማሌ ክልል(1/6)
ድሬደዋ አስተዳደር(1)
የጉኒኖ ከተማ
ይርጋጨፌ ከተማ
ወናጎ ከተማ
ገደብ ከተማ
ወላይታ ከተማ
በሌሀዋሳ ከተማ
ዲላ ከተማ
አረካ ከተማ
ሳውላ ከተማ (150 ሺ)
ቦዲቲ ከተማ
አርባምንጭ(500 ሺ)
ጠበላ
ቡታጅራ ከተማ
ሀላባ ቁሊቶ(200 ሺ)
ሆሳዕና ከተማ (750 ሺ)
ወልቂጤ
ሾኔ(250ሺ)
ጅጂ
ድሬደዋ ከተማ(200 ሺ)
17


የነባር አባል ከተሞች ክፍያ አፈጻጸም በክልል የቀጠለ

ሲዳማ ክልል(2/2)	ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል(2/3)	ጋምቤላ ክልል(1/1)	ሐረሪ ክልል(1/1)	አፋር ክልል(1/1)
□ሐዋሳ ከተማ □ይርጋለም ከተማ (150 ሺ)	□ግልገል በለስ □ባምባሲ ከተማ	□ጋምቤላ ከተማ	□ሐረር ከተማ	□ሰመራ ከተማ


19

ክፍያ ያልፈጸሙ ነባር አባል ከተሞች





ባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ሙሉ በሙሉ ክፍያ የፈጸሙ ከተሞች ብዛት 34 ሲሆን በከፊል ከፍያ የፈጸሙ 14 እና ምንም ክፍያ ያልፈጸሙ ደግሞ 31 ከተሞች ከነበሩበት አንጻር ትልቅ መሻሻል ታይቷል። በሌላ በኩል አባል ከተሞች ክፍያ የፈጸሙበትን ጊዜ ስንመለከት 19 (23 በመቶ) ከተሞች በ1ኛው ሩብ ዓመት፤ 40(50 በመቶ) ከተሞች በ2ኛው ሩብ ዓመት፤ 12(15 በመቶ) ከተሞች በ3ኛው ሩብ አመትና 10(12 በመቶ) ከተሞች ደግሞ በ4ኛው ሩብ ዓመት እንደሆነ መመለከት ተችሏል። በመሆኑም አብዛኛዎቹ ከተሞች የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ባስተላለፈው አቅጣጫ መሰረት ክፍያቸውን የፈጸሙ መሆኑን ያሳያል።



የ2017 ዓ.ም የወጪ አፈጻጸም



በአጠቃላይ ስራ ላይ የዋለው ብር 29,413,665.25 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክት የወጣው ወጪ ብር 23,442,697.36 ሲሆን ለመደበኛ የወጣው ብር 5,970,967.89 ነው። ይህም ማለት 80 በመቶ ለፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እና 20 በመቶ ለመደበኛ በጀት የዋለ ነው።

ባለፈው አመት ለአስተዳደራዊ ወጪ ብር 3,075,240.76፣ *ለፕሮግራም ማስፈጸሚያ የወጣው ወጪ ደግሞ ብር* 57,101,578.88 *ሲሆን በጥቅሉ ብር* 60,176,819.64 *ወጪ የተደረገ ሲሆን* ባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው **የ8/92 በመቶ** ምጣኔ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት አሳይቷል። *ይህም የሆነው ባለፈው አመት የ9ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ልዩ ፕሮጀክት የነበረ በመሆኑና ለዚህም ማስፈጸሚያ ብር 43,535,700.00 ገቢ ተሰብስቦ የነበረ በመሆኑ ነው።*

ግብ 20፡ የትብብር መድረኩ ዓመታዊ የሂሳብ ሰነድ ኦዲት ተደርጓል።

የትብብር መድረኩን ዓመታዊ የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ኦዲተር በመቅጠር ኦዲት በማስደረግ የ2016 በጀት ዓመትን ገቢ እና ወጪ ሪፖርትና ዕቅድ ጨምሮ ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ በማቅረብ የማጸደቅ ስራ የተሰራ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸም እና ኦዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2017 ዕቅድን ለኦዲት ቦርድ የማስገባት ስራ ተከናውኗል። የኦዲት አስተያየትም ጥሩ (unqualified opinion) መሆኑን ሲያሳይ የግቡ አፈጻጸም ደረጃ **መቶ በመቶ** ነው።

ግብ 21 ፡ ወቅታዊ የፋይናንስ ገቢና ወጪ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል።


የ2017 ዓመታዊ እቅድ እና በጀት እንዲሁም ከሃምሌ/2016 እስከ ሰኔ/2017 ዓ.ም ያሉ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን የሚገልፅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። የግቡ አፈጻጸም ደረጃ መቶ በመቶ ነው።

ግብ 22፡የትብብር መድረኩን አንድ መደበኛ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና አንድ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ለማድረግ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል።

- የትብብር መድረኩ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ አመራሮች ጳጉሜን 1/2016 ዓ.ም ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አድዋ መታሰቢያ አዳራሽ በመሰብሰብ የትብብር መድረኩ የ2017 ዓ.ም በጀት 55,479,322.49 ብር እንዲሆን በሙሉ ድምፅ አፅድቀዋል። በተጨማሪም የቦርድ ሥራ አስፈጻሚ አባላቱ የትብብር መድረኩን የ2016 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም እና የኦዲት ሪፖርት እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድን በሙሉ ድምጽ አጽድቀዋል።

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ቦርድ ዋና ዋና ውሳኔዎች

- ከውጭ አገር የተገኙ ተሞክሮዎች ተቀምረው በአውደጥናት መልክ ለክቡራን ከንቲባዎች ማካፈልና ሰነዶቹንም ለአባል ከተሞች ማሰራጨት ቢቻል፤
- የከተሞች ውዝፍ ክፍያን በተመለከተ ቦርዱ የሚያውቀው ተሰብሳቢ ስለሆነ እስከ ሰኔ 2017 ዓ.ም ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ የ2016 ውዝፍ በዚህ በጀት ዓመት እስከ ጥር 2017 ዓ.ም እንዲሁም የ2017 በጀት ዓመት ክፍያ ደግሞ እስከ ታህሳስ 2017 ዓ.ም መከፈል ይኖርበታል፡፡
- የተቋማዊ መዋቅር ማሻሻይ ጥናት የድርጅቱን ዲጂታይዜሽን ስራዎች በሚያግዝ መልኩ ተጠንቶ እንዲቀርብ በማለት የትብብር መድረኩን ወደ ላቀ ደረጃ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ ውሳኔዎችን በመወሰንና ትብብር መድረኩ ውሳኔዎችን በባለቤትነት እንዲያስፈጽም አቅጣጫ በማስቀመጥ ስብሰባው ተጠናቋል። **በመሆኑም የግቡ አፈጻጸም ደረጃ መቶ በመቶ ነው።**






ምስል24፡ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ስብሰባ (ጳጉሜን/2016 ዓ.ም)

- በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከጥቅምት 26-27/2017 ዓ.ም በሃዋሳ ከተማ የተካሄደ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና ውሳኔዎች አስተላልፏል፡፡
  - ❖ የትብብር መድረኩ አርማ እና ስያሜ ሊሻሻል ይገባል፡፡
  - ❖ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ እና የመመዝገቢያ ክፍያዎች መከለስ አለባቸው፡፡
  - ❖ በዚህ በጀት ዓመት የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ በየሩብ ዓመቱ እንዲሁም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲካሄድ ወስኗል፡፡ በመጨረሻም ጉባኤው የተሻሻለውን የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ አጽድቋል፡፡





ምስል25፡ የጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች ድምጽ ሲሰጡ



ግብ 23፡ የተቋሙን ሰራተኞች አቅም ለማጎልበት በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

- ሁለት የተቋሙ ሠራተኞች በራሳቸው ባገኙት ስልጠና ክፍያ ተፈጽሞላቸው ስልጠና የወሰዱ ሲሆን ሁለት ሰራተኞች ደግሞ የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ባወጣው የስልጠና መርሃ ግብር በመካታተል የስልጠና ዕድል ተመቻችቶ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ የግቡ አፈጻጸምም 44 በመቶ ነው፡፡

3.5. የፕሮግራምና የፕሮጀክት ሰራዎች የክትትልና ግምገማ ተግባራት

ግብ24፡ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ስትራቴጂክ ዕቅድ የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ (*Mid-Term Evaluation*) ተካሄዷል፡፡

- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ የሁለት አመት ተኩል አፈጻጸም አስመልክቶ የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህ የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ የሚያተኩረው ከዕቅዱ የሁለት ዓመት ተኩል አፈጻጸም የተገኘውን መረጃ በመጠቀም በትግበራው ሂደት ላይ ሲሆን ዓላውም እቅዱን በመተግበር እና በዓላማዎች መመዘኛዎች ስኬት ላይ ያለውን እድገት ለመገምገም፤ ዓላማዎችን በማሳካት ሂደት

እንቅፋቶችን ለመለየት፤ ድርጅቱን በስትራቴጂክ እቅዱ የመጨረሻ አጋማሽ ላይ ሊያግዙ የሚችሉ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመስጠት እንዲሁም የግምገማ ሪፖርቱ ቀጣዩን ስትራቴጂክ እቅድ ለማዘጋጀት እንደ ግብአት እንዲያገልግል በማሰብ የተከናወነ ሲሆን በዚሁ መሰረት በብዙዎቹ መመዘኛዎች የተሻለ ውጤት እንደተመዘገበ ግምገማው አሳይቷል። ለአብነትም በአቅም ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥ ለአባል ከተሞች የእውቀትና ተሞክሮ ማዕከል ሆኖ በማገልገል፤ የአባል ከተሞችን ቁጥር በመጨመር ረገድ የስትራቴጂክ እቅዱ ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የአባላት ቁጥር በ62 በመቶ ጨምሮ 111 የደረሰ መሆኑ፤ከአባል ከተሞች የሚሰበሰብ የአባልነት ክፍያ ድርሻ 48 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ ከ80 በመቶ በላይ የደረሰ መሆኑና የትብብር መድረኩ የአባል ከተሞችን በመወከል በአገር አቀፍና አለም አቀፍ መድረኮች የአጋርነትና ኔትወርኪንግ ስራን በማጠናከር ረገድ ጉልህ መሻሻሎች እንዳሉ ግምገማው አሳይቷል፡፤

ግብ 25፡ ለአባል ከተሞች የሚዘጋጁ ስልጠናዎችና አውደጥናቶች አፈጻጸም ግምገማ እንዲሁም የስልጠናና የልምድ ልውውጥ የፍላጎት ዳሰሳ ተከናውኗል።

- በበጀት አመቱ በተከናወኑ ስልጠናዎችና አውደጥናቶች ወቅት 7 የስልጠናዎችና አውደጥናቶች አፈጻጸም ግምገማ እንዲሁም 2 የስልጠናና የልምድ ልውውጥ ፍላጎት ደሰሳ ተካሂዷል። በዚሁ መሰረትም የተዘጋጁ ስልጠናዎችና አውደጥናቶች አፈጻጸም ግምገማ ለማድረግ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ውጤት የሚያሳየው በቀረቡት ገለጻዎች ተሳታፊዎች ደስተኛና በጋራም ሆነ በተናጠል ትልቅ ትምህርት የወሰዱበት መድረክ መሆኑን ገልጸው መድረኮቹ በሁሉም ረገድ የተሳኩና ለተሳታፊዎች ግንዛቤን የፈጠሩ እንዲሁም ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመተግበር ተነሳሽነትን የፈጠረባቸው መሆኑን አመልክተዋል።

- በሌላ መልኩ የተደረጉ የስልጠናና አውደጥናት ፍላጎት ዳሰሳ ውጤቶች እንደሚያሳየው ስልጠናን በተመለከተ የፍላጎት ዳሰሳ ከተደረገባቸው ሁለት መድረኮች የአገልግሎት አሰጣጥና ዲጂታይዜሽን፤ የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አሰባሰብ፤ በስማርት ሲቲ ትግበራ፤ በካዳተር ስርዓት እንዲሁም በከተማ አመራር ላይ ስልጠና እንደሚፈልጉ በተደጋጋሚ የተጠየቁ ሲሆን በተመሳሳይ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ አሰባሰብ፤ በአገልግሎት አሰጣጥና ዲጂታይዜሽን፤

በስማርት ሲቲ ትግበራ፤ በካዳስተር ስርዓት፤በኮሪደር ልማት ስኬቶችና ተግዳሮቶች እንዲሁም በንብረት ግብር አተገባበር ዙሪያ የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ማድረግ እንደሚፈልጉ የቅድሚያ ቅድሚያ በመስጠት ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ሲሆን በቀጣይ የሚዘጋጁ የስልጠናና አውደጥናት መድረኮች በተቻለ መጠን የከተሞችን ፍላጎቶች መሰረት ተደርገው እንዲዘጋጁ የሚደረግ ይሆናል፡፡



ግብ 26፡ በተመረጡ 9 አባል ከተሞችና ከተማ ልማት ቢሮዎች በመገኘት የስልጠናዎች፤ አውደጥናቶችና ትምህርታዊ ጉዞዎች ተግባራዊነትና ያመጡትን ፋይዳ የተመለከተ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ በ2 ከተሞች ተደርጓል፡፡

በአዳማና ቢሾፍቱ ከተሞች በመገኘት ክትትል የተደረገ ሲሆን በከተሞቹ ተግባራዊ የተደረጉ የተለያዩ የልማት ስራዎችና ለሌሎች ከተሞች የሚተላለፉ ውጤታማ መልካም ተሞክሮዎች በተመለከተ ያሉ የአፈጻጸም ሂደቶችን ለማየት በተደረገው ጥረት በሁለቱም ከተሞች በርካታ መልካም አፈጻጸም የታየባቸው ተግባራት እንዳሉ ተለይቶ ተሞክሮዎቹን ለሌሎች ከተሞች

ለማስተላለፍ ይረዳ ዘንድ የምርጥ ተሞክሮ መለያና መቀመሪያ ሰነድ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

የትብብር መድረኩ ማኔጅመንት አባላት በ10/07/2017 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር በመገኘት ከቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ም/ስራ አስኪያጅና የማዘጋጃ ቤት የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ አዲሱ መልካ ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ ክቡር ስራአስኪያጁ እንደገለጹት የቢሾፍቱ ከተማ 62,125.84 ስኩዌር ሜትር የቆዳ ስፋት ያላት ሲሆን ይህም ለመኖሪያ፤ ለኢንዱስትሪና ለከተማ ግብርና ተብሎ የተለየ ሲሆን አሁን ላይ ከተማዋ በ20,000 ስኩዌር ሜትር ቦታ ላይ ያረፈች መሆኗን ገልጸዋል፡፡

በውይይቱም አቶ አንዱዓለም ጤናው የትብብር መድረኩ ስለሚሰራቸው ስራዎችና የማኔጅመንት አባላትም በከተማው ስለተገኙበት አላማ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በመቀጠልም ክቡር ስራ አስኪያጁ ከተማ አስተዳደሩ በኮሪደር ልማት፤የአስፋልት መንገድ ስራ፤ በካዳስተርና በስማርት ሲቲ ትግበራ ዙሪያ እየተሰሩ ስላለ የልማት ስራዎች በስፋት ገለጻ አድርገዋል፡፡ የማኔጅመንት አባላቱ ባደረጉት የመስክ ጉብኝትም እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደርና የአስፋልት መንገድ ስራ እንዲሁም ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማቋቋሚያ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ቢዝነስ ግሩፕ አሰሪነት እየተገነቡ ያሉ 7 ባለ 7 ፎቅ ህንጻዎች ግንባታ ስራን ጎብኝተዋል፡፡

ስማርት ሲቲ ትግበራን በተመለከተ

ከተማ አስተዳደሩ ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ አማካይነት የስማርት ሲቲ አተገባበር ጥናት አካሄዷል፡፡ በዚሁ መሰረት በስድስት የስማርት ሲቲ ምሶሶዎች ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ተለይቷል፡፡

- ከተማዋን የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ 7ቱን ሐይቆች የማገናኘት ስራ በጥናቱ በተመላከተው መሰረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ሐይቆቹ በግል ባለሃብቶች የለሙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለአከባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ ባለመሆናቸው ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ ለማድረግ በመንገድ ማስተሳሰርና የማገናኘት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ከተማዋን የሚመጥን ስታንዳርድ ከለር ተለይቶ በዚሁ አግባብ “***ንጹህ፤ አረንጓዴና ደማቋ” ቢሾፍቱ*** በሚል መርህ የስማርት ሲቲ ትግበራ ለመንግስትና ለግል ተቋማት ካስኬድ ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡

- በ11 የከተማው ሴክተር ተቋማት የዲጂታል አገልግሎት ስራ ተጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በከተማው እያንዳንዳቸው 7 ኪሎሜትር ርቀት የሚሸፍኑ 88 ካሜራዎች እንዲተከሉ ተደርጎ እስካሁን የከተማው 30 በመቶ እንዲሸፈን ተደርጓል፡፡ 24 ሰዓት የሚሰራ የሁኔታ መከታተያ ክፍል(*Situation Room*) ተደራጅቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ከዚህ በፊት በጋሪ፤ በመኪናና በባጃጅ ይፈጸሙ የነበሩ በርካታ ህገ ወጥ ወንጀሎችና መቆጣጠር አስችሏል፡፡

የኮሪደር ልማት ስራን በተመለከተ

የቢሾፍቱ ከተማ የኮሪደር ልማት የሳይክል መንገድ፤ የእግረኛ መንገድ፤ የፍሳሽ ማስወገጃ፤ የመብራትና ስልክ ዝርጋታ እንዲሁም **የከተማ ውስጥ ደን** (Inner City Forest) ልማት ስራዎችን አቀናጅቶ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ 24 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ በ12 ቢሊየን ብር በጀት በመሰራት ላይ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ባለው 56 ሄክታር የአረንጓዴ ስፍራ ውስጥ 32 ሄክታር መሬት በተለያዩ የእጽዋት ዝርያዎች ተሸፍኗል፡፡ የተተከለ ዛፎችንና የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን እንዲንከባከቡ በሙያው የተመረቁ ባለሙያዎች ቅጥር ተፈጽሞ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በከተማው የሚሰራው የአረንጓዴ ልማት ስራ ለከተማ ውበት ብቻ ሳይሆን የአካባቢ የዘላቂ ልማትን በማሰብ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ በሚያስችል ሁኔታ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህም ለሌሎች ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት የሚሆን ተሞክሮ እንደሆነ ታይቷል፡፡

የመሬት ምዝገባና ካዳስተር ስራ በተመለከተ

የመሬት መረጃን ወደ ዲጂታል ስርዓት ለመቀየር በታቀደው መሰረት በከተማው ካሉ 3 ክ/ከተሞች በአንዱ ስራ ተጀምሯል፡፡ ይህንኑ ስራም በበላይነት የሚያስተባብር ባለሙያ ተመድቦ እየተሰራ እንደሚገኝ ተብራርቷል፡፡





ምስል26፡ የኢከትመ ማኔጅመንት አባላት በቢሾፍቱ ከተማ የመስክ ጉብኝት ሲያደርጉ

4. በእቅድ ተይዘው ያልተከናወኑ ተግባራትና ያልተከናወኑበት ምክንያት

- በ2017 በጀት ዓመት ከተያዙት ዕቅዶች መካከል ጥቂቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይከናወኑ ቀርተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋነኛውና በርካታ ተግባራትን ያስተጓጎለው የበጀት እጥረት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለ100 አባል ከተሞች በ“ከተማ ከንቲባዎች ስኬቶች፣ ተግዳሮቶችና እድሎች” ዙሪያ ለማካሄድ የታቀደ የልምድ ልውውጥ መድረክ፤ለ125 የከተሞች ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊዎች በማናጀሪያል ኮሙዩኒኬሽን ዙሪያ ለመስጠት የታቀደ ስልጠና እንዲሁም ለ100 የከተማ ሥራ አስኪያጆች በ“Urban Resilience” እና

በ“ዲጂታላይዜሽን” ላይ ትኩረቱን ያደረገው ሥልጠናም በዚሁ የፋይናንስ እጥረት ምክንያት ሊሰረዝ ችሏል፡፡

- ከበጀት ችግር በተጨማሪ ከተቋሙ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ክልላዊ ሁኔታዎች ምክንያት የተስተጓጎሉ ዕቅዶችም ነበሩ፡፡ ለአብነት በአማራ ክልል ለሚገኙ 30 ከተሞች ከንቲባዎችና ኃላፊዎች በ“Urban Resilience” እና “ቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት” ላይ ታቅዶ የነበረው ሥልጠና በክልሉ በነበረው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት ሊከናወን አልቻለም፡፡ እንዲሁም ከታህሳስ 15 እና 16 ቀን 2017 ዓ.ም ለኦሮሚያ ክልል አባል እና እጩ አባል ከተሞች እንዲሁም ለክልሉ የከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ የስራ ኃላፊዎች በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ጅማ ከተማ ላይ ስልጠና ለመስጠት ለከተሞች ጥሪ እንዲተላለፍ ለቢሮው ደብዳቤ ተጽፎ ስልጠናው እንዲሰጥ መግባባት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ክልሉ ላልተወሰነ ጊዜ ስልጠናው እንዲራዘም በመጠየቁ ምክንያት ስልጠናውን ማሳካት አልተቻለም፡፡

- የትብብር መድረኩን አገልግሎቶች የሚያስተዋውቅና ተቋሙ በከተማ ልማት ዘርፍ ለአባል ከተሞች የሰጣቸውን አውደጥናቶችና ስልጠናዎች ተግባራዊ ስለመሆናቸውና ስኬታማነታቸውን የሚዳስስ የ15 ደቂቃ ዶክመንተሪ ፊልም ለማዘጋጀት ታቅዶ አልተከናወነም፤

- የትብብር መድረኩ አቅም በቢሮ መገልገያዎች እንዲጠናከር ይደረጋል የሚል ዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በበጀት እጥረት ምክንያት ማከናወን አልተቻለም፡፡

- በተመረጡ ከተሞች በመገኘት የስልጠናዎች፤ አውደጥናቶችና ትምህርታዊ ጉዞዎች ተግባራዊነትና ያመጡትን ፋይዳ የተመለከተ ክትትልና ግምገማ በታቀደው መሰረት በበቂ ሁኔታ አለመከናወኑ፤

5. ከእቅድ ውጭ የተከናወኑ ተግባራት

በበጀት ዓመቱ ከተያዘው መደበኛ ዕቅድ በተጨማሪ የመድረኩን ዓለም አቀፍ ተደራሽነት ለማሳደግና የተገኙ ስኬቶችን በስፋት ለማጋራት ያለሙ ስትራቴጂካዊ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

- በአዲስ አበባ በተዘጋጀው የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ዝግጅት ላይ በአዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ በመሳተፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ከመደረጉም በተጨማሪ በአውደ

ርዕይ ላይ በመሳተፍ የትብብር መድረኩን አጠቃላይ ገጽታና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለጎብኝዎች ከማስተዋወቅም በላይ ከተለያዩ ተቋማት ጋር የኔትወርኪንግ ስራ ተከናውኗል፡፡

- ከዚህ ውጪ የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ላይ መሳተፉንና ሰለ ፎረሙ አጠቃላይ ሁኔታ የሚዳስስ ዜና አንዲሁም የኢትዮጵያ ብሮድካስቲን ኮርፖሬት (ኢቢሲ) ፎረሙን በተመለከተ ባዘጋጀው ዶክመንተሪ ፊልም ላይ የትብብር መድረኩ ዋና ዳይሬክተርን ቃለመጠየቅ እንዲያደርጉ በማመቻቸት የተቋሙ አጠቃላይ አገልግሎቶች ለህዝብ እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

- የትብብር መድረኩ ዋና ዳይሬክተር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጣ ፕላስ ከተሰኘው ፕሮግራም ጋር በከተማ ልማት ዘርፍ ዙሪያ ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ዩቲዩብን ጨምሮ በሁሉም የትብብር መድረኩ ሶሻል ሚዲያዎች ላይ እንዲጫን በማድረግ የተቋሙን እይታ ለመጨመርና ገጽታ ለመገንባትም ተችሏል፡፡



ምስል 27፡- የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም

- ከዓለም አቀፉ የከተሞችና የአካባቢ መንግሥታት የትብብር መድረክ (UCLG-CIB Working Group) ጋር ያለውን ግንኙነት በመጠቀም የመድረኩን ቁልፍ ስራዎች በድርጅቱ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ እንዲታተሙ በማድረግ ረገድ በተለይም በኔዘርላንድና በኬንያ የተካሄደውን የልምድ ልውውጥ ጉዞ እንዲሁም በአገር ውስጥ ለአባል ከተሞች የተሰጡትን የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችና አውደጥናቶች ፋይዳና ውጤት የሚተነትኑ ዝርዝር

ጽሑፎች ተዘጋጅተው ዌብሳይታቸው ላይ ተጭኗል። ጽሑፎቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቅ መድረክ ላይ መውጣታቸው የመድረኩን ሥራዎች ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማስተዋወቅና ሰፊ እውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ አስችሏል። ከዚህም ባሻገር ይህ የዜና ሽፋን የኢትዮጵያ ከተሞች እንደ ማኅበራዊ ጥበቃ፣ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትና የምግብ ዋስትና ባሉ ወሳኝ ዘርፎች እያስመዘገቡ ያሉትን ተጨባጭ ለውጦች በማሳየት የመድረኩን መልካም ገጽታ ለመገንባት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ይህም ከUCLG-CIB ጋር ያለውን ሙያዊ ግንኙነት ይበልጥ በማጠናከር ለቀጣይ የትብብር ዕድሎች፣ የእውቀት ልውውጦች እና የጋራ ፕሮጀክቶች ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።


UCLG CIB
Working Group
Capacity and Institution Building

ABOUT US | NEWS | LIBRARY | COMPEND

Cross-Continental Urban Governance Exchange: Ethiopian Cities Municipalities

September 13, 2024 cib

From June 3-8, 2024, a delegation of representatives from the Ethiopian Cities Association (ECA), an alliance of 98 Ethiopian cities working towards improving the living conditions of the urban Ethiopian population, completed a six-day study tour to the Netherlands, focusing on urban governance and development practices. The delegation, which included mayors from Mekelle, Dire Dawa, and Wolkite, along with ECA staff and a VNG International expert, participated in a series of knowledge-sharing sessions and site visits across several Dutch cities.

The tour was held as part of the Uniting Local Government in Ethiopia (ULGE), a European Union (EU) funded project implemented by VNG International and ECA. The study tour kicked off at the national headquarters of the Association of Netherlands Municipalities (VNG) in The Hague, where the delegation received a warm welcome. VNG International Director, Mr. Pieter Jeroense, provided a briefing to the Ethiopian visitors.

Home ▸ News

Ethiopian Cities Unlock Investment Strategies at UCLG Africa Conference

January 29, 2025 cib



A six-member delegation from the Ethiopian Cities Association (ECA), led by Dessie City Mayor H.E. Samuel Molalegn, participated in the Fourth African Investment Conference in Kisumu, Kenya (November 25–27). Hosted by AfSNET, Afreximbank, and UCLG Africa, the event focused on leveraging the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) to boost sub-sovereign trade and investment.

Under the theme *"AfCFTA: A Pathway for Sub-Sovereign Development,"* discussions highlighted digital platforms like the African Trade Gateway and Kisumu's emergence as an investment hub. The delegation, including mayors from Shire, Mettu, Yirgachefe, Bambasi, and Gilgel Beles cities, gained experiences of sustainable urban planning, investor engagement, and digital infrastructure to enhance municipal services.

Mayor Samuel Molalegn emphasized translating continental strategies into local action, stating, *"Ethiopian cities are poised to lead Africa's economic integration."* The conference reinforced ECA's role in advancing Ethiopia's urban development through AfCFTA-aligned frameworks.

Contact: ECA Communications Team - ethiopiancities2011@gmail.com www.ethiopiancities.org

UCLG CIB
Working Group
Capacity and Institution Building

ABOUT US | NEWS | LIBRARY | COMPEND

Home ▸ News

Empowering Ethiopian Cities: Training for Sustainable Urban Dev conflict Tigray

November 12, 2024 cib



In a significant step toward regional recovery and development, the Ethiopian Cities Association conducted a two-day training program for over 40 Mayors from the Tigray Region. The training held in Dire Dawa Administration, marks a crucial transition from conflict to constructive urban development focused on critical areas of city management including decentralized governance, municipal revenue generation, and urban food security.

"This program represents more than just training; it is about rebuilding our urban fabric with contemporary concepts and sustainable practices," stated Mr. Solomon Yidego, Deputy Head of the Urban and Construction Bureau of the Tigray Regional Government. His words reflect the region's commitment to moving forward following the Pretoria Peace Agreement, emphasizing the role of strong municipal leadership in maintaining peace and stability.

Ethiopian Cities Association Director General, Mr. Andualem Tenaw, outlined the organization's approach to urban development. "Our focus is on creating smart, inclusive cities that serve all residents effectively," he explained. He mentioned the importance of learning from both domestic and international experiences, which will be facilitated through organized tours and knowledge-sharing programs to address post-conflict challenges.

The training program specifically addressed three critical areas: decentralization principles, municipal revenue enhancement, and urban food security strategies. These topics are particularly relevant in the context of Tigray's recovery, where strengthening local governance and ensuring basic services are crucial for maintaining peace and stability.

The initiative demonstrates how urban development can serve as a cornerstone for sustainable peace and human rights protection in post-conflict regions.



Strengthening Urban Safety Nets: Ethiopian Cities Unite for Disability Inclusion and Food Security

April 29, 2025 ob

Ethiopian Cities Association (ECA), in collaboration with VNG International's "We Are Able" program, organized a one-day experience sharing workshop in Adama. The event focused on inclusive urban safety net projects, emphasizing the participation of people with disabilities (PWDs), implementation challenges, and sustainable solutions.

Mr. Birhanu Teshome, Head of the Urban Food Security and Safety Net Office at the Ministry of Urban Development and Infrastructure, highlighted the significant progress of Ethiopia's Inclusive Urban Food Security Safety Net Program.

"Initially covering only 11 cities, the program now benefits 1.76 million citizens across 88 cities with a budget of $703 million," he said. He added that the program has brought tangible improvements in food security and livelihood support for vulnerable groups, including PWDs.

Mr. Andualem Tenaw, Director General of ECA, stressed the association's efforts to tackle service delivery inefficiencies, governance gaps, and uneven urban development.

"We are collaborating with local and international partners to help cities learn from best practices," he said. "This second workshop with the 'We Are Able' program is a prime example of knowledge-sharing to foster inclusive job creation and urban development."

The workshop also highlighted the "We Are Able" program, which seeks to enhance food security while ensuring that urban development considers the needs of people with disabilities. Participants discussed various activities designed to create job opportunities for residents and promote inclusive practices.

Experts from different cities presented their experiences on employment opportunities for PWDs, addressing implementation challenges and solutions. Cities represented included Addis Ababa, Dire Dawa, Harar, and Adama.

The workshop reinforced the need for stronger collaboration between cities, development partners, and disability advocates to ensure no one is left behind in Ethiopia's urban growth.

Search

Search

Share

Tweets

Looking back at 8 years of CIB - departure jes Post https://t.co/ejE7wny9y6 via @UCLG_CIB @uclg_org #UCLGmeets... https://t.co/5tatheqkZZ
2023-06-13 09:28

Marràqueix ha acollit la reunió anual del Grup de Treball de Capacitat i Creació Institucional de @uclg_org... https://t.co/9jAdBkjDjf
2023-06-02 10:53

ምስል 28፡- በተቋሙ የዜና ሽፋን የተሰጣቸው የአቅም ግንባታ ስራዎች

• የትብብር መድረኩ ዋና ዳይሬክተር ከተባበሩት የአለም ከተሞች እና አካባቢ መንግስታት (United Cities and Local Governments) ፕሬዝዳንት እና የሜግ ከተማ ክቡር ከንቲባ ቫን ዛነን ጋር ጥቅምት 23/2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውይይት አድርገዋል፡፡ የዚህ ውይይት ዋና አላማ በአለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የከተሞችን እና የአካባቢ መንግስታት ትብብር ስለሚጠናከርበት ሁኔታ እና አንገብጋቢ በሆኑ የኢትዮጵያ የከተማ ልማት ችግሮች ዙሪያ የጋራ አረዳድ ለመፍጠር እና መፍትሄዎች ለማመላከት ነበር፡፡ ውይይቱም የኢትዮጵያ ከተሞች የልማት፣ የመልካም አስተዳደር እና ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፖሊሲዎችን በመተግበር ረገድ የተስተዋሉ መልካም ተሞክሮዎች እና የትብብር መድረኩ አባላት ፍላጎት እና አገልግሎት አሰጣጥ ነባራዊ ሁኔታን አካቷል፡፡ ሁለቱም ሃላፊዎች ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት እና የማህበረሰብን ችግሮችን የመቋቋም አቅም ለማጎልበት የከተሞች ሚና ከፍ ያለ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተው በመወያየት በትብብር መድረኩ አባል ከተሞች መካከል ያለውን ትብብር ለማጠናከር እና ከተሞች የመንግስት ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን በተሟላ ሁኔታ እንዲተገብሩ አቅማቸውን ለማሳደግ የጋራ መግባባት ተፈጥሯል፡፡




ምስል 29፡ የትብብር መድረኩ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ከUCLG ፕሬዝዳንት እና የሄግ ከተማ ክቡር ከንቲባ ቫን ዛነን ጋር

- **የትብብር መድረኩ ከኔዘርላንድ የከተሞች ማህበር (VNGi) ዊአር ኤብል ፕሮግራም ጋር በመተባበር መጋቢት 15/2015 ዓ.ም በአዳማ ከተማ አስተዳደር በአካታች የስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ የአውደጥናት ፕሮግራም በማካሄድ የአካል ጉዳተኞች በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች አካታችነትና ተጠቃሚነት ዙሪያ የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር ተከናውኗል፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ከድሬዳዋ አስተዳደር፣ ከሀረር ከተማ አስተዳደር፣ ከአዳማ ከተማ አስተዳደር እና ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የተውጣጡ 35 የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎች በአውደጥናቱ ላይ ተሳትፈ ሆነዋል፡፡**

በአውደጥናቱ ላይም የድሬደዋ ከተማ የስራና ክህሎት ቢሮ ተሞክሮ ሰነድ፣ የአዳማ ከተማ የስራና ክህሎት ቢሮ ተሞክሮ፣ የሐረር ከተማ ሴፍቲኔት ተሞክሮ፣ የፌደራል የከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ጽ/ቤት የአካል ጉዳተኞች በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት አካታችነትና ተጠቃሚነት፣ በአፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮችና ዘላቂ መፍትሔዎች እንዲሁም የዊአር ኤብል ፕሮግራም ስኬቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

<u>የእውቀት ሽግግርና ስርፀት፤</u>

በአውደ ጥናቱ የተካሄደው የእውቀት ሽግግርና ስርፀት መርሃ ግብር የአካል ጉዳተኞችን በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች ውስጥ ተጠቃሚነትና አካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ

ተግባራዊ ዕውቀቶችንና ልምዶችን ለማጋራት ያለመ ነበር። ይህ የተቀናጀ አካሄድ ፖሊሲን ከተግባር፣ ሀገራዊ እይታን ከአካባቢያዊ ተሞክሮ ጋር በማጣመር ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት የሚያስችል ጠንካራ መሠረት ለመጣል ታቅዶ የተከናወነ ነው።

የእውቀት ሽግግሩ ይዘት በሁለት ወሳኝ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን የመጀመሪያው "የአካል ጉዳተኞች በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች አካታችነትና ተጠቃሚነት" ሲሆን ይህ ክፍል በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንና ዘላቂ መፍትሄዎቻቸውን የዳሰሰ ነበር። ይህም አመራሮችና ባለሙያዎች ችግሩን በስፋት እንዲገነዘቡና ስኬታማ መፍትሔዎችን እንዲለዩ አስችሏቸዋል። ሁለተኛው ደግሞ "የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መስፈርት" ላይ ያተኮረ ሲሆን የምልመላ ሂደቱ ፍትሐዊና አካል ጉዳተኞችን ያላገለለ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ መርሆዎችንና ስልቶችን አካቷል።

ይህንን ዕውቀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ንድፈ-ሀሳብን ከተግባር ጋር ያጣመረ ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። የአዳማ፣ የሐረር እና የድሬዳዋ ከተሞች አካል ጉዳተኞችን በማካተት ረገድ ያስመዘገቧቸውን ስኬቶችና የተሻገሯቸውን ተግዳሮቶች በተሞክሮ መልክ ሲያቀርቡ ለሌሎች ከተሞች እንደ ተግባራዊ ትምህርት ሆኖ አገልግሏል። ይህ የተሞክሮ ልውውጥ በውይይት የታጀበ በመሆኑ ተሳታፊዎች ጥያቄዎችን እንዲጠይቁና የራሳቸውን ልምድ እንዲያጋሩ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ከዚህ በተጨማሪም ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የቀረበው የውይይት ሰነድ ችግሩን ከሀገራዊ ፖሊሲ አንጻር በመተንተን ለውይይቱ ሰፊና ስትራቴጂካዊ ይዘት ሰጥቶታል።

የመርሃ ግብሩ ዋነኛ ትኩረት ዕውቀቱ በአውደ ጥናቱ አዳራሽ ብቻ እንዳይቀር ዘላቂነቱንና ስርፀቱን ማረጋገጥ ነበር። ይህንን ለማሳካትም የቀረቡት የተሞክሮ ሰነዶች እና የውይይት ሰነድ በዲጂታል መልክ (soft copy) ተዘጋጅተው በጋራ በተከፈተው የቴሌግራም ቡድን እና በትብብር መድረኩ ድረ-ገጽ ላይ ተጭነዋል።



ምስል፡30 የተሳታፊዎች የጋራ ፎቶ

- **በከተሞች መካከል የእውቀት ሽግግርን ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመምራትና ስኬታማ ተሞክሮዎችን በቀላሉ ሊተገበሩ በሚችሉበት አግባብ ለማሰራጨት የሚያስችል አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ሰነድ በተለያዩ ከተሞች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በምን መልኩ ወደ ተሞክሮ ሰነድ መቀመር እንደሚቻል የሚያሳይ እንደ መመሪያ** (blueprint) **ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሰነዱ በቀላሉ ዝርዝር ርዕሶችን ከማቅረብ ባለፉ እያንዳንዱን የልማት ዘርፍ በጥልቀት በመመርመር የተሞክሮ ሰነዱ ሊመልሳቸው የሚገቡ ቁልፍ ጭብጦችንና የትንተና ነጥቦችን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ የዚህ ሰነድ ዋነኛ ውጤት የተበታተኑ ስኬቶችን ወጥና ደረጃውን የጠበቀ የተሞክሮ ሰነድ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓታዊ ማዕቀፍ** (Systematic Framework) **መፍጠሩ ነው፡፡ ሰነዱ ለእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ሊቀመር የሚገባውን ጭብጥ በግልጽ ይቀርጻል፡፡ ለምሳሌ፣ "ስማርት ሲቲ" በሚለው ጭብጥ ስር አንድ ከተማ ከፖሊሲ ቀረጻ አንስቶ የቴክኖሎጂ አተገባበርንና የአገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ያስገኘችውን ውጤት እንዴት መመዝገብ እንዳለበት ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ "ካዳስተር" በሚለው ዘርፍ የህግ ማዕቀፉን፣ የዲጂታይዜሽን ሂደቱንና በመሬት ባለቤትነት ላይ ያመጣውን ለውጥ እንዴት**

መተንተን እንደሚቻል አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ "የኮሪደር ልማት" በሚለው ርዕስ ሥር የኢኮኖሚ፣ የአረንጓዴ ልማትና የትራንስፖርት መሠረተ ልማትን በማቀናጀት የተገኘን ስኬት እንዴት በሰነድ መያዝ እንደሚቻል ያመላክታል፡፡

በአጠቃላይ ሰነዱ የመሬት ውስጥ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ካዳስተር፣ ስማርት ሲቲ፣ የከተማ ግብርና፣ ኢንቨስትመንትና ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ፤ የሞተር አልባ እና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት፣የአንድ ማዕከል አገልግሎት እና የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ያሉትን ወሳኝ የአገልግሎት ዘርፎችንም በማካተት የትኞቹ ተሞክሮዎች በምን መልኩ ተቀርጸው ለሌሎች ከተሞች ትምህርት ሊሆኑ እንደሚችሉ ግልጽና ተግባራዊ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይህም የተሞክሮ ልውውጡ በዘፈቀደ ሳይሆን በተቀናጀና ውጤት ተኮር በሆነ መንገድ እንዲመራ በማድረግ የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

6. ያጋጠሙ ችግሮች፤የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤

6.1. ያጋጠሙ ችግሮች

- በ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተግዳሮቶች አጋጥመዋል፡፡ በዋነኝነት በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የነበረው የጸጥታ ችግር በዕቅድ የተያዙ ሥራዎችን በወቅቱና በተፈለገው ደረጃ ለማከናወን ትልቅ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህ ሁኔታ የጉዞ ገደቦችን ከመፍጠሩም ባሻገር የታቀዱ የልምድ ልውውጦችንና የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ለማካሄድ የሚያስችል አስተማማኝ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ የመርሃ ግብሮችን መስተጓጎልና መሰረዝ አስከትሏል፡፡ (ለምሳሌ የኦሮሚያ እና የአማራ ክልሎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች)፤

- የተወሰኑ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችና አውደ ጥናቶችን ለማስኬድ ያጋጠመው የበጀት እጥረት ሌላኛው ቁልፍ ተግዳሮት ነበር፡፡ ይህም ችግር በተለይ በርካታ ተሳታፊዎችን የሚያሳትፉና ከፍተኛ ሎጂስቲክስ የሚጠይቁ ወሳኝ ተግባራትን እንዳይከናወኑ በማድረግ እክል ፈጥሯል፡፡

- በሌላ በኩል ለውጭ አገር የልምድ ልውውጥ የተመረጡ አንዳንድ ከንቲባዎች አስፈላጊውን የጉዞ ፈቃድ በወቅቱ ባለማግኘታቸው ምክንያት በፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡

- **ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት** በመኖሩ የተነሳ የትብብር መድረኩ ሁለትና ሶስት የስልጠናና ልምድ ልውውጥ መድረኮችን ለማዘጋጀት እቅዶ የነበረውን ለአንድ መድረክ ለማዋል ከማስገደዱም በላይ ለነዳጅና ትራንስፖርት እንዲሁም ለምሳና ሪፍሬሽመንት የሚወጡ ወጪዎችን በእጥፍ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ በዚህም የቢሮ ዕቃ ግዢ ሙሉ በሙሉ እንዲቀርና ለመስጠት የታቀዱ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲሰረዙ አድርጓል፡፡

- የዩኤልጂ ፕሮጀክት ይሸፍን የነበረው 40 በመቶ የአስተዳደራዊና ፕሮግራም ወጪዎች ክፍያ ፕሮጀክቱ በመጠናቀቁ የተነሳ በተቋም ላይ ጫና መፍጠሩ፤

- የድርጅቱ የቢሮ ኪራይ ወጪ ከሚያዝያ 1/2017 ዓ.ም ጀምሮ በእጥፍ የጨመረ መሆኑ፤

- የከተሞች አመታዊ መዋጮ ክፍያ የመክፈል ፍላጎት የጨመረ ቢሆንም የጸጥታ ችግርና ከተሞች እየተገበሩ ካሉት ወቅታዊ ፕሮጀክቶች(ኮሪደር ልማት) ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የበጀት እጥረት እየገጠማቸው በመሆኑ የተነሳ **15 አባል ከተሞች ሙሉ በሙሉና** 25 ከተሞች ደግሞ በከፊል አመታዊ የአባልነት መዋጮ በወቅቱ ባለመክፈላቸው ብር 17,495,000.00 ተሰብሳቢ ሆኖ ለቀጣይ የበጀት ዓመት ተሻግሯል፡፡

6.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- በሃገሪቷ የተረጋጋ ሁኔታ አለመኖሩ ለዕቅድ አፈጻጸም እንደችግር ቢስተዋልም በአንጻራዊነት ሰላም የሆኑ ከተማ አስተዳደሮች ጋር ስራዎችን ለማከናወን ተችሏል::
- ከንቲባዎች በሚመቻቸው ወቅት እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- አባል ከተሞች ያለባቸውን አመታዊ መዋጮ እንዲከፍሉ በተደጋጋሚ ማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፤

6.3. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የትብብር መድረኩን የህንጻ መገንቢያ መሬት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መረከብና ለቀጣይ ተግባር ዝግጅት ማድረግ፣

- የተሰራውን የድርጅቱ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ በማጸደቅ ስራዎችን መተግበር እንዲሁም ከመዋቅሩ ጋር ተናባቢ የሆኑ ማኑዋሎችና መመሪያዎች ዝግጅት ማድረግ፤

- እያጋጠመ ካለው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበትና አባል ከተሞች ተቋሙ ከሚያመቻቻቸው የስልጠና፤ የልምድ ልውውጥና የውጭ አገር ትምህርታዊ ጉዞዎች ለመጠቀም ያላው ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ የጨመረ እና ከተቋሙ አቅም በላይ እየሆነ በመሆኑ በቀጣዩ በጀት ዓመት የከተሞችን የአመታዊ መዋጮ ማሻሻል እንደሚገባ ያሳያል፡፡
- የተሻሉ ተሞክሮዎች በአባል ከተሞች እንዲተገበሩ እና የትግበራውን ሂደት የመስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ በሂደቱም የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት ለከተሞቹ አስፈላጊው ድጋፍ ማድረግ፤
- በወጪ መጋራት አግባብ መሰረት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢውን ግንኙነት በመፍጠር መስራት፤
- የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በስፋት በመተግበር ቀጣይነት ያለውና የተጠናከረ የሥራ አካል ማድረግ፤
- በቀጣይ ዓመት በሰመራ ሎጊያ ለሚካሄደው 10ኛው የከተሞች ፎረም ተገቢውን ዝግጅትና ተሳትፎ ማድረግ፤
- ትብብር መድረኩ ከአለም አቀፍ አጋሮች ድርጅቶች (አውሮፓ ህብረት፣ ከኔዘርላንድስ ማዘጋጃ ቤቶች ማህበር (VNG)፣UCLG-CIB Working Group፤ BRICS+ እና ሌሎችም ድርጅቶች) ጋር የጀመረውን የኔትወርኪንግ ስራ አጠናክሮ በመቀጠል ወደ ተጨባጭ የፕሮጀክት ትብብር በማሸጋገር አባል ከተሞች የአቅም ግንባታ ስልጠና እና ልምድ እንዲያገኙ በትኩረት መስራት፡፡
- የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ባለስልጣን መ/ቤቱ አዲስ ባዘጋጀው የበጎ አድራጎት ማህበር ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተሻሽሎ እንዲቀርብ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት አሻሽሎ በጠቅላላ ጉባኤ ማጸደቅ፤
- በተጨማሪም ከላይ እንደ ችግር የተስተዋሉ ጉዳዮች በቀጣይ የሥራ ዘመን እንዳይደገሙ ከስራ አስፈጻሚ ቦርድ አመራሩ ጋር በመነጋገር መፍትሄ መፈለግ ይገባል፡፡ ለአብነትም የበጀት እጥረትን ለመቅረፍ ከአባላት አመታዊ ክፍያ ባለፈ አማራጭ የገቢ ምንጮችን በስፋት ማፈላለግና ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር

በመተባበር የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት መሥራት ወሳኝ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆን እንዳለባቸው አመላክቷል።

7. የማስፈጸሚያ ስልቶች፤

7.1 ክትትልና ድጋፍ

- የትብብር መድረኩ አባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎችን የክህሎት እና የእውቀት ክፍተቶችን ለመሙላት በሚዘጋጁ መድረኮች የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተከናውኗል።

- የስልጠና ተሳትፎ ምጣኔ እና የተሳታፊዎች አስተያየትን መነሻ በማድረግ በቀጣይ በሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና ልምድ ልውውጥ መድረኮች የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ተደርጓል።

- የተቀመሩ መልካም ተሞክሮዎች፣ የስልጠና ሰነዶች፣ የዘርፉ የህግ ማዕቀፎች እና ሌሎችም ለአባል ከተሞች ተደራሽ እንዲሆኑ የድርጅቱ ይፋዊ ድረገጽ በየጊዜው በአዳዲስ ሰነዶች እንዲደራጅና ለከተሞች እንዲደርስ ተደርጓል።

- በአባል ከተሞች መካከል የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማመቻቸት የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ እና ተባብሮ የመስራት ባህል እንዲጎለብት በማድረግ ለከተሞች ድጋፍ ተደርጓል።

- በከተሞች የተተገበሩ መልካም ተሞክሮዎችን የመለየትና የመቀመር ስራ በመስራት የእውቀት ሽግግርና ስርጸት ስርዓት ለማረጋገጥ ከተሞች ምርጥ ተሞክሮ ሰነድ እንዲያዘጋጁ ተከታታይነት ያለው የእውቀት ስራ አመራር የድጋፍ ተደርጓል።

7.2 ግምገማ፤ ሪፖርትና ግብረ-መልስ

- በተቋም ደረጃ በየሳምንቱ መጨረሻ የስራ ግምገማ በማድረግ ክፍተቶች ተለይተው ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ በማኔጅመንት ውይይት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፤

- የስልጠናዎችና አውደጥናቶች ዝክረ ተግባርና አፈጻጸም ሪፖርት በዝርዝር ተዘጋጅቷል፣
- ለሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና መርሃ ግብር በማመቻቸት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ተደርጓል፤

- የሩብ ዓመት፤የግማሽ ዓመት፤ የዘጠኝ ወርና የአመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቷል እንዲሁም ተገምግሟል።
- የስልጠናና አውደጥናት አቀራረብን አስመልክቶ በተሳታፊዎች የሚሞላ የመገምገሚያ ቅጽ በማዘጋጀት መረጃ በመሰብሰብ ትንተና እንዲሁም የግብረመልስና ግምገማ ስራ እንዲሰራ በማድረግ ለቀጣይ ተግባራት በግብዓትነት እንዲወሰድ ተደርጓል። በተጨማሪም የልምድ ልውውጥ እና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ከተሞች ያላቸውን ውጤታማ ስራ እና ሊያስተምር የሚችል መልካም ተሞክሮ ለሌሎች ማካፈል እንዲቻል እንዲሁም የእውቀት እና የክህሎት ክፍተቶችን በስልጠና ለመሙላት ይቻላቸው ዘንድ የከተሞችን ፍላጎት ለማካተት ታስቦ መረጃ ተደራጅቷል።

8. በበጀት አመቱ አፈጻጸም በጥንካሬና በድክመት የታዩ ጉዳዮች፤

8.1. በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮች

- ትብብር መድረኩ የ20 ከተሞችን የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነክ ጉዳዮችን ዝርዝር ጥናት እንዲከናወን ማድረጉ በመረጃ ላይ ለተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ ግብዓት መሆን መጀመሩና ይህንኑ መሰረት በማድረግ ዘመናዊና ተጠቃሚን የሚያሳትፍ "የኢትዮጵያ ከተሞች ዳሽቦርድ" ተሰርቶ ለህዝብ ይፋ መደረጉ፤
- የትብብር መድረኩ ባመቻቻቸው የውጭ አገራት የልምድ ልውውጥ መድረኮች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ከተሞች እንዲማሩባቸውና እንዲጠቀሙባቸው የእውቀት ሽግግርና ስርጸት በከፍተኛ ሁኔታ የተሰራ መሆኑ፤

- የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ስብሰባና የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በወቅቱ መካሄዱ፤
- የኦዲት ሪፖርት አፈጻጸም ጥሩ(*Unqualified*) መሆኑ፤
- የአባል ከተሞች የክፍያ አፈጻጸም ከዚህ በፊት ከነበረው እየተሻሻለ መሆኑና ቦርድ ያስቀመጠውን አቅጣጫ አብዛኛው ከተሞች ተቀብለው እየፈጸሙና የመክፈል ፍላጎታቸውም እየጨመረ መሆኑ(ባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት 48(61%) ነባር ከተሞች አመታዊ ክፍያ የፈጸሙ ሲሆን አሁን ላይ 81(85%) ከተሞች የአመታዊ

መዋጮ ክፍያቸውን ፈጽመዋል። ከ17,495,000.00 ተሰብሳቢ ውዝፍ ክፍያ ከ2012-2016 ዓ.ም 3,650,000 ብር ብቻ ሲሆን ቀሪው የ2017 በጀት ዓመት ያልተከፈለ መሆኑን ያሳያል።

- በሌላ በኩል የስራ አስፈጻሚ ቦርድ በሰጠው የስራ አቅጣጫ መሰረት ከውጭ የተገኙ በርካታ ተሞክሮዎች ተቀምረው ለአባል ከተሞች በህትመትና በዲጂታል መልኩ እንዲሰራጩ በማድረግ ከፍተኛ የእውቀት ሽግግርና ስርጸት ስራ ተሰርቷል።

- ትብብር መድረኩ ከውጭ አገራት ባለድርሻ አካላት ለአብነትም ከUCLG፤ BRICS+ እና ሌሎች መሰል ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ የስራ ግንኙነት መፈጠሩ የትብብር መድረኩን በአለም አቀፍ መድረኮች ከፍ ከማድረጉም በላይ ለትብብር መድረኩ እና አባል ከተሞች በቀጣይ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች እያደረገ መሆኑ። ለአብነትም ትብብር መድረኩ ባከናወናቸው የኔትወርኪንግ ስራዎች መሰረት የብሪክስ አገራት ከተሞች እና ማዘጋጃቤቶች ማህበር በመመስረት ረገድ ጉልህ ተሳትፎ ከማድረጉም በላይ ትብብር መድረኩ የማህበሩ አባል እንዲሆን ጥያቄ የቀረበ መሆኑ። በተጨማሪም ከተለያዩ አህጉር አቀፍና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ከፈጠራቸው የኔትወርኪንግ ስራዎች የተነሳ ለአባል ከተሞች ከንቲባዎች በየትኛውም ጊዜ የውጭ አገር ልምድ ልውውጥ ፕሮግራም ለማመቻቸት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

- የትብብር መድረኩን አገልግሎቶችና የከተሞችን አጠቃላይ ገጽታ በተመለከተ 'የከተሞች ድምጽ' በሚል ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄትና 'ሲቲ ኦፍ ዘ ዊክ' በሚል ሳምንታዊ ፖስተሮችን ዲዛይን በማድረግ መሰራቱ እንዲሁም የሚዘጋጁ የስልጠናና አውደጥናት መድረኮችን አፈጻጸም በአገር ውስጥ በሚገኙ የሜንስትሪም ሚዲያ፤ ሶሻል ሚዲያና ፕሪንት ሚዲያዎች እንዲዘገቡና ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ በከፍተኛ ሁኔታ መሰራቱ፤

- በበጀት አመቱ 23 **የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ከንቲባዎች እንዲሁም የሴክሬታሪያቱ ማኔጅመንት አባላት በተለያዩ የውጭ አገራት** በመሄድ ጠቃሚ ልምድና ተሞክሮ እንዲቀስሙ ተደርጓል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኪሱሙ ኬንያ በተካሄደው የ4ኛው የከተማ ኢንቨስትመንት ጉባኤ ላይ የተሳተፈው ልኡክ ቡድን አስመልክቶ የትብብር መድረኩ ለክልላዊና አካባቢያዊ መንግስታት አቅም ግንባታ የሰጠውን ትኩረትና የልኡክ ቡድኑ አባላት ላደረጉት ንቁ ተሳትፎ የአፍሪ ኤግዚም ባንክ የምስጋና ደብዳቤ መላክ ችሏል።

- በትብብር መድረኩ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ የታየው ከፍተኛ የተሳታፊዎች ቁጥር (High Participation Rates) የተቋሙ ሥራዎች በአባል ከተሞች ዘንድ ያላቸውን ተፈላጊነትና ፋይዳ በግልጽ የሚያሳይ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ የስራ አፈጻጸም የ20/80 ምጣኔን ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ መልካም አፈጻጸም መገኘቱ(የፕሮግራም ወጪ 80% እና የአስተዳደር ወጪ 20% መሆኑ)፤
- የዩኤልጂ 4 ዓመት ፕሮጀክትን በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ በተቀመጠለት ጊዜ መዝጋት መቻሉ እና ሪፖርት መደረጉ እንዲሁም የዩኤልጂ ፕሮጀክት የመጨረሻ ዘመን ግምገማ በገለልተኛ አማካሪ ድርጅት እንዲከናወን በአማካሪ ቅጥር ልየታና ለአማካሪ ድርጅቱም በፕሮጀክቱ አፈጻጸምና ባመጣቸው ውጤቶች ዙሪያ በተለያዩ አግባቦች የተደራጀ መረጃ መሰጠቱ ይገኝበታል።

8.2. *በድክመት የታዩ ጉዳዮች*

- አማራጭ የገቢ ምንጮችን በስፋት ማፈላለግና ማግኘት አለመቻሉ፣
- በወጪ መጋራት ይከናወናሉ ተብለው የታቀዱ ተግባራት አለመከናወናቸው
- በአገር ውስጥ የከተሞችን የእህትማማችነት ቁርኝት/City twininning) ስራ በተሟላ ደረጃ አለመሰራቱ ይገኝበታል።

9. ማጠቃለያ


የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በ2017 በጀት ዓመት በአባላት አቅም ግንባታ እና በእውቀት ሽግግር ላይ ያተኮሩ በርካታ ተግባራትን በማከናወን እጅግ አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም ትብብር መድረኩ የከተሞችን የአመራር ብቃት ለማሳደግ እና ለዘርፉ እድገት ወሳኝ የሆኑ ዕውቀቶችን ለማደራጀት ያለውን ቁርጠኝነት በጉልህ ያሳየበት የስኬት አመት ነበር፡፡

- በበጀት ዓመቱ ከተመዘገቡት ጎላ ያሉ ስኬቶች መካከል የአቅም ግንባታ ሥልጠና በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ በዚህም የከተማ ልማትን በበላይነት የሚመሩ 156 የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ከንቲባዎች፣ የማዘጋጃቤት ስራ አስኪያጆች እና የክልል ከተማና መሠረተ ልማት ዘርፍ ቢሮ ኃላፊዎች እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን የሚያሳድግ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በአመቱ ውስጥ በትብብር መድረኩ አምስት ስልጠናዎችንና ሁለት አውደጥናቶች የተዘጋጁ ሲሆን በሁሉም መድረኮች መገኘት ከነበረበት የተሳታፊ ቁጥር ተቀራራቢና ከፍተኛ የተሳታፊዎች ቁጥር (High Participation Rates) የታየባቸው ሲሆን ለአብነትም በድሬደዋ(133 በመቶ)፤ በጅግጅጋ (157 በመቶ)፤ በአርባምንጭ (86 በመቶ)፤በመቀሌ (106 በመቶ) እንዲሁም በሃዋሳ (80 በመቶ) መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሚፈጠሩ መድረኮች አስፈላጊነትና ጥራት እንዲሁም የተቋሙ ተቀባይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑንና ክቡራን ከንቲባዎች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሲቀሩ እንኳን ተወካይ የሚልኩበት፤ልምድ የሚያጋሩ ከተሞች ለሌሎች ተገቢነት ያለው ተሞክሮ የሚያቀርቡ መሆኑን እንዲሁም የመስክ ጉብኝት ተሞክሮዎች አስተማሪነታቸው የጎላና አባል ከተሞች ያገኙትን ልምድ ለመተግበር ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየገቡ ያለበትን ሁኔታ ያሳያል፡፡ ይህ የተሳታፊዎች ቁጥር ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ52 ተሳታፊዎች እድገት ያስመዘገበ ሲሆን ይህም የመድረኩን ስኬታማነትና እያደገ የመጣውን ተደራሽነት በግልጽ ያሳያል፡፡

- የተሞክሮ ሰነዶች የመቀመርና የማዘጋጀት ስራን በተመለከተ ከዓለም አቀፍ መድረኮች የተገኙ ስድስት ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲሁም በአገር ውስጥ የተገኙ ስምንት ስኬታማ ተሞክሮዎች በድምሩ አስራ አራት (14) የተሞክሮ ሰነዶች ተዘጋጅተው

ለእውቀት ሽግግር ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ለከተሞች ሁለንተናዊ አገልግሎት የሚሆን ጠንካራ የእውቀት ክምችት ተፈጥሯል፡፡ተከ

- የተሰበሰበውን እውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥና ከተሞች በቀጥታ ልምድ እንዲለዋወጡ ለማስቻል ወሳኝ የልምድ ልውውጥ መድረኮች በስኬት ተዘጋጅተዋል፡፡ በአገር ውስጥ በከተማ ፕላን አፈጻጸም (በተለይም በኮሪደር ልማት) እና የአካል ጉዳተኞችን በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች አካታችነትና ተጠቃሚነት ዙሪያ በተዘጋጁ አውደ ጥናቶች 115 ባለሙያዎችና አመራሮች ልምድ እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም፣ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም እንዲቻል 23 ከንቲባዎችና ሌሎች አመራሮች በተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች ላይ ተሳታፊ በመሆን በርካታ እውቀቶችን የቀሰሙ ሲሆን የሀገራችንን የከተማ ልማት እንቅስቃሴም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲተዋወቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡



ቻርት 1፡- *የ2017 እና የ2016 በጀት ዓመታት ተመሳሳይ ወቅት የልምድ ልውውጥና የስልጠና ተሳፊዎች ብዛት እንዲሁም የተሞክሮ ሰነድ ቅመራ ሰነድ ብዛት በቁጥር ንጽጽር*

- የከተሞች አመታዊ መዋጮ ክፍያ አፈጻጸምን በተመለከተም በበጀት አመቱ ከ96 ነባር አባል ከተሞች 81(85 በመቶ) ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ ባለፈው አመት ክፍያ ፈጽመው

ከነበረው 48 ነባር ከተሞች(61 በመቶ) አንጻር ሲታይ የመክፈል ፍላጎት የጨመረ እንደሆነ ያሳየ ቢሆንም 15 ከተሞች ሙሉ በሙሉ እና 25 ከተሞች ደግሞ በከፊል በተለያዩ ምክንያቶች የአባልነት ክፍያ ባለመክፈላቸው *17,495,000.00* ብር ውዝፍ ያልተሰበሰበ መሆኑን ያሳያል፡፡

- ትብብር መድረኩ በተዘጋጁ የስልጠናና አውደጥናት መድረኮች ላይ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ ብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች የመጡ 51 ጋዜጠኞችን በመጋበዝ የዘገባ ስራ የሰሩ ሲሆን የተዘገቡ ዜናዎችን የሚዲያ ሞኒቴሪንግ ስራ በማከናወን በትብብር መድረኩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም በአገር አቀፍና በተለያዩ የክልሎች ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲተላለፍና የተቋሙን አገልግሎቶችና ተልዕኮ በማስተዋወቅ የተቋሙን እይታ እንዲጨምር ተደርጓል፡፡

በጠቅላላው የ2017 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ በአመራር ብቃት ማጎልበት፣ በእውቀት ክምችት መገንባት እና በተግባራዊ የልምድ ልውውጥ መድረኮች አማካኝነት ዓላማዎቹን በላቀ ደረጃ ያሳካበት እንዲሁም የተቋሙን እይታና ግጽታ ከፍ በማድረግ ረገድ እጅግ ውጤታማ ዓመት ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ ስኬት ለቀጣይ የከተሞች እድገትና ብልጽግና ጠንካራ መሰረት የጣለ ሲሆን የትብብር መድረኩን ቁልፍ ሚናም ዳግም ያረጋገጠ ሆኗል፡፡

አባሪ፡- በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የ2017 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ማጠቃለያ፤

ተቁ	የተከናወኑ ግቦች	የአመቱ ዕቅድ	ክንውን	አፈጻጸም በ%	ምርመራ
	I.የተከናወኑ ግቦችና ተግባራት አፈጻጸም				
1	ከነባርና አዲስ አባል ከተሞች ገቢ መሰብሰብ	40,350,000.00	22,230,000.00	56%	
1.1	ከነባር አባል ከተሞች	37,200,000.00	20,405,000.00	54.8%	
1.2	ከአዲስ አባል ከተሞች	3,150,000.00	1,825,000.00	57.9%	
2	ከውጭ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ ገቢ መሰብሰብ	5,304,776.44	5,304,776.44	100%	
3	ከአገር ውስጥ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ ገቢ መሰብሰብ	3,000,000.00	-	-	
4	የተቋሙን ሰራተኞች አቅም ለማጎልበት በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡	9	4	44%	
5	የትብብር መድረኩን የ2016 ዓ.ም ዓመታዊ የሂሳብ ሰነድ አዲት ማስደረግና የ2017 እቅድና በጀት ማጸደቅ	100%	100%	100%	
6	የትብብር መድረኩን አንድ መደበኛ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ማድረግ	100%	100%	100%	
7	የትብብር መድረኩን አንድ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ማካሄድ	100%	100%	100%	
8	በለጋሽ ድርጅቶች በሚወጡ ማስታወቂያዎች መሰረት ሶስት የሃብት ማፈላለጊያ ኮንሴፕት ኖቶች እና ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት ብር ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ገቢ ማድረግ፣	5	2	67%	
		5,000,000.00	-	-	
9	በወቅታዊ የከተማ ልማት አጀንዳዎች" ዙሪያ ያተኮረ በ100 አባል ከተሞች መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደጥናት ተካሂዷል፡፡	100	80	80%	

10	ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተማ ከንቲባዎችና የማኔጅመንት አባላት የተውጣጡ 28 ተሳታፊዎች በተለያዩ አለም አቀፍ ጉባዔዎች እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 23ቱ ተሳትፈዋል፡፡	28	23	82%	
11	ለ30 የሱማሌ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በህዝብ ተሳትፎ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጧል፡፡	30	47	157%	
12	ለ30 የትግራይ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች ባልተማከለ አስተዳደር፣ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በከተሞች ምግብ ዋስትና" ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ40 ተሰጥቷል፡፡	30	40	133%	
13	ለ19 የቤኒሻንጉል ጉሙዝና የጋምቤላ ክልል ከተሞች ከንቲባዎች፤ ስራአስኪያጆችና የክልል የስራ ሃላፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደርና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ16 ተሰጥቷል፡፡	19	16	84%	
14	ለ22 የደቡብ ኢትዮጵያ፤ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ ሲዳማና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች አባል ከተሞች ከንቲባዎች፤ ስራአስኪያጆችና የክልል የስራ ሃላፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደርና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ19 ተሰጥቷል፡፡	22	19	86%	
15	ለ32 የትግራይ ክልል ከተሞች ስራአስኪያጆችና የክልል የስራ ሃላፊዎች ባልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደርና በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ34 ተሰጥቷል፡፡	32	34	106%	

16	ከተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ አገር መሰል ተቋማትና ድርጅቶችጋር የስራ ግንኙነትና የአጋር አካላት ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡	100%	100%	100%	
17	የ ULGE ፕሮጀክት 100 ቡክሌትና የተሞክሮ ሰነዶች ለማሳተም ታቅዶ 260 ኮፒ የተሞክሮ ሰነዶች ታትመዋል፡፡	100	260	260%	
18	የትብብር መድረኩ የአባል ከተሞች ቁጥር 96 ከነበረበት ወደ 111 እንዲያድግ ተደርጓል፤	30	15	50%	
19	የትብብር መድረኩን አገልግሎቶችና አጠቃላይ ገጽታ የሚያስተዋውቅ 12 ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄት ለማዘጋጀት ታቅዶ 11 የዜና መፅሔቶች ተዘጋጅተዋል፡፡	12	11	92%	
20	የአባል ከተሞችን አጠቃላይ ገጽታ የሚያስተዋውቅ 48 የሳምንቱ ከተማ ፖስተር ለማዘጋጀት ታቅዶ 48 ተዘጋጅተዋል፡፡	48	48	100%	
21	በአመቱ ውስጥ የትብብር መድረኩ ባዘጋጃቸው 5 ስልጠናዎችና 2 የአገር ውስጥ የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶች ላይ ጋዜጠኞችን በመጋበዝ የዘገባ፣ የቀረጻና የዶክመንቴሽን ስራዎች በማከናወን የተቋሙ ገጽታና እይታ እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ የግቡ አፈጻጸም መቶ በመቶ ነው፡፡	100%	100%	100%	
22	በተመረጡ ከተሞች የዘርፉን ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን (key performance indicators) መሰረት በማድረግ የመነሻ ሁኔታ መረጃዎችን በማሰባሰብ አንድ ጥናታዊ ሰነድ ተዘጋጅቷል	100%	100%	100%	
23	ከስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ የተቋማዊ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት ማካሄድ፡፡	100	100	100%	
24	የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ስትራቴጂክ ዕቅድ የመካከለኛ ጊዜ ግምገማ (Mid-Term Evaluation) ተካሂዷል፡፡	100%	100%	100%	
ወጪ	አስተዳደራዊ ወጪ		5,970,967.89	**20%**	
	የፕሮግራም ወጪ		23,442,697.36	**80%**	
	ጠቅላላ ወጪ		**29,413,665.25**		